ይድረስ:-

ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት!
በተለይም: በመጀመሪያው መንገዳችን ጊዜ: ሳንለያይ: አብረን ለተጓዝነው:-

በእግዚአብሔር ስም: ለኹለተኛ ጊዜ: ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን አቀርብላችኋለሁ::

የኢትዮጵያ መካነ አእምሮ ወደሚገኝበት: የእውቀት መዲና ለመጓዝ: ፈቃደኞች በመኾናችሁ: በድካም ሳትዝሉ: አንደኛውን ክፍል ጨርሳችሁ: እስከዚህ ለመድረስ ለቻላችሁት ኹሉ: አድናቆቴን እየገለጽሁ: እንደገና: "ኑ!" እላለሁ::

ወደዚያች: የመጨረሻዋ ማረፊያ ከተማ የሚያጓጉዛችሁ: ያ: በመንፈስ ቅዱስ የሚነዳው የውይይት ሠረገላ: ይኸው: አኹንም ተዘጋጅቶ: ኹለተኛ ጉዞውን ሊጀምር ይጠብቃችኋልና: ተሣፈሩ!

# ኢትዮጵያ
# እና
# ኢትዮጵያዊነት

"እኔ ምንድር ነኝ? ማንስ ነኝ?"
"እግዚአብሔር ማነው?"
"የተፈጥሮ ባልንጀራዬስ?"

*"ኢትዮጵያዊ መልኩን÷*
*ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ሊለውጥ ይችላልን?"*

ለዚህ አምላካዊ ቃል: ማብራሪያ÷
የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊው አንድነት:
በተዋሕዶ ምሥጢር ስለተገለጸባቸው:
ስለእነዚያ ሦስት ገጸ ባሕርያት: ለቀረቡት
ሰብአውያን ጥያቄዎችም: መልስ የተሰጠበት::

ኢትዮጵያ: በቅዱሱ ኪዳን: ከእግዚአብሔር ተቀብላ
ሕዝቧን: ከጥንት ጀምሮ የምታስተዳድርበት÷ ዛሬም:
ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቿ: በያሉበት:
ሕይወታቸውን የሚመሩበትን
ሥርዓተ መንግሥት የያዘ::

በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ

ዋጋው ብር 35

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤


የደራሲው ባለመብትነት፡ በሕግ የተጠበቀ ነው።

፲፱፻፺፯ ዓመተ ምሕረት።
Copyright © 2005 Ermias Kebede Wolde-Yesus

ይህን መልእክታዊና ትምህርታዊ መጽሐፍ፡ ደግሞም፡ *"ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ!"*፡ *"ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፍረጃ!"*፡ **Ethiopia: The Classic Case** እና "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት -አንደኛ መጽሐፍ" የተባሉትን፡ ሌሎችንም፡ ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን መጻሕፍት ለማግኘት፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ ባሳታሚው አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።

---

አሳታሚ እና አከፋፋይ
Publisher & Distributor
**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።**
**Ethiopia: The Kingdom of God Services**
መልእክት ሣጥን ቁጥር ፰፻፲፪ P. O. Box 812
ስልክና ዕምነቅ ቁጥር፡ ፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና ፫-፳-00-፹፭
Tel. & Fax. 4-16-18-85 & 3-20-00-85
አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ። Addis Abeba, ETHIOPIA
ወይም or
**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**
**Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971**
Email: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org



### ከዚህ ገጽ ተቀዳሚ ላይ የሠፈረው፡ የመለከታዊው መንግሥት ምልክትና ማኅተም መግለጫ

በኅብረ ቀለማት የተከናወነው፡ ይህ ቅዱስ ዓርማ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው ኢትዮጵያ፡ መለኮታዊ ምልክቷና ታላቁ ማኅተሟ ነው፡፡

፩ኛ፡- በላይኛው ወገን ያለው፡ የአረንጓዴ፡ ብጫና ቀይ ቀለማትን የያዘው ሥዕላዊ ክበብ፡ ኖኅ፡ በቀስተ ደመና ምልክትነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ቃል ኪዳን የሚያመለክተው፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሲኾን፡ የሰንደቅ ዓላማውን፡ የአንድነቱንና የሦስትነቱን ምሥጢር፡ ከብዙው በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፡-

ሀ=ኸ) የአብ፡ የወልድ፡ የመንፈስ ቅዱስን፡ አንድ አምላክነት፡

ለ) የነፍስ፡ የሥጋንና የመንፈስን፡ አንድ ሰውነት፡

ሐ) የኢትዮጵያዊን አንድ የውሕደት ዘር፡ ሴማዊነት፡ ካማዊነትና ያፌታዊነት፡

መ) የኢትዮጵያን መለኮታዊ መንግሥት፡ ሕዝባዊነት፡ ክህነታዊነትና መለካዊነት ያስረዳል፡፡[፬]

፪ኛ፡- በመካከለኛው ወገን ያለው ሥዕላዊ ሰውነት፡ ኢትዮጵያ፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር እንደዘረጋች የሚያሳይ ሲኾን፡ ይህችው እመቤት፡ የአምላክ እናት፡ የጽዮንና የብሔረ ኢትዮጵያ፡ የፍጥረተ ዓለሙም ንግሥት የኾነችው፡ ድንግል ማርያም መኾኗን ያመለክታል፡፡[፭]

፫ኛ፡- በታችኛው ወገን ያለው ሥዕላዊ አካል፡ በብሉዩ ኪዳን፡ ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፡ ቀዳሚ ምሳሌው ኾኖ የተገለጸለትን፡ በአዲሱም ኪዳን፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" ተብሎ፡ በእግዚአብሔር ቃል የተነገረለትን፡ ዘለዓለማዊዉን ካህንና የጽዮንን ንጉሥ፡ የብሔረ ኢትዮጵያና የፍጥረተ ዓለሙም ንጉሠ ነገሥት የኾነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያሳያል፡፡[፮]

# ክ ፍ ል ኹ ለ ት፡፡

# "ፈጣሪዬ" የምለው

# እግዚአብሔር፣

# ማነው?

## ማ ው ጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ስለኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት ሓተታ:: | ፸፭ |
| ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሓተታ:: | ፸፱ |
| የጋብቻ ሥርዓት: በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተከብሮ ስለመኖሩ:: | ፹፱ |
| ስለኢትዮጵያና ስለእሥራኤል የበኩር ልጅነት ትርጓሜ:: | ፺፩ |
| እሥራኤል: ከኢትዮጵያውያን ስለተማሩት ሥርዓተ መንግሥት:: | ፺፭ |
| ጠላት: በሰንደቅ ዓላማችን ላይ ስላደረሰው ጠንቀኛ ጥቃት:: | ፺፯ |
| ምዕራፍ ፪፡ | |
| አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት:: | ፳፪ |
| ምሥጢረ ሥላሴ:: | ፳፬ |
| ስለቅድስት ሥላሴ:: | ፳፭ |
| የእግዚአብሔር አንድነትና በስም ሦስትነት:: | ፳፯ |
| የእግዚአብሔር አንድነትና በግብር ሦስትነት:: | ፳፰ |
| የእግዚአብሔር አንድነትና በአካል ሦስትነት:: | ፳፱ |
| የእግዚአብሔር አንድነት: በሦስትነት፡ ሦስትነት በአንድነት ምሥጢር:: | ፴ |
| ስለምሥጢረ ሥላሴ ማጠቃለያ:: | ፴፪ |
| ምሥጢረ ሥጋዌ:: | ፴፯ |
| እግዚአብሔር: ለምን ሰው መኾን ፈለገ? | ፴፰ |
| የሥጋዌ ምሥጢር የተገለጸበት ጊዜ:: | ፩፻ |
| የመለኮትና የትስብእት (የሰውነት) መዋሐድ:: | ፩፻፩ |
| የኢየሱስ ክርስቶስ: ኹለት ልደት:: | ፩፻፫ |
| "ተዋሕዶ"፡ "Orthodox" እና "Coptic" ስለሚባሉት ቃላት:: | ፩፻፬ |
| ስለምሥጢረ ሥጋዌ ማጠቃለያ:: | ፩፻፰ |
| ምሥጢረ ጥምቀት:: | ፩፻፱ |
| የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት:: | ፩፻፲ |
| የሰብአዊው ፍጡር ጥምቀትና የሚያገኘው ኹለተኛ ልደት:: | ፩፻፲፪ |
| ሕፃናት: በ፵ እና በ፹ ቀን ስለሚጠመቁበት ኢትዮጵያዊው ሥርዓት:: | ፩፻፲፭ |
| ስለኢትዮጵያውያን የጥምቀት ሥርዓት:: | ፩፻፲፱ |
| ስለምሥጢረ ጥምቀት ማጠቃለያ:: | ፩፻፳፪ |
| ምሥጢረ ቍርባን:: | ፩፻፳፯ |
| ቅዱሱ ቍርባን ፡ በስንዴ ኅብስትና በወይን ጭማቂ ስለመኾኑ:: | ፩፻፳፱ |
| ስለኅብስቱና ወይኑ: ወደመለኮት ሥጋነትና ደምነት መለወጥ:: | ፩፻፴ |
| ስለአዲሱ ኪዳን ጽላትና ታቦት:: | ፩፻፴፩ |
| የቅዱስ ቍርባን አስፈላጊነት:: | ፩፻፴፬ |
| ስለቅዱስ ቍርባን የሚደረገው ሥርዓተ ቅዳሴ | ፩፻፴፰ |

## ማ ው ጫ

| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ሞት ስለሌለባት የእግዚአብሔር መንግሥት:: | ፩፻፵፩ |
| ስለንስሐ፡ ፍቱን መድኃኒትነትና ስለመምህረ ንስሐ፡ ሥልጣን ክህነት:: | ፩፻፵፫ |
| ራስን ለካህን የማሳየት ትርጓሜ:: | ፩፻፶ |
| ከንስሓ ስለሚያርቁ ማስፈራሪያ መልእክቶች:: | ፩፻፶፬ |
| ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን:: | ፩፻፶፭ |
| የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ:: | ፩፻፶፱ |
| የሦስት መዓልትና የሦስት ሌሊት ስሌት:: | ፩፻፷፫ |
| የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ ለመዋቲው ሰው፡ ያቀዳጀው የድል አክሊል:: | ፩፻፷፬ |
| ስለትንሣኤ ዘጉባዔ:: | ፩፻፷፬ |
| ስለፊተኛውና ኋለኛው ትንሣኤ:: | ፩፻፸፩ |
| የምሥጢረ ትንሣኤ ነገር ሲጠቃለል:: | ፩፻፸፫ |
| በትንሣኤ ብርሃን ያሸበረቀውን የቀብር ሥርዓታችንን እናጨልመው! | ፩፻፸፭ |
| የእግዚአብሔር ሕያው ታሪኩ መገለጫ:: | ፩፻፹፩ |
| ትክክለኛው የኢትዮጵያውያን የሣልስትና የአርባ ቀን ሥርዓት:: | ፩፻፹፫ |
| ከትንሣኤ በኋላ ስላለው ህልውናችን:: | ፩፻፹፬ |
| ስለጌታችን ጾማ ምጽአትና ስለዓለሙ ፍጻሜ:: | ፩፻፹፱ |
| ትንሣኤ ሙታን አስፈላጊ የኾነበት ምክንያት:: | ፩፻፺፬ |
| የምጽአቱ፡ ምልክቶቹ እንጂ፡ ቀኑ፡ በትውልዱ ዘንድ ስለአለመታወቁ:: | ፩፻፺፱ |
| ከክርስትና ውጭ ስለኾኑት፡ ስለሌሎቹ ሃይማኖቶች:: | ፪፻፫ |

### ምዕራፍ ፬፤

ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ሥርዓቶች:: ፪፻፬

### ምዕራፍ ፭፤

ጸሎት:: ፪፻፲፩

| | |
| --- | --- |
| ስለጸሎት አስፈላጊነትና አፈጻጸሙ:: | ፪፻፲፫ |
| ስለኢትዮጵያውያን፡ የምስጋና እና የሰላምታ ጸሎታት ሓተታ:: | ፪፻፲፬ |
| "አባታችን እግዚአብሔር ሆይ!" ስለሚለው የምስጋና ጸሎት ሓተታ:: | ፪፻፳ |
| "እናታችን ማርያም ሆይ!" ስለሚለው፡ የሰላምታ ጸሎት ሓተታ:: | ፪፻፵፬ |
| መለኮት፡ በሰብአዊው ምርጫና ውሳኔ ውስጥ ያለው ተሳትፎ:: | ፪፻፷፪ |
| የሴቶች ርኩሰትና መርገም፡ በቅድስናና በበረከት ስለመተካቱ:: | ፪፻፷፰ |
| ለድንግል ማርያም ስለሚቀርበው ምስጋናና ስግደት:: | ፪፻፸፪ |
| ሥርዓተ ጸሎት:: | ፪፻፸፰ |
| የጸሎት ጊዜያት:: | ፪፻፸፬ |

## ማ ው ጫ

**አርእስት** — **ገጽ**


ምዕራፍ ፯፡
በዓል:: ፩፻፷፱

በዓል የምናከብርበት ምክንያትና ዓላማ:: ፩፻፷፱
ስለበዓላት ዝርዝር ሐተታና የበዓላቱ ስሞች ትርጓሜ:: ፩፻፸፪
የዕለቱ በዓላት:: ፩፻፹፯
የሳምንቱ በዓላት:: ፩፻፹፯
የወሩ በዓላት:: ፩፻፹፯
የወር በዓላት ስም ዝርዝር:: ፩፻፺
የዓመቱ በዓላት:: ፩፻፺፮
የጌታ የልደት በዓል፡ መስከረም ፩ ቀን ስለመኾኑ:: ፪፻፫
የጌታ ልደት፡ ከነአጽዋማቱና በዓላቱ፡ ከቀመሩ አዋጅ ተለይቶ ስለመኖሩ:: ፪፻፱
ስለስሕተቱ፡ መኖሩንም ስለማወቅና ስላለማወቅ:: ፪፻፲፪
የኢትዮጵያውያኑ የዘመን አቆጣጠር፡ ከሌሎቹ የሚለይበት ባሕርይ:: ፪፻፲፫
የጌታን የልደቱን ቀን ማናጋት፡ ያስከተለው ብርቱ ጠንቅ:: ፪፻፴፪
ስለገና ዛፍ:: ፪፻፴፫
ስለሺሁ ዓመት:: ፪፻፴፫
የጌታ የልደቱ ቀን፡ ወደተገቢ ቦታው ስለሚመለስበት መንገድ:: ፪፻፴፯
ስለቅድስት ድንግል ማርያም የልደት ቀን:: ፪፻፴፰
"ዓበይት" እና "ንዑሳን" በዓላት:: ፪፻፵፪
ርእሰ ዐውደ ዓመት:: ፪፻፵፬
በበዓሉ የሚፈጸሙ ሃይማኖታውያን ባህሎች:: ፪፻፵፯
የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት:: ፪፻፵፱
የድንግል ማርያም በዓለ ልደት:: ፪፻፶
በዓለ ግዝረት:: ፪፻፶፱
በዓለ ስምዖን:: ፪፻፶፱
በዓለ መስቀል:: ፪፻፷፮
ደመራ:: ፪፻፷፮
የእውነተኛው መስቀል ፍለጋና ስለመገኘቱ:: ፪፻፷፪
ዕሌኒ ንግሥትና ልጇ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ:: ፪፻፷፬
የመስቀሉ ነገርና ኢትዮጵያዊው አጼ ዳዊት:: ፪፻፷፯
ወርኀ ጽጌ:: ፪፻፸
ጾመ ስደትና ማኅሌተ ጽጌ:: ፪፻፸፮
ዘመነ አስተምህሮ:: ፪፻፸፪
የኅዳር ሚካኤል:: ፪፻፸፫

## ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| የኅዳር ጽዮን፡፡ | ፫፻፴፬ |
| ዘመነ ነቢያት፡፡ | ፫፻፴፭ |
| ዕለተ ትስብእት፡፡ | ፫፻፴፭ |
| ብሥራተ ገብርኤል፡፡ | ፫፻፴፮ |
| ዕንሰታ ለማርያም፡፡ | ፫፻፴፮ |
| ስለቅድስት ድንግል ማርያም ፅንሰት፡፡ | ፫፻፴፮ |
| በኣታ ለማርያም፡፡ | ፫፻፵ |
| ድንግል ማርያም፡ በስእለት የተገኘች ልጅ ስለመኾኗ፡፡ | ፫፻፵፩ |
| የታኅሣሥ ገብርኤል፡፡ | ፫፻፵፪ |
| ዘመነ ስብከት፡፡ | ፫፻፵፫ |
| የጥር ሥላሴ፡፡ | ፫፻፵፬ |
| ዘመነ አስተርእዮ፡፡ | ፫፻፵፬ |
| በዓለ ጥምቀት፡፡ | ፫፻፵፭ |
| ጥምቀት፡ የእኛም፡ የየማላችን በዓል ስለመኾኑ፡፡ | ፫፻፵፮ |
| ቃና ዘገሊላ፡፡ | ፫፻፵፯ |
| የድንግል ማርያም፡ እመ አምላክነትና እማላጅነት፡ በይፋ የታወቀበት ሠርግ፡፡ | ፫፻፵፱ |
| የቅዱሳን አማላጅነት ተረጋግጦ የተመሰከረበት ኹኔታ፡፡ | ፫፻፶፬ |
| አስተርእዮ ማርያም፡፡ | ፫፻፶፭ |
| የድንግል ማርያም፡ የዕረፍቷ፡ የትንሣኤዋና የዕርገቷ ዜና፡፡ | ፫፻፶፭ |
| ኪዳነ ምሕረት፡፡ | ፫፻፶፯ |
| የአጽዋማት ሰንበታት፡፡ | ፫፻፶፯ |
| መርዓዊ፡፡ | ፫፻፶፱ |
| ዘዘወረደ፡፡ | ፫፻፷ |
| ቅድስት፡፡ | ፫፻፷፩ |
| ምኩራብ፡፡ | ፫፻፷፪ |
| መፃጉዕ፡፡ | ፫፻፷፬ |
| ደብረ ዘይት፡፡ | ፫፻፷፭ |
| ገብር ኄር፡፡ | ፫፻፷፮ |
| ኒቆዲሞስ፡፡ | ፫፻፷፯ |
| ሆሣዕና፡፡ | ፫፻፷፱ |
| ትንሣኤ/ፋሲካ፡፡ | ፬፻፫ |
| የትንሣኤ ፍጹም ደስታና ሐሤት የሚገለጽበት ሥርዓት፡፡ | ፬፻፭ |
| ማዕዶት፡፡ | ፬፻፯ |
| ዳግማዊ ትንሣኤ፡፡ | ፬፻፯ |
| በዓለ ዕርገት፡፡ | ፬፻፱ |
| ርክበ ካህናት፡፡ | ፬፻፲ |

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤

## ማ ው ጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| በዓለ መንፈስ ቅዱስ (በዓለ ሃምሳ) :: | ፬፻፲፩ |
| ዘመነ ክረምት:: | ፬፻፲፬ |
| ጴጥሮስ ወጳውሎስ: ቅዱሳን ሐዋርያት:: | ፬፻፲፭ |
| የአብርሃሙ (የሐምሌ) ሥላሴ:: | ፬፻፲፯ |
| ደብረ ታቦር:: | ፬፻፳ |
| ቡሔ:: | ፬፻፳፩ |
| በዓለ ፍልሰታ ለማርያም:: | ፬፻፳፪ |
| የፍልሰታ በዓል ሰማያዊ ልዕልና:: | ፬፻፳፬ |

ምዕራፍ ፯፤

| | |
| --- | --- |
| መንፈስ - ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ - ቤተ ክህነት:: | ፬፻፳፯ |
| ጊዜያዊ መሰናበቻ:: | ፬፻፳፱ |
| ስለክፍል ሦስት መጽሐፍ መግለጫ:: | ፬፻፳፱ |
| የክፍል ኹለት ጥቅሶችና ማብራሪያዎች:: | ፬፻፴ |


\+ \+ \+

# ምዕራፍ ፩፤

## መ ነ ሻ።

"ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" በሚለው፡ በዚህ አጠቃላይ አርእስት ሥር ተዘጋጅተው ከሚወጡት፡ ሦስት ተከታታይ መጻሕፍት መካከል፡ የመጀመሪያው ክፍል፡ "አንደኛ መጽሐፍ" በሚል፡ ንዑስ ርእስ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ታትሞ ወጥቶ፡ ለሥርጭትና ለንባብ በቅቷል።

ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት፡ ሊገለጹና ሊታወቁ የሚገባቸው ቊም ነገሮች ኹሉ፡ በዚያ መጽሐፍ ምዕራፎች ፩፡ ፪ እና ፫ ውስጥ እንዲካተቱ ስለተደረገ፡ ያ፡ ሰፊ ማብራሪያን የያዘው ጽሑፍ፡ ለዚያ ለአንደኛው፡ ለዚህ፡ ለኹለተኛውና ለሚቀጥለው፡ ለሦስተኛው መጻሕፍት፡ መቅድም፡ መግቢያና መቃረቢያ ኾኖ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ስለኾነ፡ እዚህ ላይ ማካለሉ፡ ወይም፡ ሌላ ተጨማሪ ሐተታ መስጠቱ አላስፈለገም።

የዚህ ውይይት፡ የመጀመሪያ ክፍል የኾነው፡ "'እኔ' የምለው እኔነቴ፡ ማነው?" የሚለው ዓቢይ ርእስ፡ በውስጡም፡ ከእርሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውንና ንዑሳን አርእስት የኾኑትን፡ ከሦስቱ የሕይወት ሥርዓታት፡ ሥነ ፍጥረትን፥ ከሦስቱ፡ የሰውነት አባላት፡ ነፍስን፥ ከሦስቱ መሣሪያ ኀይላት፡ ጾምን፥ ከሦስቱ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሀብታት፡ ኪዳነ ልቦናን እና ከሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ ቤተ ሕዝብን የያዙት፡ ፍጡር፡ ራሱን የሚያውቅባቸውና የሚጠቅምባቸው ምሥጢራት፡ በአንደኛው መጽሐፍ፡ በሚበቃ የተብራሩ መኾናቸው፡ በአንባብያን ዘንድ ይታወቃል።

ይኸው ውይይት፡ በኹለተኛው ክፍል፡ በዚሁ መልኩ እንዲቀጥል፡ ከአዳምና ሔዋን ጋር ተስማምተን፥ ከዚያ ደረጃ ያደረሰንን፡ ቸሩ እግዚአብሔርን ካመሰገንን በኋላ፡ ለሚቀጥለው ቀጠሮአችን እንዲያበቃን ጸልየን፡ በተለመደው አሸኛኘት፡ በፍቅር ተሳስመን፡ ለጊዜው ተለያይተን እንደነበረም ይታወሳል።

ፈጣሪያችን፡ ለዚያ ስምምነታችንና ቀጠሮአችን አብቅቶን፡ እነሆ፡ እንደገና ለመገናኘት ችለናል። በዚህ በኹለተኛው መጽሐፍ ደግሞ፡ የውይይታችን ኹለተኛ ክፍል የኾነውን፡ "'ፈጣሪዬ' የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?" የሚለውን ዓቢይ ርእስ፥ በውስጡም፡ ከእርሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውንና ንዑሳን አርእስት የኾኑትን፡ ከሦስቱ የሕይወት ሥርዓታት፡ ሃይማኖትን፥ ከሦስቱ፡ የሰውነት አባላት፡ መንፈስን፥ ከሦስቱ መሣሪያ ኀይላት፡ ጸሎትን፥ ከሦስቱ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሀብታት፡ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስን እና ከሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ ቤተ ክህነትን የያዙትን፡ ፍጡር፡ ፈጣሪውን የሚያውቅባቸውንና የሚገናኝባቸውን ምሥጢራት፡ በጥልቀትና በምጥቀት ተንትነን በመጠያየቅና በመመላለስ ልንነጋገርበት፡ ይኸው ተዘጋጅተናል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህም ሲያበቃ፡ በዚሁ ይዘት የምናካኺደውንና የመጨረሻው የውይይታችን ሦስተኛ ክፍል የኾነውን፡ ***"'ባልንጀራዬ' የምለው ፍጡር ማነው?"*** የሚለውን ዓቢይ ርእስ፡ በውስጡም፡ ከእርሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን፡ ንዑሳን አርእስት የኾኑትን፡ ከሦስቱ የሕይወት ሥርዓታት፡ ምግባርን፡ ከሦስቱ የሰውነት አባላት፡ ሥጋን፡ ከሦስቱ መሣሪያ ኃይላት፡ ምጽዋትን፡ ከሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ ቤተ ምልክናን እና ከሦስቱ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሀብታት፡ ኪዳነ አሪትን፡ የያዙትን፡ ፍጡር፡ ***"ባልንጀራዬ" የሚለውን ፍጡር*** የሚያውቅባቸውንና የሚያገለግልባቸውን ምሥጢራት፡ በሦስተኛው መጽሐፍ፡ እናከናውናለን፡፡

እንግዲህ፡ ኢትዮጵያዊነታቸውን ለማጽደቅ፡ ቆርጠው ከተነሡት፡ ከጎልማሳው አዳምና ከኮረዳዪቱ ሔዋን ጋር፡ እስከዚህ ያደረስነው ውይይታችን፡ በዚያው፡ በቀደመው መልክ፡ እያንጻንጸቸው፡ በተራ ባቀረቧቸው ጥያቄዎች፡ እኔም በሰጠኋቸው መልሶች፡ የተቀናበረው መጽሐፋዊ ድርሰት፡ እንዲህ ሲል ይጀምራል፡፡

አኹንም፡ ይህን፡ ኹለተኛውን፡ የውይይት ጉዟችንን፡ በዚያው፡ በቆዩበት፡ የቀናና የነቃ መንፈስ ኾነው፡ ከእኛ ጋር፡ አብረውን ይቀጥሉ ዘንድ፡ በኢትዮጵያዊው ትሕትናና ፍቅር፡ እነሆ፡ ጋብዘንዎታል፡፡

## "ኢትዮጵያ"፡ ማናት? "ኢትዮጵያዊነት"ስ ምንድር ነው?

ጥያቄ፡- *ወደኹለተኛው ዋና ውይይታችን ከመግባታችን በፊት፡ በመጀመሪያው ውይይታችን ጊዜ፡ ስለ"ኢትዮጵያ" እና ስለ"ኢትዮጵያዊነት" ገልጸህልን ከነበረው የቁም ነገር ዝርዝር መካከል፡ በተለይ፡ እዚህ ላይ ትዝ ያለንን፡ አንዱን፡ አስቀድመን እናወሳልህ ዘንድ ብትፈቅድልን? ይኸውም፡ ለአንድ አካል፡ የተለያየ ብዙ ስም ሊወጣለት እንደሚችል፡ ያም አካል፡ በማናቸውም ዓይነት ስም ቢጠራ፡ ለምሳሌ፡ እኛ፡ 'አዳም' ወይም 'መልካሙ'፡ 'ሔዋን' ወይም፡ 'ቆንጂት' ብንባል፡ በስሙ እንጂ፡ በእኛ ማንነት ላይ የሚያስከትለው የባሕርይ ለውጥ እንደሌለ ኹሉ፡ "ኢትዮጵያ"፡ ወይም፡ ከዚህ ስም የሠረፀው፡ "ኢትዮጵያዊነት" የሚለው የቃላቱ ምንጭና ትርጉም፡ በ"ኢትዮጵያ" እና በ"ኢትዮጵያዊነት" ባሕርይ ላይ የሚኖረውም ውጤት፡ ከዚህ የተለየ ሊኾን እንደማይችል የሚያረጋግጠው እውነታ ነው፡፡ ይህም ማለት፡ በዚህ ውይይት፡ ትኩረት የተሰጠው፡ የ"ኢትዮጵያ" እና የ"ኢትዮጵያዊነት" ነገር፡ የኹለቱም እውነተኛ የባሕርይ ምንነት፡ ምን እንደኾነ፡ በትክክል የማወቁና የማሳወቁ፡ የመታወቁም ጉዳይ እንጂ፡ የስሙና የቃሉ ትርጉም አለመኾኑን ያስገነዘበን መግለጫህ ነው፡፡*

*በዚያ መሠረት፡ **"'እኔ' የምለው እኔነቴ፡ ማነው?"** የሚለውን፡ የመጀመሪያውን ውይይታችንን ፈጽመን፡ **"ባልንጀራዬ" የምለው ፍጡር ማነው?"** ወደሚለው፡ ወደመጨረሻው ውይይታችን ከመሸጋገራችን በፊት፡ **"'ፈጣሪዬ' የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?"** ወደሚለው፡ ወደመካከለኛው ውይይታችን ርእስ ለመግባት፡ ይኸው፡ ከደጃፉ ላይ ቆመን እንገኛለን፡፡*

# ምዕራፍ ፩፤ መ ነ ሻ::
## "ኢትዮጵያ": ማናት? "ኢትዮጵያዊነት"ስ ምንድር ነው?

*ስለዚህ: ወዳለፍነው የኋለኛውና ወደምንቀጥለው የፊታችን ገሃ ለመነሣት: እንዲህ ቆመን በምንገኝበት አማካይ ቢታ ላይ ሣለን: ስለ"ኢትዮጵያ" እና ስለ"ኢትዮጵያዊነት" እውቀት: ባጭር ቃልም ቢኾን: እንደተለመደው: የምታስጨብጠን መሣሪያና የምታስታጥቀን ኀይል ይኖራልን?*

*መልስ:-* የመጀመሪያውና የመጨረሻው ጉዞአችን መገናኛ በኾነው: በዚህ: በማዕከላዊው መድረክ ላይ ሣለን: አዎን! "ኢትዮጵያ"ን እና "ኢትዮጵያዊነት"ን በሚመለከት: የማስታውሳችሁ: አንድ ቁም ነገር ይኖራል፡ እርሱም: ባጭር ቃል: እኛ ኢትዮጵያውያን: "'ኢትዮጵያ': ድንግል ማርያም ናት: 'ኢትዮጵያዊነት': ኢየሱስ ክርስቶስ ነው!" በምንለው: የእውነትና የእውቀት ትጥቃችን: ምንጊዜም: በመንፈስ በቅታችሁ፡ በአእምሮ ነቅታችሁና በአካል ጉልብታችሁ መገኘት የሚገባችሁ መኾኑን ነው::

በዚህ: የእውነት ኀይልና የእውቀት መሣሪያ በኾነው ትጥቃችን ላይ ስለተመሠረተው: ስለኢትዮጵያ እና ስለኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን: በእያንዳንዳችሁ ውስጥ የሚሰማችሁ: ልዩ ፍቅርና ቅንዓት ካለ: የዚህ መንፈሳዊ ስሜታችሁ: ትክክለኛው ምክንያት: ምን እንደኾነ: መነሻውን: በቀላሉ ታውቁታላችሁ:: ያም መነሻ: እናታችን ኢትዮጵያ የኾነችውን: ቅድስት ድንግል ማርያምንና ፍጹሙ የኢትዮጵያዊነት ሕያው መገለጫ የኾነውን: ልጇን: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን: ኹለቱንም: በአንድነት: እንደእግዚአብሔር ቃል: *"በፍጹም ነፍሳችሁና በፍጹም ልባችሁ: በፍጹም አሳባችሁና በፍጹም ኀይላችሁ"* ስለምትወድዷቸው መኾኑን: ስለእነርሱ ያላችሁ: ይኸው ፍቅራችሁም: በውስጣችሁ: ሃይማኖታዊዉን የቅንዓት እሳት ስለሚያቀጣጥልባችሁ መኾኑን: ኀሊናችሁ በቀጥታ ሲነግራችሁ ታገኙታላችሁ::[፯]

በዚህ አንጻር ደግሞ: በኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያዊነት ላይ ጥላቻ ኖሮአቸው: በእነዚሁ ባሕርያት ላይ በደልንና ጥፋትን ለማድረስ የሚያስቡ: ያገር ተወላጆችም ኾኑ: ባዕዳን ካሉ: ያን የማጥቃት ዓላማቸውን የሚፈጽሙት: በእነማን ላይ መኾኑን አውቀውት: እየራሳቸውን: ከጊዜያዊውና ከምድራዊው፡ ከዘለዓለማዊውና ከሰማያዊው ቅጣት ለማዳን: ዛሬውኑ በንስሓ መመለስ ይኖርባቸዋል::

## በመልካም ሊኖር የቻለውና የሚችለው ማነው?

*ጥያቄ:- "'እኔ' የምለው እኔነቴ: ማነው?" በሚለው: በመጀመሪያው ውይይታችን ጊዜ: ይህንኑ ርእስ በሚመለከት: ስለእየራሳችን ምንነትና ማንነት: በጥልቀትና በምጥቀት እንድንመራመር: ወደእውነተኛው የእግዚአብሔር እውቀትም ለመድረስ የምታስችለንን ጠባቢቱን መንገድ ይዘን እንድንጓዝ ማድረግህ ይታወሳል::*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይህም፡ ለዚያ ላለፍንበትና ለዚህ ላለንበት፡ ወደፊትም ለሚጠብቀን የውይይት ጉዞአችን፡ መነሻ መደብ፡ መንደርደሪያ ሠረገላና መድረሻ ግብ የኾነን፡ የቅዱሱ ኪዳን ነገር ነው፡፡

በዚህ ረገድ፡ ተጨማሪ ማብራሪያን ትሰጠን ዘንድ፡ ልናቀርብልህ የፈለግነው ጥያቄ አለ፡ ይኸውም፡ አንድ ሰብአዊ ፍጡር፡ ይህንኑ፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ ጠብቆና አክብሮ፡ ወይም ሳይጠብቅና ሳያከብር፡ በመልካም ለመኖር ስለመቻሉ፡ ወይም፡ ስላለመቻሉ፡ አጥጋቢ ምላሽ ሊሰጥበት የሚያስፈልገው ጥያቄ ይኾናል፡ ይህም ማለት፡ የቅዱሱ ኪዳን አካላት የኾኑትን፡ "ሰባቱን ቃል ኪዳናት፡ በሃይማኖት የተቀበላቸውና በምግባር ጠብቆ የሚፈጽማቸው ግለሰብም ኾነ ኅብረተሰብ፡ ሕዝብም ኾነ መንግሥት፡ በመልካም ይኖራል!" ሲባል፡ ይህን መልካም አኗኗር፡ የሚያገኘው፡ "በሥጋው ብቻ ነውን? ወይስ፡ በነፍሱ ብቻ? ወይስ፡ በሥጋውም፡ በነፍሱም ጭምር?" ለሚሉት አጠያያቂ ኹኔታዎች፡ በቂ ማብራሪያን መስጠትና ማግኘት ያስፈልጋል ማለት ይኾናል፡፡

ለቅዱሱ ኪዳን ታማኝ ኾኖ የሚገኝ፡ ግለሰብ፡ ወይም፡ ኅብረተሰብ፡ ወይም፡ ሕዝብ፡ ወይም፡ መንግሥት ቢኖር፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ በመልካም ሊኖር የቻለውና የሚችለው፡ ምናልባት፡ ለእኛ፡ እንደሚመስለን፡ በመንፈስ ብቻ እንጂ፡ በሥጋ፡ እውንና ገሃድ ኾኖ የታየበት ጊዜ እንደነበረ፡ የምናስታውሰው ነገር የለንም፡፡ አንተ፡ ስለዚህ ነገር ምን ትላለህ?

መልስ፡- ለዚህ ጥያቄያችሁ፡ መልስ የሚኾነውን የተሟላ ቃል፡ ካለፈው ውይይታችን ብቻ ሳይኾን፡ ከዚህ፡ አኹን ከምንጀምረውና ወደፊት ከምንቀጥለው፡ ከመጨረሻው ውይይቶቻችን ጭምር፡ ተጠቃልሎ ታገኙታላችሁ፡ እስከዚያው ድረስ ግን፡ ለጊዜው፡ በኹለት ተራ ቍጥሮች የተወሰነውን ማብራሪያ፡ እንደሚከተለው እሰጣችኋለሁ፡ ይህንም ሳደርግ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ በህልውናቸውና በኑሮአቸው፡ በሃይማኖታቸውና በአምልኳቸው፡ በምግባራቸውና በሥርዓታቸው ላይ ያላቸው አቋም፡ ከእግዚአብሔር ያገኙት የፈጣሪ ሥራ ስለኾነ፡ ምንጊዜም ቢኾን፡ ጥርጥርና ውልውል፡ ማመንታትና መሸፋፈን የሌለበት፡ የማይናወጽና እንደፀሓይ ብርሃን ግልጽ መኾኑን፡ ለየራሳቸውና ለአምላካቸው፡ ለሌላውም ፍጡር ኹሉ አረጋግጠው ከማሳወቅ የቦዘኑበት ጊዜ አለመኖሩን እያስገነዘብኋችሁ ነው፡፡

ማብራሪያዬም ይኸውላችሁ፡-

፩ኛ. "ቅዱሱን ኪዳን፡ ጠብቆና አክብሮ የሚገኝ ሰው፡ በመልካም ይኖራል!" ማለት እኮ፡ "ያ ግለሰብ፡ ሥጋዊው ሰው በሚመኘው ዓይነትና መጠን፡ ምድራዊ ኑሮው ብቻ፡ ፍጹም ተመቻችቶለት፡ ዓለማዊውን ተድላ ደስታ ያገኛል፡" ማለት አይደለም፡፡

# ምዕራፍ ፩፡ መ ነ ሻ፡፡
## በመልካም ሊኖር የቻለውና የሚችለው ማነው?

"ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ፡ በዚህ ዓለም፡ በመልካም መኖር" ማለት፡ "እግዚአብሔር የሰጠውን፡ ወይም፡ እርሱ የፈቀደለትን፡ ወይም፡ የራሱ ነፍስ፡ ሥጋዊውንና መንፈሳዊውን አስማምታ በማዋሐድ፡ በአግባቡ ፈልጋና መርጣ የተከተለችውን፡ ማናቸውንም ኑሮ፡ በምስጋና ተቀብሎ፡ በፈጣሪው ሥርዓት፡ በደስታ ይኖረዋል፡" ማለት ነው፡፡ይህም፡ በማግኘትም፡ በማጣትም፡ በክብርም፡ በውርደትም፡ በሕመምም፡ በጤናም፡ በኀዘንም፡ በደስታም፡ በመሳሰሉት ኹኔታዎች ጊዜ፡ የሚገጥመውን የሕይወት ዕድል ኹሉ ያጠቃልላል፡፡

ለዚህ እውነታ፡ ሌላውን፡ የራቀውንና የማላውቀውን ትቼ፡ ራሴን ምሳሌ አድርጌ፡ በማስረጃነት እንዳቀርብላችሁ ፍቀዱልኝ! አዎን! "የእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት ጸንቶ ይሠራበት ነበር" ይባል በነበረው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ እኔ፡ ከፍተኛ ኃላፊነት ባለው ሹመት ሳይቀር፡ የዛሬውን አገልግሎቴን እፈጽም ነበረ፡ በደርግ አገዛዝ፡ "በመንግሥታዊ ሥልጣን እሥረኛነት"፡ ወደወህኒ ቤት ገብቼ፡ በዚያ፡ ከሰባት ዓመታት በላይ በቆየሁበት ጊዜም፡ ያንኑ አገልግሎቴን፡ አካኼድ ነበር፡ ከዚያም ተፈትቼ ከወጣሁ በኋላ፡ በግዞትና በስደት ኑሮ ሣለሁም፡ ያን አገልግሎቴን ቀጠልሁት እንጂ፡ አላቋረጥሁትም፡፡

የእኔ፡ ከሥልጣን ተሽሮ፡ ከክብርም ተዋርዶ፡ ኹሉን ማጣት፡ ተይዞም፡ ወደእሥር ቤት መጣል፡ ከዚያም ወጥቶ፡ በግዞትና በስደት መከራ መኖር፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴና በአገልግሎቴ ላይ ያስከተለው ምንም ዓይነት ለውጥ አልነበረም፡ ለእኔ፡ ከእሥራቱ በፊትና በኋላ፡ በግዞትና በስደትም፡ ያሳለፍሁት የኑሮ ኹኔታ፡ ኹሉም፡ "መልካም" ነበር እንጂ፡ በክፋት መልክ ያሳደረብኝ ስሜቱም፡ ትዝታውም እንኳ፡ አልነበረብኝም፡ ምንጊዜም አይኖርብኝምም፡፡

ታዲያ! ይህ ሊኾን እንዴት ቻለ? ሊኾን የቻለው፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ የተነሣ ነው፡፡ በዚሁ ማንነቴ፡ የማገለግላት፡ የእግዚአብሔር እውነትና የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ መልካሚቱ ኢትዮጵያ፡ በማናቸውም ጊዜ፡ ኹኔታና ቦታ፡ ከመልካምነት ባሕርይዋ ስለማትለወጥ፡ በእኔም በአገልጋይዋ ላይ፡ በማናቸውም ጊዜ፡ ኹኔታና ቦታ የሚደርሰውን፡ ማንኛውንም የሕይወት ዕድል፡ በመልካምነት እንድቀበለው ስለምታበቃኝ፡ ያ፡ በሥጋውያን ዘንድ "ክፉ" ተብሎ፡ በክፋት የተፈጸመብኝ የጭካኔ ተግባር፡ ለእኔ "መልካም" ኾኖልኝ፡ በዚያው በመልካም ኹኔታው ጸንቶ ሊቀጥል ችሏል፡፡ ይህን እውነታ፡ እውን አድርጎ ሊያሳየን፡ ራሱ "እውነት" የኾነው እግዚአብሔር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ፡ ከቤዛነቱ ጋር፡ በአርአያነቱ ጭምር ያስተማረን መኾኑ፡ ከቶ፡ ለአፍታም ቢኾን፡ ሊዘነጋ አይገባም፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ታላቁ መጽሐፍ፡ በብሉይ ኪዳኑ መነሻ ላይ፡ እግዚአብሔር፡ በእያንዳንዱ፡ በመለኮታዊ ቀኑ የፈጸመውን፡ የፈጣሪነት ሥራውን የገለጸው፡ "ያ፡ መልካም እንደኾነ አየ!"፡ በሰባቱ የእርሱ ቀኖች የፈጠረውን፡ ፍጥረቱን ባከተተበት፡ በመጨረሻው ቀን ደግሞ፡ "እግዚአብሔርም፡ ያደረገውን ኹሉ አየ፡ እነሆም፡ እጅግ መልካም ነበረ::" በሚል ቃል ሲኾን፡ በሐዲስ ኪዳኑ መዳረሻም ላይ፡ "ነገር ኹሉ፡ ለመልካም እንዲደረግ እናውቃለን፡" ባለው በሐዋርያው መልእክት፡ ይህንኑ የመልካምነትን ምሥጢር አጽንቶታል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "በመንፈስ፡ ደሆች የኾኑ ብፁዓን ናቸው!" ያላቸው እነማን ይመስሉናል? እኒህ እኮ፡ ገንዘቡንና ንብረቱን፡ ሥልጣኑንና ኃይሉን፡ እውቀቱንና ጥበቡንም ይዘውት እያሉ፡ "ይህ ኹሉ፡ ገንዘብና ንብረት፡ ሥልጣንና ኃይል፡ እውቀትና ጥበብ፡ የእግዚአብሔር እንጂ፡ የእኔ አይደለም፡ ከእነዚህ መካከል፡ አንዱን፡ ኹለቱን፡ ወይም፡ ሦስቱንም፡ ለፈለገው የሚሰጠውና የሚነሳው፡ እርሱ ነው፡ ለእኔ እንደሰጠኝ፡ ከእኔ መልሶ ሊወስዳቸውና ለሌላው፡ ላለው ሊጨምርለት፡ ወይም፡ ምንም ለሌለው ሊሰጣቸው ይቻለዋል!" ብለው፡ አደራቸውን በሚገባ ሠርተውበት የሚያስረክቡ ታማኞች አገልጋዮች ናቸው::

እነዚህ ኹሉ ሀብቶች የሌሏቸው ደሆቹም እኮ፡ "እነዚህን ኹሉ ያጣን ምስኪኖች ነን!" ብለው ሳያዝኑ፡ "እግዚአብሔር ቢፈቅድና እኛም፡ በእውነት ብንፈልግ እኮ፡ ለእርሱ የሚሳነው፡ ምንም ነገር ስለሌለ፡ ሊሰጠን ይችላል፡" ብለው በማመን፡ በሥጋዊ ፍላጎት፡ ፍትወትና ምኞት ሳይቃጠሉ፡ ወይም፡ እነዚያን ሀብታት ባገኙት ላይ ስስት፡ ቅንዓትና ምቀኝነት ሳይሰማቸው፡ የድህነት ኑሮአቸውን፡ ያለማማረር፡ በምስጋና ተቀብለው፡ ዕድላቸው ያስገኘላቸውን 'ማናቸውንም ተግባር፡ በቅንነትና በትጋት እየሠሩ፡ በደስታ የሚቀጥሉ ናቸው::

ይህን ኹሉ እውነታ ለማረጋገጥ፡ የሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ተካያጆች (ተዋዋዮች)፡ በዚህ ዓለም ያሳለፉት፡ የሕይወተ ሥጋ አኗኗራቸው ዜና መዋዕል፡ አብነት ኾኖን፡ በማስረጃነት ሊያገለግለን ይበቃል፡ እኒያ ተካያጆች፡ አዳምና ኖኅ፡ መልከ ጼዴቅና አብርሃም፡ ሙሴና ዳዊት፡ ከነቤተሰቦቻቸውና ወገኖቻቸው ጋር፡ በመጨረሻም፡ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በምድራዊው ዕድሚያቸው ያሳለፉትን፡ የፈተናና የመከራ ሕይወት የምናውቀው አይደለምን? ያን የመሰለውን ኑሮአቸውን፡ መልካም አድርገው፡ በምስጋና ከመቀበል በቀር፡ ስለማማረራቸው፡ በዜና መዋዕላቸው የሰማነው፡ አንዳች ነገር ነበርን? የለም:: እነርሱን የመሰሉት፡ ኢትዮጵያውያን አባቶችና እናቶች፡ ቀድሞ እንደነበሩ፡ ዛሬም፡ በብዛት ስላሉ፡ የስንቶቹን፡ ስም ጠቃቅሶ መጨረስ ይቻላል? አይቻልም:: ለመኾኑ፡ ይህ፡ የሥጋ ምቾት ጉዳይ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ከቶ፡ ከቁም ነገር ገብቶ ተቈጥሮ ያውቃልን? እንኳንስ ሊቈጠር፡ ተወስቶም አያውቅም::

# ምዕራፍ ፩፤ መ ነ ሻ።
## በመልካም ሊኖር የቻለውና የሚችለው ማነው?

፪ኛ. ሌሎቹ፡ በማወቅም ኾነ ባለማወቅ፡ በትፋቱም ኾነ በክህደት፡ በማመንታትም ኾነ በዓመፅ፡ በምርጫም ኾነ በግዳጅ፡ በፍላጎትም ኾነ በንቀት፡ በማናቸውም ዓይነት ተቃራኒ መልኩ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የተለዩት ወገኖችና ከቃል ኪዳኑ ውጭ የኾኑት ባዕዳን፡ ሥጋውያኑም ኾኑ መንፈሳውያኑ፡ ኹሉም፡ "እፎይ!" ብለው፡ በሥጋቸው ተመችቷቸው፡ በመልካም የሚኖሩ መስለው የሚታዩት እኮ፡ በዚያ፡ ፈጣሪ፡ ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ፡ ለፍጡሩ በሰጠው፡ የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን ተጠቅመው፡ ያገኙት መኾኑን፡ ልንረሳ አይገባም።

ታዲያ! ያን፡ እነርሱ ያገኙትን፡ ሥጋዊውን የምቾት ኑሮ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ የሚፈልጉትና የሚመኙት ኾኖ፡ የሚያስቀናቸው ይመስላችኋልን? አውቀውና ንቀውት የተዉት ስለኾነ፡ ይጸየፉታል፡ ያዝኑበታል እንጂ፡ ከቶ፡ በሕሊናቸው እንኳ አይመኙትም፡ በዓይናቸውም፡ ዘወር ብለው አያዩትም።

እነዚያ፡ ሥጋውያኑና ዓለማውያኑስ ቢኾኑ፡ ከቶ፡ የፈለጓትን፡ ያችን፡ እውነተኛ ተድላ ደስታ፡ በጊዜያዊነትም እንኳ ቢኾን፡ የሚያገኟት ይመስላችኋልን? አያገኟትምኮ! በንስሓ ካልተመለሱ በቀር፡ መርጠው የያዙትን፡ ያን፡ የምቾት ኑሮአቸውን፡ ዛሬ፡ በሥጋትና በጭንቀት ያሳልፉታል፡ የኋላ ኋላም፡ ለዘለዓለም ይጎዱበታል እንጂ፡ አዎን! አያገኙትም።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸውን፡ በክሕደት፡ በዓመፅና በአመንዝራነት ትተው፡ ማንነታቸውንም ለውጠው፡ ዓለማዊነቱን የመረጡት፡ እኒህ ቅምጥሎች፡ "የመጨረሻው ድህነት" የሚሉትን፡ ማናቸውንም፡ የዚህን ዓለም፡ የሥጋ ፈተናና የመከራ ኑሮ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ "እጅግ መልካም ነው!" ብለው፡ በምስጋናና በደስታ ሲቀበሉት፡ እነሆ፡ ራሳችሁ ትመለከቱታላችሁ። ያን የመሰለውን የሥጋ ፈተናና የመከራ ኑሮ፡ እንዲህ እንዲቀበሉት የሚያደርጋቸውም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው ሲኾን፡ እነርሱም፡ ይህንኑ፡ የቃል ኪዳን ሃይማኖት፡ አምነውበት፡ አክብረውትና ጠብቀውት ሊይዙት የቻሉትኮ፡ በዚያ፡ የመምረጥ ነጻነታቸውና የመወሰን ሥልጣናቸው ስለተጠቀሙ መኾኑንም፡ እንዳትዘነጉት ያስፈልጋል። እኒሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ ያን ፈተናና መከራ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የድል ኃይል ተቋቁመው፡ አኹን በሚገኙበት፡ በምድራዊው ህልውናቸው፡ የመጀመሪያውን የትንሣኤ ሕይወት፡ በብዕልና ታድለው፡ በመንፈስ ይኖሩት ዘንድ፡ ለዚህ ዕድል ያበቃቸው፡ ያ ምርጫቸውና ውሳኔያቸው መኾኑን፡ በሚገባ እንዳስተዋላችሁት አምናለሁ።

ይህ ዓለም፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከየራሱ ክፋት የተነሣ፡ የሚቀይበት ዘመኑ፡ አጭር ኾነበት እንጂ፡ ደግሞም፡ ኃይለኛው የተፈጥሮ ወገኑ፡ መብቱን ወሰነበት እንጂ፡ በፈለገውና በመረጠው መልክ፡ በፍጹም ነጻነት ይኖርበት ዘንድ፡ ከፈጣሪው የተሰጠው ሰፊ ሜዳ መኾኑን፡ ዛሬ፡ እናንተም፡ ልታውቁ ችላችኋል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ከዚህም ጋር፡ ለፈተና በሚደርስበት፡ በተለያዩ መከራዎቹ አማካይነት፡ እየራሱ፡ በሰውነቱ፡ ምን፡ ወይም፡ ማን መኾኑን፡ ለየራሱ፡ ለፈጣሪውና ለሌላው ሰብአዊ ፍጡር፡ አረጋግጦ እያስመሰከረ አልፎ የሚኼድበት፡ ጊዜያዊ የእንግድነት ዳስ እንጂ፡ እንኳንስ፡ መኖሪያው ሊኾነው ይቅርና፡ የቀናት መቆያው ይኾን ዘንድ፡ የሚያስተማምነው ቦታ አለመኾኑ፡ በየራሱና በኹሉም ዘንድ፡ በቀላሉ የታወቀ እውነታ ነው፡ ይህን እውነታ፡ አምኖ ለመቀበል የተቻለው ወገን፡ እምብዛም ባይኾንም፡ በሰው ኹሉ ላይ፡ በየጊዜው በሚደርሰው የሞት ጽዋ፡ እነሆ፡ እየንጻንጹ፡ በየዕለቱ ይመለከተዋል።

የዘመኑ ሰው፡ ቃሉን አምኖ መቀበል አቃተው እንጂ፡ የፍጡር ዕድሜ ሊወስነው በማይቻል መጠን፡ ሲሳዩን፡ በምልዓት አትረፍርፎ፡ ለፍጥረቱ የሰጠው ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህንኑ እውነታ አበክሮና ደጋግሞ አመልክቶናል፡ ይኸውም፡ *"ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፡ ሀበነ የዮም!"* ማለትም፡ *"ለዛሬ ዐውሎ የሚያሳድረንን፡ የየዕለቱን ምግባችንን ስጠን!"* ብላችሁ ጠይቁኝ ባለው፡ በጸሎት ትምህርቱ የሰጠን መመሪያ ነው፡ ይህን ያለው ለምን ይመስለናል? ኹሉን ማድረግ በማይሳነውና የስጦታ ኹሉ ባለቤት በኾነው፡ በእርሱ፡ በባለጸጋው ፈጣሪ ዘንድ እንኳ፡ በዚህ ዓለም እንድንቆይበት የተወሰነችልን ዕድሜ፡ ቢበዛ፡ ከአንዲት ቀን ልታልፍ የማትችል መኾኗን አረጋግጦ ሊያሳውቀን አይደለምን? አዎን! ነው።

የማንነታችን ማረጋገጫ የኾነው የፍርድ ውሳኔ ታውቆ፡ የሚታወጀውም፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ እያለን አይደለም፡ እውነተኛው ዳኛ መጥቶ፡ የዚህን ዓለም ሐሰዊና አስመሳይ ሥርዓት አጋልጦ በሚያፈራርሰውና የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ ዛሬ፡ በገድል የሚኖሩባትን፡ ዘለዓለማዊት የኾነችውን የእርሱን ሥርዓተ መንግሥት፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ በይፋ ገልጦ፡ በገሃድ እንድትሰፍን በሚያደርግበት፡ በመጨረሻው የፍርድ ጊዜ መኾኑ፡ በሚበቃ ተነግሮናል።

ስለዚህ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ እየተፈጸመ ያለው ሃይማኖታዊ ምግባር፡ በዚህ ውይይታችን ላይ፡ በየቦታውና በየመልኩ በተገለጸው መሠረት፡ ራሳቸው፡ እውነተኛውን ሕይወት እየኖሩና ለሌሎች እየጸለዩ፡ ቅዱሱን ኪዳን አለማክበርና አለመጠበቅ ያስከተለውንና ሊያስከትል የሚችለውን ጠንቅ፡ በልዩ ልዩ ምክንያት ለተለዩትና ላላወቁት በማስረዳት፡ የበደሉት፡ ወደዚሁ ቅዱስ ኪዳናቸው በንስሓ ተመልሰው፡ ያላወቁትም በእውቀት ተቀብለውት፡ በአግባብ እንዲኖሩት ማስተማርና መምከር፡ መገሠጽና ማስጠንቀቅ መኾኑን፡ እስካኹን፡ በማስተዋል እንደተመለከታችሁት አምናለሁ።

# ምዕራፍ ፪፡

## ሃይማኖት::

**ጥያቄ፡-** *ካለፈው ውይይታችን የቀረብን፡ ወይም፡ ከዚያ የመነጨ ተጨማሪ ጥያቄ ቢኖረን፡ ያን አጣርተን ለማለፍ ስንል፡ አኹን ለሚጠብቀንም ሰፊ ውይይት፡ መግቢያ ይኾነን ዘንድ፡ ይህን ያህል፡ ጠይቀን፡ መልሶችህን ካገኘን፡ አኹን፡ ወደዋናው የውይይታችን ርእስ እንድናተኵር ፍቀድልን?*

**መልስ፡-** መልካም! እኔም፡ ፍሬ ነገር ያዘለ፡ የተለመደ ጥያቄያችሁን እጠብቃለሁ::

**ጥያቄ፡-** *እንግዲያማ፡ በእኛ በኩል፡ በቅድሚያ፡ "ሃይማኖት ምንድር ነው?" የሚለው ጥያቄ፡ ለዚህ፡ ለኹለተኛው ውይይታችን፡ መሠረትና መነሻ ኾኖ ቢብራራልን እንወድዳለን::*

**መልስ፡-** "ሃይማኖት"፡ በሰብአዊ ፍጡር፡ መንፈሳዊ ልቦና ላይ በተመሠረተ፡ ነፍሳዊ ሕሊናና ሥጋዊ አእምሮ፡ ህልው ኾኖ፡ የሚታወቅና የሚታመን፡ ረቂቅ የአሳብ ውሳኔ ነው:: ባጭር ቃል ሲጠቃለል፡ "ሃይማኖት"፡ ለኢትዮጵያዊው፡-

፩ኛ. የማያልፈውንና የሚያልፈውን፡ ረቂቁንና ግዙፉን፡ የሚታየውንና የማይታየውን፡ ሕያውንና ምውቱን ፍጥረተ ዓለም የፈጠረ፡ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው አንድ አምላክ መኖሩን፡ ከዚያም፡ ራሱ አማኙ ሰው፡ በዚሁ ፈጣሪው መልክ የተፈጠረ መኾኑን ማመን ነው፡

፪ኛ. "በፈጣሪ መልክ ተፈጠረ!" የተሰኘበት ነፍሱ፡ በመጀመሪያ፡ ከሥጋዋ፡ ቀጥላ፡ ከፈጣሪዋ፡ ከዚያም፡ ከተፈጥሮ ወገኗ ጋር፡ በግል የምትጋባው፡ የቃል ኪዳን ግዴታ ኾኖ፡ በእውነተኛ መንፈሳዊ አምልኮ የሚገለጸው በጎ ምግባር ነው፡ ሃይማኖት::

**ጥያቄ፡-** *ያ፡ አንድ አምላክ የኾነው ፈጣሪ፡ ስሙ፡ ማነው?*

**መልስ፡-** በዚህ ውይይት፡ የመጀመሪያ ክፍል እንደተገለጸውና ትርጓሜው እንደተብራራው፡ ያ፡ አንድ አምላክ፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በሃይማኖት ታውቆና በስሙ፡ "እግዚአብሔር" ተብሎ፡ በልዕልናና በክብር፡ በፍቅርና በፍርሃት ይጠራል፡ ይመለካል፡ ይመሰገናል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ጥያቄ፡- *ሃይማኖት ምን እንደኾነ፡ ጠለቅ ብሎ እንዲገባኝ፡ ስለዚህ ምሥጢራዊ ቃል፡ ጥቂት ዘርዘር አድርገህ ብትገልጽልን?*

*መልስ፡-* መልካም፡፡ "ሃይማኖት"፡ ለኢትዮጵያዊው፡ ምን ማለት እንደኾነ፡ እንዲህ በሚል ሓረግ አጠቃልዬ ላቅርብላችሁ! "እኔ ፍጡር ነኝ! የፈጠረኝ አምላኬም፡ 'እግዚአብሔር' ይባላል! የእርሱን፡ ስሙን እየቀደስሁ፡ ክብሩን ወርሼ፡ በዘለዓለም ሕይወት እኖር ዘንድ፡ ጥንቱኑ፡ በራሱ ፈቃድ፡ የእርሱ መልኩና ህላዌው በኾኑትው በረቂቋ የነፍስ አካልና ባሕርይ የፈጠረኝ ነኝ፡ ቀጥሎ፡ የአባቴን የአብርሃ ዘር፡ ከእናቴ የደም አስኳል ጋር በማሕፀን በማዋሓድ፡ ግዙፉን፡ የሥጋን አካልና ባሕርይ አልብሶ፡ እንዲህ፡ በረቂቅነትና በግዙፍነት አከናውኖ የሠራኝ ነኝ፡ በመጨረሻ፡ ራሱ፡ ከድንግል ማርያም፡ ሰው ኾኖ ተወልዶ፡ ከክፉት አግዛዝ፡ ከኃጢአት ቀንበርና ከሞት ፍዳ፡ ነጻ ያወጣኝ ነኝ፡፡

"ይህ ብቻ አይደለም፡ እርሱ፡ የዘለዓለም አባት፡ ቅድስት እናቱም፡ የዘለዓለም እናት ኾነውኝ፡ እኔም፡ የዘለዓለም ልጃቸው ኾኜ፡ በእነርሱ ሕይወትና መንግሥት፡ በዘለዓለም ሕያውነት ነግሼ እኖር ዘንድ፡ በመንፈሳዊው ቅዱስ አካልና ባሕርይ እንደገና የወለደኝ ነኝ፡ በዚህ፤ የእግዚአብሔር ልጅነቴ አካልና ባሕርይ፡ ዛሬ፡ በምድራዊው ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ፡ ኋላም፡ በመንፈሳዊው ዓለም፡ በአዲሱ የትንሣኤ አካል፡ በሕይወተ ነፍስ፡ ለዘለዓለም፡ በተድላ ደስታ የሚያኖረኝ፡ ድንቅ የሥራ ፍሬው ነኝ፡፡

"ከዚህ ጋር፡ ለእኔ ጥቅምና አገልግሎት ይውል ዘንድ፡ ሌላውን ፍጥረት ኹሉ፡ በየወገኑና በየመልኩ ፈጥሮ፡ በሥርዓት የሚመራና የሚያስተዳድር፡ ኹሉን የያዘና ኹሉን የሚችል፡ የኹሉ በላይና የሚሳነው የሌለ፡ ፍጥረቱን ኹሉ አስተካክሎ የሚወድ፡ እያንዳንዱ ፍጡሩ፡ በተፈጥሮ ዓቅሙ፡ የፈለገውን ያደርግ ዘንድ፡ ፍጹም የመምረጥ ነጻነትንና የመወሰን ሥልጣንን የሰጠ፡ እውነተኛ ዳኛ፡ የጠፋውን ፈልጎ ያዳነና የሚያድን፡ ቸርና ደግ፡ ሰላማዊና ርኅሩኅ፡ መሓሪና ይቅር ባይ፡ በመጨረሻ፡ ለኹሉም፡ እንደየሥራው ዋጋውን የሚከፍልና የማያልፍ መንግሥት ያለው፡ አንድ አምላክ አለ!" ብሎ ማመን ነው፡ ሃይማኖት ማለት፡፡

ይህ፡ አንድ አምላክ የፈጠረው፡ የሥነ ፍጥረት ሥራና የእርሱ የኾነው ምሥጢራዊ ነገር ኹሉ፡ በዚህ መልክ የሚታወቅበት ሥርዓተ እውቀት፡ አዎን! "ሃይማኖት" ይባላል፡፡ ይኸው አንድ አምላክ፡ መላእክትን ኾነ ሰውን በፈጠረባቸው ጊዜያት፡ ይህችንም "ሃይማኖት" አብሮ ፈጥሩዋታል፡ ይህም እውነታ፡ መላእክት፡ ከፈጣሪ ባሕርይ በመገኘታቸው፡ ሰውም፡ በእርሱ መልክ በመፈጠሩ ተረጋግጦ ታውቋል፡፡

ፈጣሪ፡ በነቢዩቱ፡ *"ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ፡ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፡"* ብሎ እንደተናገረው፡ የሕይወት ሕግ የኾነችው፡ ይህችው "ሃይማኖት"፡ በተለይ፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በኪዳን ልቦና ተጠብቃ ኖራለች፡፡

ይኸውም: ጥንት: ከፍጥረት መጀመሪያ ጊዜ አንሥቶ: በእነዚሁ ፍጡራን ሰውነት ውስጥ: "ሕሊና" ከተባለው የነፍስ ባሕርይ ጋር ተፈጥራ: በመካከለኛውም ዘመን: በእግዚአብሔር ጣቶች: በድንጋይ ጽላት ላይ: በዓሥሩ ቃላት ተጽፋ: በኪዳን አሪት ተገልጻለች::

## የኪዳን አሪት: ዐሥሩ (ዐሠርቱ) ቃላት::

ከእነዚያ ቃላት መካከል: ከሃይማኖታዊው ምግባር ጋር የተያያዙትን: የኋለኞቹን አምስቱን: ለመጨረሻው ውይይታችን አቆይቼ: ከሃይማኖታዊው አምልኮ ጋር የተያያዙትን: የመጀመሪያዎቹን አምስቱን ብቻ: እንደሚከተለው ልጥቀስላችሁ!

"፩ኛ. *አምላክህ: እኔ: ፈጣሪህ ነኝ!*

"፪ኛ. *ከእኔ በቀር: ሌሎች አማልክት አይኹኑልህ! በላይ: በሰማይ ካለው: በታችም: በምድር ካለው: ከምድርም በታች: በውኃ ካለው ነገር: የማናቸውንም ምሳሌ: የተቀረጸውንም ምስል: ለአንተ አታድርግ! አትስገድላቸው! አታምልካቸውምም! በሚጠሉኝ ዘንድ: እስከሦስተኛና እስከአራተኛ ትውልድ ድረስ: የአባቶችን ኃጢአት: በልጆች ላይ የማመጣ: ለሚወድዱኝና ትእዛዜን ለሚጠብቁ ግን: እስከሺ ትውልድ ድረስ: ምሕረትን የማደርግ: እኔ ፈጣሪህ: ቀናተኛ አምላክ ነኝ::*

"፫ኛ. *ፈጣሪህ: ስሙን በከንቱ የሚጠራውን: ከበደል አይነጻውምና: የአምላክህን ስም: በከንቱ አትጥራ!*

"፬ኛ. *የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ! ስድስት ቀን ሥራ! ተግባርህንም ኹሉ አድርግ! ሰባተኛው ቀን ግን: ለእግዚአብሔር ለአምላክህ: ሰንበት ነው! አንተ: ወንድ ልጅህም: ሴት ልጅህም: ሎሌህም: ገረድህም: ከብትህም: በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ: በእርሱ: ምንም ሥራ አትሥሩ! እግዚአብሔር: በስድስት ቀን: ሰማይንና ምድርን: ባሕርንም: ያለባቸውንም ኹሉ ፈጥሮ: በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና! ስለዚህ: እግዚአብሔር: የሰንበትን ቀን: ባርኮታል: ቀድሶታልም::*

"፭ኛ. *ፈጣሪህ: በሚሰጥህ ምድር: ዕድሜህ እንዲረዝም: አባትህንና እናትህን አክብር!"*

**ጥያቄ:-** *በእግዚአብሔር ጣቶች: በድንጋይ ጽላት ላይ ተጽፈው: ለሙሴ የተሰጡት ትእዛዛት: ዐሥር መኾናቸውን: ቀደም አድርገን አውቀናል: እዚህ ላይ ግን: አምስቱ ብቻ ተለይተው የተከፈሉት ለምንድር ነው?*

**መልስ:-** አዎን! የእግዚአብሔር መንግሥት ሕግጋት: ዐሥሩ ቃላት ሲኾኑ: እነርሱም: የመጀመሪያዎቹ አምስቱ: ነፍስ: ሃይማኖቷን የምትመሠርትባቸውና እውነተኛነቷን: ለራስዋና ለፈጣሪዋ አረጋግጣ የምታሳይባቸው ባሕርያት ናቸው::

የቀሩት፡ የኋለኞቹ አምስቱ ደግሞ፡ ነፍስ፡ በሥጋዋ አማካይነት፡ ሃይማኖታዊ ምግባርዋን፡ ለሌሎቹ ፍጡራን አረጋግጣ የምታሳይባቸው የሥራ መግለጫዎች ናቸው። እነዚህን፡ የኋለኞቹን፡ አምስቱን ቃላት፡ "በመጨረሻው ውይይታችን ጊዜ፡ መነሻ አድርገን እንነጋገርባቸዋለን።" ያልኋችሁን ታስታውሱታላችሁ።

እንግዲህ፡ "ዐሥሩ ቃላት" ከተባሉት፡ መካከል፡ እነዚህ፡ አኹን የዘረዘርሁላችሁ አምስቱ ትእዛዛት፡ "ነፍስ"፡ ረቂቅ ሕሊናዋ በኾነው "ሃይማኖቷ"፡ ለፈጣሪዋ ያላትን ታማኝነትና ፍቅር የምታረጋግጥባቸው እውነታዎች መኾናቸውን በመጠኑም ቢኾን፡ እንደሚከተለው ላብራራላችሁ፦

አንደኛው እውነታ፡ የሰብአዊው ፍጡር ነፍስ፡ "ፍጠረኝ ሳልለው፡ ራሱ፡ ወድዶና ፈቅዶ፡ እኔን፡ በመልኩ ከመፍጠሩና ይህን የሥጋ አካል ከማልበሱ ፍቅር ጀምሮ፡ ለመልካም ሀልውናዬና ሕይወቴ፡ የሚያስፈልገኝን የሥነ ፍጥረት ጸጋ ኹሉ፡ ግዙፉንና ረቂቁን፡ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን፡ አስቀድሞ አዘጋጅቶና አትረፍርፎ እስከመስጠት የሚጨነቅልኝን እግዚአብሔርን፡ በፍጹም ልቤ፡ በፍጹም ነፍሴ፡ በፍጹም አሳቤና በፍጹም ኃይሌ በመውደድ፡ 'ፈጣሪዬ፡ መጋቢዬ፡ ጠባቂዬ፡ አዳኜና አምላኬ' ብዬ፡ የማመልከው፡ እርሱን ብቻ ሊኾን ይገባል!" የምትልበት አምላካዊ ቃል ነው።

ኹለተኛው እውነታ ደግሞ፡ ይኸው ሰብአዊ ፍጡር፡ የራሱን ፍጡርነት፡ የእግዚአብሔርንም ፈጣሪነት አምኖ ከተቀበለ በኋላ፡ እርሱን፡ ፈጣሪውን ብቻ የሚያመልክ ለመኾኑ፡ ፈጣሪውም እርሱን፡ በአምላክነቱ የሚጠብቀው ለመኾኑ፡ ኹለቱም፡ ቃል ኪዳን መጋባታቸውን፡ ምናልባትም፡ በእርሱ፡ በፍጡሩ በኩል፡ ቃል ኪዳኑን በማፍረስ፡ ጥፋት ቢፈጽም እንኳ፡ ከፈጣሪው ዘንድ፡ ይቅርታ እንዲደረግለት ከጠየቀ፡ ምሕረትን እንደሚያገኝ፡ በዚሁ ቃል ኪዳን ውስጥ መተማመኛ መሰጠቱን፡ ዳሩ ግን፡ ፍጡሩ፡ በዚህ መብቱ መጠቀምን ትቶ፡ ጨርሶ ክዶና በምዖ፡ ወደሰይጣን፡ ወደሰውና ወደሌላ ፍጡር፡ ወይም፡ ወደጣዖት፡ ወደገንዘብና ወደሥነ እውቀት፡ ወደሥልጣንና ወደመሳሰሉት ባዕዳን አምልኮዎች፡ በምንም ዓይነት መልኩ ተማርኮ፡ በአመንዝራነት የሚኼድ የኾነ እንደኾነ፡ ቀናተኛነቱን፡ አስቀድሞ በገለጸለት አምላኩ፡ የሚቀጣ መኾኑን፡ የተረዳችው ነፍስ፡ ይህን ግዳጅዋን አክብራ ሳትፈጽም በምትቀርበት ጊዜ፡ የሚደርስባትን ጉዳትና ጥፋት የምታውቅበት አምላካዊ ቃል ነው።

ሦስተኛውም እውነታ፡ ይኸው ሰብአዊ ፍጡር፡ እግዚአብሔርን፡ ስሙን፡ በከንቱ መጥራት ብቻ ሳይኾን፡ የእርሱ፡ የመለኮት የኾኑትን ኹሉ፡ ለራሱና ለሌላ የግል ዓላማው ማስፈጸሚያ እንዲውሉ ማድረግ፤ ወይም፡ ለማድረግ መሞከር፡ አድራጊውን ፍጡር፡ በእግዚአብሔር ላይ ታላቅ በደልን እንደመፈጸም የሚያስቆጥርና ጽኑ ቅጣትን የሚያስከትል ስለኾነ፡ ነፍስ፡ እንዲህ ያለውን አድራጎት፡ መፈጸሙ ቀርቶ፡ ከማሰብ እንኳ እንድትታቀብ የሚያስጠነቅቃት አምላካዊ ቃል ነው።

ይኸውም፡ ግለሰቡ፡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የኾኑትን ካህናት፡ እንዲሁም፡ ምልክቱን፡ ሃይማኖቱንና ሥርዓቱን፡ ንዋያት ቅድሳቱንና መግሪያዎቹን፡ ቦታዎቹንና ቤቶቹን፡ እነዚህን የመሰሉትን ኹሉ፡ በእውነትና ለእውነት ሳይኾን፡ በሓሰትና ለሓሰት፡ ለመልካም ሳይኾን ለክፋት፡ ለልማት ሳይኾን፡ ለጥፋት፡ ለማዳን ሳይኾን ለመግደል፡ ለመጥቀም ሳይኾን ለመጉዳት፡ ይልቁንም፡ በማስመሰል፡ የሚጠቀምባቸው የኾነ እንደኾነ ማለት ነው።

አራተኛው እውነታ፡ ይኸው ሰብአዊ ፍጡር፡ በቃል ኪዳኑ መሠረት፡ ፈጣሪውን፡ በእውነትና በመንፈስ የሚያመልከው መኾኑን፡ ለራሱም፡ ለፈጣሪውና ለሌላው ፍጥረተ-ዓለም የሚያረጋግጠው፡ "የእግዚአብሔር ሰንበት" የተባለችውን፡ የሳምንቱን ሰባተኛና የመጨረሻ ዕለት፡ እርሱን፡ ፈጣሪውንና አምላኩን እግዚአብሔርን ብቻ በማሰብ፡ ስለእርሱ ብቻ በመናገርና እርሱን የሚያስደስተውን በጎ ምግባር ብቻ በማድረግ የሚያሳልፍባት መኾኑን፡ ነፍስ፡ ራስዋን የምታሳውቅበት አምላካዊ ቃል ነው።

አምስተኛውም እውነታ፡ ይኸው ሰብአዊ ፍጡር፡ "ነፍስ አወቀ!" ተብሎ፡ እግዚአብሔር አምላኩን፡ የራሱ አእምሮ ጠባይዕ (የተፈጥሮ ሰብአዊ እውቀት) በሚያስገኝለት "ሃይማኖቱ" አማካይነት እስከሚያውቀውና እስከሚያየው ድረስ፡ የማያየውንና የማያውቀውን ፈጣሪውን፡ እንዲያየውና እንዲያውቀው፡ እንዲወድደውና እንዲታመንበት የሚያደርገው፡ ቀደም ብሎ፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ፡ በሥጋ ከወለዱት አባትና እናት፡ በፍጹም ፍቅር የተለገሠው፡ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ፡ ምስክርና ማስረጃ ሊኾነው እንደሚችል አሳይቶ ለማሳመን፡ ወላጆች፡ በፈጣሪ ደረጃ እንዲወደዱ፡ እንዲከበሩና እንዲፍፈሩ፡ እግዚአብሔር፡ ምሳሌ እንጻደረጋቸው፡ ነፍስ፡ አስቀድማ፡ በመለማመድ ታውቅ ዘንድ፡ የተሰጣት አምላካዊ ቃል ነው።

## መንፈሳዊው ሃይማኖትና ሥጋዊው ሥነ እውቀት።

**ጥያቄ፡-** *ከዚህ ቀደም ብለህ፡ በውይይታችን አርእስት መነሻ ላይ፡ ሃይማኖትን በሚመለከት ስትጀምርልን፡ "ሃይማኖት"፡ በሰብአዊ ፍጡር፡ መንፈሳዊ ልቡና ላይ በተመሠረተ፡ ነፍሳዊ ሕሊናና ሥጋዊ አእምሮ፡ "እኔ ፍጡር ነኝ!" የሚያሰኝ፡ ምሥጢርና ሥርዓተ እውቀት እንደኾነ አድርገህ፡ የሠነዘርኸው አገላለጽ፡ ረቅቆብናልና፡ እስኪ፡ እባክህ በበለጠ አብራራልን?*

**መልስ፡-** ሥጋዊ አእምሮ፡ በሕዋሳት ስለሚታየውና ስለሚዳሰሰው፥ ስለሚሰማውና ስለሚሸተተው፥ ስለሚቀመሰውና ስለመሳሰለው ግዙፍና ረቂቅ ነገር ማሰብ፡ ያሰበውንም በሒሳብ ማስላት፥ ወይም በንግግር፥ በጽሕፈት፥ በሥዕል፥ በቅርጽና በመሳሰለው ዘዴ ስሜቱን ወይም አሳቡን መግለጽ እንጂ፡ መንፈሳዊ የኾነውን ነገር ወይም አሳብ፡ ሊያውቅና ሊረዳ አይቻለውም።

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ሥጋዊ ስለኾነ፡ የማሰብ፥ የማወቅና የመረዳት ኃይሉ፡ እጅግ ቢበዛ፡ ከተራቀቀው፡ ከሥጋዊው ሥነ እውቀት (science) አልፎ እንዲመራመር፡ ዓቅሙ አይፈቅድለትም፡ "ሥጋዊ" የኾነውንም እንኳ ሊያደርግ፡ ዓቅሙ የተወሰነ ነው፡፡

ይህንም እውነታ፡ ዓይን፡ የፀሓይን ቀርቶ፡ ኃይለኛ የኾነ፡ ሰው-ሠራሽ ብርሃንን ለማየት፡ ጆሮም፡ ሊቀበለው ወደሚችል፡ የሞገድ ኃይል መጠን፡ እንዲገዘፍ፡ ተደርጎ ካልተለወጠለት በቀር፡ ረቂቁን ኀዋዊ ድምፅ ሊሰማ፥ እጅም፡ ሊሸከም ከሚገባው ክብደት በላይ ሊያነሣ አለመቻሉን፡ በምሳሌነት በመጥቀስ፡ በቀላሉ መረዳትና ማስረዳት አያዳግትም፡፡

የእግዚአብሔር ነገር ደግሞ፡ "ረቂቅ" የሚባለውን፡ ሥጋዊውን የእውቀት አድማስ ሳይቀር አልፎ፡ ጽንፍ ወደሌለው ወደመንፈሳዊው ህልውና ዘልቆ የሚገባ በመኾኑ፡ ሰብአዊት ነፍስ፡ ማለትም፡ የሰው ነፍስ፡ የእግዚአብሔርን ነገር፡ በመንፈሳዊው ልቦናዋ ካልኾነ በቀር፡ በነፍሳዊው ባሕርይዋ ብቻም እንኳ ቢኾን፡ ልትደርስበት ይከብድባታል፤ በሥጋዊ አእምሮዋማ፡ ፈጽሞ አይቻላትም፡፡ መቼም፡ ስለሰው ነፍሳዊ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ አካላትና ባሕርያት፡ በውይይታችን የመጀመሪያው ክፍል የሰጠኋችሁ ማብራሪያ በቂ ስለኾነ፡ "ነፍሳዊ አስተሳሰብ"፥ "ሥጋዊ አእምሮ" እና "መንፈሳዊ ልቦና" ስል፡ ምን ማለቴ እንደኾነ፡ እናንተም፡ አኹን በደረሳችሁበት የእውቀት ደረጃ፡ በሚበቃ "ተገንዝባችሁታል!" ብዬ አምናለሁ፡፡

እንዲህ፡ በሃይማኖት አውቀን የምንቀበለው እውነታ፡ ምን ዓይነት ከባድና የቱን ያህል ረቂቅ እንደኾነ፡ በዚህ ረገድ፡ ሲነገሩና ሲጻፉ ከኖሩት የመለኮት ዕፁብ ድንቅ ትንግርታዊ ሥራዎች መካከል፡ ዋና ዋናዎቹን ለዓይነትና በምሳሌነት፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ በመጠኑ እጠቃቅስላችኋለሁ:-

- "እግዚአብሔር፡ በቃሉ፡ ይህን ዓለም፡ 'እምኀበ አልቦ፡ ኀበ ቦ'፡ ማለትም፡ 'ካለመኖር ወደመኖር'፥ ወይም፡ 'ከምንምነት፡ ወደምንነት አምጥቶ፡ በርቅቀትና በግዝፈት ፈጠረ፡፡'

- "'ብርሃን ይኹን!' ሲል፡ ብርሃን ኾነ፡፡

- "ሰውን፡ በመልኩ ፈጠረ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ከወንዱ ከአዳም ጎን፡ አንዲት አጥንትን ወስዶ፡ ሔዋንን ሴት አድርጎ ሠራት፡፡

- "ራሱ፡ በአንድነትና በሦስትነት ይኖራል፡፡

- "ያ፡ ፍጥረትን ያስገኘ ቃሉ፡ በተለየ አካሉ፡ ያለወንድ ዘር፡ በድንግል ማሕፀን ተፀንሶ፡ በኀቱም ድንግልና (የድንግልናዋን ማኅተም፡ በንጽሕና አጽንታ ከጠበቀችና ድንግልናዋ፡ ለዘለዓለም ሳይገሠሥ ከምትኖር ልጃገረድ፡ ያለወንድ ዘር) ተወለደ፡፡

- "በቃሉ ብቻ፡ ሕሙማንን ፈወሰ፤ ሙታንን አስነሣ፤ የዕውራንን ዓይኖች፡ በእጁ ዳስሶ አበራ፥ ማዕበል ባናወጸው ባሕር ላይ እየተራመደ ኼዶ፡ ማዕበሉን ጸጥ አደረገው፡፡

# ምዕራፍ ፪፡ ሃይማኖት።

## መንፈሳዊው ሃይማኖትና ሥጋዊው ሥነ እውቀት።

"የመስቀል መከራን ተቀብሎ ከሞተ በኋላ፡ በነፍሱ፡ ወደሲዖል ወርዶ፡ በዚያ ለነበሩት፡ ለተነግሕዩት ምእመናን ነፍሳት፡ የመፈታታቸውን ዜና አበሠረላቸው፡ በሥጋው ደግሞ፡ በተቀበረበት፡ ሳይበሰብስና መቃብሩን፡ "ክፈቱልኝ!" ሳይል፡ በሦስተኛው ቀን፡ ሕያው ኾኖ፡ በኹለንተናው፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፡ በሕይወተ ሥጋ አብረውት የነበሩት ደቀ መዛሙርቱ፡ ወዳሉበት ዝግ ቤት ገብቶ፡ ምሥራቹን፡ በሰላምታ አሰማቸው፡ አብሯቸውም ተመገበ።

"ስለእግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢር፡ አርባ ቀኖች ሙሉ፡ እየገለጸላቸው ከቆየ በኋላ፡ እያዩት፡ ወደሰማይ ዐረገ።

"በመንፈስ ቅዱስ አካሉም ተመልሶ፡ በጸጋው፡ ዓለሙን ኹሉ መላው።

"ከዚህ ጸጋው የተነሣም፡ ሰው፡ በውኃ ጥምቀት፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ሊወለድ የሚቻል ኾነ።

"የስንዴ ኅብስትና የወይን ጭማቂ፡ በቅዳሴ ጸሎት፡ ተለውጦ፡ የመለኮት ሥጋና ደም ይኾናል።

"ሰው ኹሉ፡ ከሰብአዊት ነፍሱ የተነሣ፡ ጨርሶ አይጠፋም፡ በሥጋ አካሉ ምክንያት፡ የሚሞትና በመቃብር የሚበሰብስ ቢኾንም፡ በክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያት፡ የ'እውነት' ወገን ከኾነ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ በመልካሚ ሕይወት፡ መጀመሪያ፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ በመንፈስ፡ በመጨረሻም፡ በሌላ አዲስ አካል፡ ተነሥቶ፡ ለዘለዓለም፡ በሕያውነት፡ የ'ሐሰት' ወገን ከኾነ ደግሞ፡ ለሰይጣንና ለሠራዊቱ በተዘጋጀው በገሃነም ሲሠቃይ ይኖራል!" የሚሉት ናቸው።

እነዚህን እውነታዎች፡ ማንኛውም ሰው፡ በለባዊት ነፍሱ፡ ወይም በሥጋዊ አእምሮው ብቻ፡ እንኳንስ ተረድቶና አውቆ፡ አምኖባቸውም ሊቀበላቸው ይቅርና፡ 'ሊኾን ይችላል!' ብሎ ሊያስበውም፡ ያዳግተዋል። ሥጋዊ በኾነው ሥነ እውቀት ተሰልቶና በምርምር ተረጋግጦ ሊቀርብለት ስለሚያስቸግር፡ የበሰለ አንጐል ያለው ሥጋዊ ምሁርም ቢኾን፡ ሊቀበለው አይቻለውም። ነገር ግን፡ ያው ሰው፡ ይህንኑ ትንግርታዊ ኹኔታ፡ በመንፈሳዊ ልቡናው ተቀብሎ ለማመዛዘንና ለማስተዋል ፍጹም ፍላጎት ካለው፡ በቀላሉ ተረድቶትና አውቆት ሊያምንበት ይቻለዋል። ሥጋዊ አእምሮአቸው፡ በፍልስፍናና በሥነ እውቀት ላይ ተመሥርቶ የተጠናከረው ያፈታውያን (የነጭ) ወገኖች፡ መንፈሳዊውን የእግዚአብሔርን ነገር በቀላሉ ሊቀበሉት የሚከብዳቸው፡ በከንቱ ጥበብና በተግባረ እድ ሙያ ግን፡ እጅግ ተራምደው፡ ይኸው እንደሚታየው፡ የምርት ሀብታቸው፡ በዚሁ አግጣጫ ዳብሮና ተትረፍርፎ፡ ዓለምን እንዳጥለቀለቀው፡ ይኸው፡ በየራሳችሁ ዓይን፡ በገሃድ ትመለከቱታላችሁ።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በሃይማኖተኛነት፡ የእግዚአብሔርን ነገር፡ በመንፈሳዊው ልቦናችን፡ በቀላሉ ተቀብለን የምንኖር በመኾናችን፡ ማለትም፡ የያፌታውያንን ፈለግ ባለመከተል፡ ከሥጋዊው ይልቅ፡ ለመንፈሳዊው የእግዚአብሔር ነገር፡ ቅድሚያንና ብልጫን ሰጥተን፡ በመንፈሳዊው እምነትና ሥርዓት የምንኖር ከመኾናችን የተነሣ፡ በሥጋውያኑ ዘንድ፡ እንደድሆች ተቆጥረንና በዚያ ፈርጅ ተመድበን እንደምንገኝ ታውቃላችሁ፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የኾነው ቅዱስ ጳውሎስ፡ *"ለፍጥረታዊ ሰው"፡ ማለትም፡ ለሥጋዊ ሰው፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር፡ሞኝነት ነውና፡ አይቀበለውም፡ በመንፈሳዊ ልቦናም የሚመረመር ስለኾነ፡ ሊያውቀው አይችልም፡፡ "መንፈሳዊ ሰው ግን፡"* በመንፈሳዊ ልቦናው፡ *"ኹሉን ይመረምራል፡ ራሱ ግን፡ በማንም አይመረመርም፡፡"* ያለው ይህንኑ ለማመልከት ስለኾነ፡ ለእናንተም፡ የተፈነጠቀላችሁን፡ ይህን የሃይማኖት ጮራ ለመቀበል፡ ፍጹሙ ፍላጎት ካላችሁ፡ በዚህ፡ የወጣኒነት (የጀማሪነት) ደረጃም[፲፩] ቢኾን፡ ምላሹን አግኝታችሁ፡ እውነቱን ልትገነዘቡት ትችላላችሁ፡፡

*ጥያቄ:- ስለዚህ የሃይማኖት ጉዳይ ለማወቅ በሞከርን መጠን፡ እየረቀቀብን ስለሚኼድ፡ እስኪ ሳትሰለች፡ የዚህኑ፡ ምሥጢር የኾነብንን ነገር፡ መልክና ሥርዓት ባለው መንገድ፡ አኹንም፡ ዘርዝረህና አስፋፍተህ አስረዳን?*

መልስ:- "እግዚአብሔር" የምንለው ፈጣሪያችንና አምላካችን፡ ማን እንደኾነ፡ በውይይታችን ቀዳማዊ ክፍል፡ ግዙፍ በኾነው፡ በሥጋዊው መንገድ፡ በመጠኑ ተብራርቶላችሁ እንደነበረ ታስታውሱታላችሁ፡፡ ነገር ግን፡ አኹን፡ በዚች አፍታ ደግሞ፡ ምንጊዜም፡ ከእያንዳንዳችን፡ ለአንዲት ቅጽበት እንኳ ሳይለየን፡ አብሮን የሚኖር መኾኑን፡ ለእየራሳችን ላረጋግጥላችሁ የምችልበት፡ ግልጽና ቀላል፡ ቀጥተኛም መንገድ አለ፡ ይኸውም፡ "እግዚአብሔር ማን እና/ወይም ምን እንደኾነ ለማወቅ፡ እርሱንም ለማየትና ተገናኝቶ ለማነጋገር፡ ወደአንድ፡ ቅርብ ወይም ሩቅ ቦታ መኼድ፥ እዚያም፡ የመግቢያ ፈቃድ መጠየቅ፡ ወይም፡ የሚያገናኝ ሰው መሻት የሚያስፈልገው ሳይኾን፡ እዚያው፡ እውስጣችን፡ በየልቦናችን ይገኛል፤" የሚል ነው፡፡ እግዚአብሔር፡ በዚያ ቦታ ስሙ፡ "ሕሊና" ይባላል፡፡

ሐዋርያት፡ *"ራሱን፡ ያለምስክር አልተወም!"* ሲሉ፡ ሥነ ፍጥረትን በመጥቀስ የተናገሩለትና ለእኛም፡ በአንድነትና በሦስትነት ተገልጾልን፡ በመንፈሳዊው አእምሮአችን ያወቅነው እግዚአብሔር አምላክ፡ ማንነቱንና ምንነቱን፡ በሥጋውያኑ ሕዋሳታችን፡ በግዘፍ በምናያቸው ፍጡራን አካላት በበለጠ እንድንገነዘብ አድርጎናል፡፡

ለዚህም ማስረጃ፡ ከፍጡራኑ አካላት መካከል፡ ወደፊት፡ ለምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን፡ እንደ ማብራሪያ ኾና፡ በምሳሌነት የምትቀርበውን ፀሓይን፡ ልንወስድ እንችላለን፡፡ ሥጋዊ ፍጡር፡ የፀሓይን አካል፡ በሌጣ ዓይኑ ትክ ብሎ ሊያይ፥ ሙቀቷንም፡ ከመጠን በላይ ሊቋቋም አለመቻሉ፡ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

# ምዕራፍ ፪፡ ሃይማኖት፡፡
## መንፈሳዊው ሃይማኖትና ሥጋዊው ሥነ እውቀት፡፡

---

ይልቁንም፡ ግዙፍ አካል ያለው መስሎ የሚታየውን፡ የሰማዩን የጠፈር ኀዋ፡ ለአያሌ ዘመናት፡ ቢበርሩት ቢበርሩት፡ የማይደረስበት መኾኑ፡ በዓለማውያኑ ጥበበኞች ሥራ መረጋገጡን፡ እነሆ እንመለከታለን፡፡

ይህ እውነታ፡ በሥጋዊው ሕዋሳታችን ብቻ፡ የእግዚአብሔርን መልክ ለማየትና ባሕርዩንም መርምረን ልንደርስበት የማይቻለን መኾኑን በቀላሉ እንድንረዳው ያደርገናል፡፡

ምናልባትም፡ ስለእግዚአብሔር ማንነትና ምንነት፡ በራሳችን ልናውቅ የምንችልበት፡ ሌላ ቀላል መንገድ ደግሞ አለን፡ ይህም መንገድ፡ ፈጣሪ፡ ለእያንዳንዳችን ያደረገልን በጎ ሥራዎቹ ኹሉ፡ ልክ፡ አንድ፡ ገንዘብ የተረፈው፡ ባለጸጋ አባት፡ ለሚወድደው ልጁ፡ አስቦ ያደረገለትን፡ ወይም፡ ልጁ፡ በልቡ ተመኝቶት የፈጸመለትን፡ የአባትነት ቸርነት የሚመስል ነው፡" ብለን በማሰብ ይኾናል፡፡

ያ አባት፡ ለልጁ ያደረገው ቸርነት ምንድር ነው? "በልምላሜ የተዋበችና በሀብት የከበረች፡ በሥልጣኔ የተራመደችና በልማት የደረጀች፡ አንዲት መልካም አገርን፡ እስከሚበቃህ ድረስ ጎብኝተህ ተመለስ!" ብሎ፡ ማናቸውንም አስፈላጊ ወጪ ኹሉ፡ በቅድሚያ አትረፍርፎ ከፍሎለት፡ ልጁን፡ ወደዚያች አገር መስደዱ ነው፡፡

እንደዚሁ ኹሉ፡ "ዓለሙን፡ አስቀድሞ፡ እንዲህ ከውናና አዘጋጅቶ፡ እኔንም፡ 'ፍጠረኝ!' ሳልለው፡ በመልኩ ፈጥሮኝ፡ ካለመኖር፡ ወደመኖር ያመጣኝ፡ እኔ፡ 'እግዚአብሔር' የምለው፡ እርሱ ግን፡ 'የሰማዩ አባታችን፡ ብሉኝ!' ያለው ፈጣሪ፡ ለእኔ ያደረገልኝ፡ ማለትም፡ ወደእርሱ፡ እንደገና እንደምመለስ አውቄ፡ በሥጋ፡ ወደዚች ምድር ልኮኝ፡ ራሴን፡ በዚህ ዓለም ያገኘሁት፡ በዚያ መልክ ነው!" ብዬ ማመኑ፡ የእግዚአብሔርን ማንነትና[፲፪] ምንነት፡ በሚበቃ አያስረዳኝምን? አዎን! በእርግጥ ያስረዳኛል፡፡

## ስለሦስቱ የሃይማኖት ጸሎቶቻችን፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የማስረዳችሁ ደግሞ፡ ይህንኑ፡ "እግዚአብሔር" የምንለውን ፈጣሪያችንንና አምላካችንን፡ በበለጠና በተሟላ ይዞታ እንድታውቁት የሚያደርጋችሁን፡ "ሃይማኖት" የተባለውን ሥርዓተ እውቀት የሚያሳያችሁን፡ መንፈሳዊውን መንገድ ነው፡ ይህን፡ "ሃይማኖት" የተባለውን ሥርዓተ እውቀት፡ ከነፍሳዊው አስተሳሰባችሁና ከሥጋዊው አእምሮአችሁ አልፋችሁ፡ በመንፈሳዊው ልቦናችሁ ተቀብላችሁ፡ በምግባር ልትፈጽሙት የሚገባችሁ ይኾናል፡፡

ይህ ጥልቅና ሰፊ እውቀት፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ፡ በየዕለቱ ሲገለጽ የኖረባቸው፡ ሦስት የሃይማኖት ጸሎቶች አሉን፡፡ እነዚህም፡- ፩ኛ፡ "የኢትዮጵያውያን"፡ ፪ኛ፡ "የሐዋርያት"፡ ፫ኛ፡ "የሠለስቱ ምዕት" የሚባሉት ናቸው፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ጥያቄ:- *ታዲያ! እነዚህ የሃይማኖት ጸሎቶች፡ ምንና ምን እንደኾኑ፡ ዘርዝረህና ተንትነህ፡ አፍታትተህም ብትገልጽልን!?*

መልስ:- መልካም! በመጀመሪያ፡ ሦስቱን ጸሎቶች፡ በየአርእስታቸውና በየኹለንተናቸው፡ ለይታችሁ ታውቋቸው ዘንድ፡ እንደሚከተለው አቅርቤላችኋለሁ፡ በ፩ኛው የሃይማኖት ጸሎት ውስጥ ብቻ የሚገኙት፡ በሌሎቹ፡ ኹለት ተከታታይ የሃይማኖት ጸሎታት ውስጥ ግን የሌሉት ቃላት፡ እንዲህ፡ *ቀለስ* እና ጎላ ብለው፡ ተሰምሮባቸዋልና በማስተዋል ተመልከቷቸው!

፩ኛ፡ "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት።"

"*እኛ ኢትዮጵያውያን፡* ኹሉን በያዘ፡ ሰማይንና ምድርን፡ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

"ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፡ አንድ የአብ ልጅ፡ አንድ ጌታ በሚኾን፡ *በእግዚአብሔር ወልድም* እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፡ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፡ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል፡ ኹሉ በእርሱ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፡ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፡ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ *ከሥጋዋ ሥጋ፥ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡* ፍጹም ሰው ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዓረገ። በአባቱም ቀኝ፡ *በዙፋኑ* ተቀመጠ። *ዳግመኛም፡* በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም።

"*በእግዚአብሔር* መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፡ ከአብ የሠረፀና በነቢያት አድሮ የተናገረው፡ *በሐዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው።* ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፡ እናመሰግነዋለንም።

"*ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡* በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።

"ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

"የሙታንን መነሣት፥ የሚመጣውንም ሕይወት፡ ተስፋ እናደርጋለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።"

## ምዕራፍ ፱፡ ሃይማኖት።
## ስለሦስቱ የሃይማኖት ጸሎቶቻችን።

### ፩ኛ፡ "የሐዋርያት የሃይማኖት ጸሎት።"

"የጌታችንና የአምላካችን፡ የመድኃኒታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በሚኾን፡ ፍጥረቱን ኹሉ በፈጠረ፡ በአንድ አምላክ እናምናለን። በባሕርዩ፡ ምክንያት የለበትምና፡ አስቀድመን እንደተናገርን፡ በዘመኑ ኹሉ ይኖራል እንጂ፡ ጥንት ወይም ፍጻሜ የለውምና። የማይጠፋ ብርሃን አለው፡ ወደእርሱም መቅረብ የሚቻለው የለም።

"ኹለተኛ፡ አይደለም፡ ሦስተኛም፡ አይደለም፡ አይጨመርበትም፡ ብቻውን፡ ለዘለዓለም የሚኖር፡ አንድ ነው እንጂ። የማይታወቅ፡ የተሠወረ አይደለም፡ ኹሉን የያዘና ከፍጥረቱም ኹሉ በላይ የሠለጠነ መኾኑን፡ በኦሪትና በነቢያት፡ ፈጽመን አወቅነው እንጂ። ዓለም ሳይፈጠር፡ አንድ ልጁና የተካከለው ኾኖ፡ ከእርሱ የተወለደው፡ ሠራዊትንና ሚመታትን፡ ሥልጣናትንም ኹሉ የፈጠረው፡ የአምላካችንና የመድኃኒታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፡ እግዚአብሔር አብ፡ አንድ ነው።

"በኋለኛው ዘመን፡ ሰው ይኾን ዘንድ የወደደ፡ ያለወንድ ዘር፡ ቅድስት ከምትኾን፡ ከድንግል ማርያም፡ ሥጋን ነሣ፡ ያለኃጢአትና ያለበደል፡ እንደሰው አደገ፡ በእንደበቱም፡ ሐሰት የለበትም። ከዚህ በኋላ፡ በሥጋ ታመመ። ሞተም። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። ወደላከውም፡ ወደአብ፡ ወደሰማይ ዓረገ። ኃይል ባለውም ቀኝ ተቀመጠ።

"ከአብና ከወልድ ጋር ህልው የሚኾን፡ ከአብ የሠረፀ፡ ዓለምን ኹሉ ያጻነ፡ አጽናኝ መንፈስ ቅዱስን ሰደደልን።

"እንግዴህ፡ የእግዚአብሔር ፍጥረት ኹሉ፡ በጎ እንደኾነ፡ የሚጣልም እንደሌለበት እንናገራለን።

"የሥጋ ሕይወት የምትኾን፡ ነፍስም፡ በኹለንተናዋ፡ ንጽሕትና ቅድስት ናት። እኛስ፡ ጋብቻ፡ ንጹሕ እንደኾነ፡ ልደትም፡ ርኵሰት እንደሌለበት እንናገራለን፡ ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮአቸዋልና። እንግዴህ፡ ከሥጋ ጋር የማትሞትና የማትበሰብስ ነፍስ፡ በሥጋችን፡ እንዳለች እናስተውል!

"እኛስ፡ የሃይማኖት ለዋጮችን፡ ሥራቸውንም ኹሉ፡ መለየታቸውንም ኹሉ፡ ሕግን፡ መለወጣቸውንም፡ እንጸየፋለን፡ እነርሱ፡ በእኛ ዘንድ የረከሱ ናቸውና።

"ዳግመኛም፡ የሞቱ፡ የጻድቃንና የኃጥአን ትንሣኤ እንዳለ እናምናለን። ኹሉ፡ እንደየሥራው፡ ፍዳውን የሚቀበልበት፡ የፍርድ ቀንም እንዳለ እናምናለን።

"ዳግመኛ፡ ክርስቶስ፡ ሰው ከመኾኑ የተነሣ፡ ምንም ምን፡ ሕፀፅ (ጉድለት) እንደሌለበት እናምናለን። እርሱ፡ በእውነት፡ ሰው የኾነው፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ፡ ለአብ፡ ሊቀ ካህናቱ ኾኖ፡ የሰውን ባሕርይ፡ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"እንግዲህ፡ እንደአይሁድ አንገዘር! እርሱ፡ ኦሪትንና ነቢያትን፡ ሊፈጽማቸው እንደመጣ እናውቃለን፡፡

"አሕዛብ ኹሉ፡ የእርሱን መምጣት፡ ተስፋ የሚያደርጉት ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከይሁዳ፥ ከዕሤይም ሥር የተገኘው፥ ሥልጣኑም፡ በትከሻው ላይ የኾነው ነው፡፡ ለእርሱ፡ ምስጋና፥ ክብርና ገናንነት፥ ቡራኬና ውዳሴ፥ ማኅሌትም ይገባል፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡"[፲፬]

### ፫ኛ: "የሠለስቱ ምዕት የሃይማኖት ጸሎት፡፡"

"ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን፡፡

"ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋር በነበረ፥ አንድ የአብ ልጅ በሚኾን፡ በአንድ ጌታ፡ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን፡፡ እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ በእርሱ የኾነ፥ በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፥ ያለእርሱ ምንም ምን የኾነ የለም፡፡

ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ፍጹም ሰው ኾነ፡፡ ሰው ኾኖ፡ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ፡፡ ተሰቀለ፡፡ ሞተ፡፡ ተቀበረ፡፡ በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ፡፡ በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዓረገ፡፡ በአባቱም ቀኝ፡ ተቀመጠ፡፡

"ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል፡፡ ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም፡፡

"በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፤ እርሱም፡ ጌታ፥ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከአብ የሠረፀና በነቢያት አድሮ የተናገረ፡፡ ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም፡፡

"ከኹሉ በላይ በምትኾን፡ ሐዋርያት በሰበሰቧት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡

"ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን፡፡

"የሙታንን መነሣት፥ የሚመጣውንም ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡"[፲፭]

እንግዲህ፡ ለሰው፡ የህልውናው መሠረትና የሕይወቱ ዋስትና የኾነውን፡ "ሃይማኖት"ን፡ አብዛኛው የዘመኑ ትውልድ፡ ሲያደርግ እንደሚታየው፡ እናንተ፡ በማቃለል የምትመለከቱት ሳይኾን፡ ቀዳሚ ቁምነገር አድርጋችሁ፡ በቍርጥ ልትከታተሉት የተነሣችሁ መኾናችሁን ስለተገነዘብሁ፡ የእነዚህን የሃይማኖት ጸሎታት ሐተታ፡ እያከታተልሁ አቀርብላችኋለሁ፡፡

እናንተ፡ ምናልባት፡ አዘውትራችሁ፡ ወደቤተ ክርስቲያን እየኼዳችሁ የማታስቀድሱ ከኾናችሁ፡ ስለእነዚህ ሦስት የሃይማኖት ጸሎቶች መኖርና ስለአቀራረባቸው መለያየት፡ ልታውቁ አይቻላችሁ ይኾናል፡፡

# ምዕራፍ ፪፡ ሃይማኖት።
## ስለሦስቱ የሃይማኖት ጸሎቶቻችን።

ይልቁንም፡ ቀደም ብዬ፡ በ፩ኛና በ፫ኛ ተራ ቍጥሮች ያሰማኋችሁን የሃይማኖት ጸሎቶች፡ ኢትዮጵያውያን ምእመናንና ምእመናት፡ ለረዥም ዘመን፡ እንዲማርዋቸውና እንዲጸልዩዋቸው፥ በሥርዓተ ቅዳሴያችንም ጊዜ፡ በያግባቡ እንዲያዜሟቸው ሲደረግ፡ በ፩ኛው ተራ ቍጥር፡ አኹን፡ እናንተ ለሰማችሁትና የራሳችን ለኾነው፡ "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት" ግን፡ ይህ ዕድል ተነፍጎትና ምንም ዓይነት ቦታ ሳይሰጠው፡ እስከዛሬ ተጥሎ እንደኖረ፡ ሳታውቁም ትችላላችሁ።

*ጥያቄ፡- እኛ፡ ወደቤተ ክርስቲያን መኼድ ባይቻለን፡ በዚህ፡ በእየራሳችን ድክመት ምክንያት፡ እውቀቱን ብናጣ አያስደንቅም፤ ነገር ግን፡ የኢትዮጵያውያን ለኾነው፡ "የሃይማኖት ጸሎት"፡ እንደቀሩት፡ ጸሎቶች፡ ለምን፡ እስከዛሬ፡ ይህ ዕድል ተነፍጎትና ምንም ዓይነት ቦታ ሳይሰጠው፡ ተጥሎ እንደኖረ፥ ዛሬስ፡ ይኸው ጸሎት፡ በአንደኛነት ተራ ገብቶ፡ እንዴት፡ ሊጸለይበትና ሊቀደስበት እንደቻለ ብትገልጽልን?*

**መልስ፡-** ***"ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!"*** በሚለው መጽሐፌ ውስጥ በሰፊው እንዳተትሁት፡ ግብፃውያን ጳጳሳት፡ የሃይማኖት መሪዎቻችን ኾነው በቆዩበት ረዥም ዘመን፡ የኢትዮጵያ የኾነው ኹሉ እንዲጠፋና በዚያ ምትክ፡ የእነርሱ የኾነው እንዲተከል፥ የእነርሱ የበላይነትና የኢትዮጵያውያን ጥገኝነት እንዲረጋገጥ፡ ታላቅ ምሥጢራዊ ዘመቻ የተካኼደበት ስለነበረ፡ ማንነታችንና ምንነታችን ተለይቶ የሚታወቅበት፡ ይህ የሃይማኖታችን ጸሎት፡ በይፋ ተገልጾና ተጽፎ፡ ሕፃናት እንዳይማሩት፥ ሕዝቡም፡ በግልም ኾነ በኅብረት እንዳይጸልየው ማድረግ፡ ለጠላቶቻችን፡ ቀላሉ ዘዴ ኾኖ ኖረ።

ይኹን እንጂ፡ በዚያ የፈተና ዘመን ውስጥ፡ ኢትዮጵያውያን፡ *"እንግዴህ ወዲህ፡ ሕጌን፡ በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይኾን፡ በልባቸው እጽፈዋለሁ፤ በልቦናቸውም አኖረዋለሁ፤ ካሁን በኋላም፡ ሰው፡ ሰውን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፤ እኔው ራሴ አስተምራቸዋለሁ።"* ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች፡ በሰጠው ቃል ኪዳኑ መሠረት፡ ያን፡ የቅዱሱን ኪዳን፡ የሃይማኖት ጸሎታቸውን፡ በሰውነታቸውና በሕይወታቸው፡ ሕያው አድርገውት፡ ፈጣሪያቸውን፡ በእውነትና በመንፈስ እያመለኩበት፡ እስከዚህ ዘመን ቆይተው፡ እነሆ፡ ዛሬ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነትና በእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤት፡ እንዲህ፡ በጽሑፍ ገልጸው፡ በይፋ ሊያወጡት በቅተዋል።

እዚህ ላይ፡ እናንተንና እናንተን የመሰሉ፡ የዚህ፡ የዛሬው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ አባሎች ያልተረዳችሁት፥ ወይም ግልጽ ያልሆነላችሁ መሠረታዊ የኾነ፡ አንድ ቁም ነገር መኖሩን፥ ይኸው ቁም ነገር፡ ገብቷቸውና ግልጽ ሆኖላቸው፡ ነገር ግን፡ ሊቀበሉት የማይፈልጉ ወገኖች እንዳሉም ልገልጽላችሁ እወድዳለሁ።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ቁም ነገሩም፡ የዚህ፡ የዛሬው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ አባሎች የኾንነው፡ ናንተና የእናንተ መሰሎች፡ የእኔም ተልእኮ፡ ምን እንደሆነ፡ በእኛና እኛን መሰሎች ዘንድ ሳይቀር፡ በትክክል የመታወቁ ወይም ያለመታወቁ ጉዳይ ነው:: እስካሁን ባስተዋልኩትና በተገነዘብሁት መጠን ግን፡ ትውልዱ፡ በጠቅላላ፡ ተልእኮውን፡ በበጎ ጎኑ፡ ያወቀውና የተረዳው አልመሰለኝም::

ስለዚህ፡ ለእናንተና እናንተን ለመሰሉት፡ የዛሬው ትውልድ አባሎች ለኾናችሁት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፡ "ሊታወቁት ይገባችኋል!" ብዬ፡ ላሳስባችሁ የምፈልገው ቁም ነገር አለ:: ይህም፡ *"አሁንና እንግዴህ ወዲህ፡ የእናንተና የእናንተ መሰሎች፡ የእኔም ተልእኮ፡ ዲያብሎስና ባዕዳን፥ እንዲሁም፡ የወገን ጠላቶች የኾኑት ተባባሪዎቻቸው፡ በረቂቅ ጥበባቸውና ምሥጢራዊ ኃይላቸው፡ ሽፋፍነውና አሥረው፡ ሲጨቁኗትና ሲያንገላቷት የኖረችውን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የሆነችውን ኢትዮጵያን፡ ይህን በመሰለ ሰይጣናዊ ደባ፡ በሥውር ከሚካኼድባት ጥቃት ለማዳንና ከዚህ ከምትገኝበት የሃይማኖት እሥራትና ጭቆና በማስፈታት፡ እውነተኛ ማንነቷን ገሃድ ማውጣት ነው::"* በሚል አጭር ቃል ይጠቃለላል፡-

የትውልዱ ተልእኮ፡ ይህ እንዲኾን ያስገደደው ዓቢይ ምክንያት፡፡ በዘመናችን፡ በእየራሳችን፡ በአገራችንና በወገናችን ላይ እየወረደ ያለው፡ ታላቁ መከራ መኾኑን፡ እናንተና እናንተን የመሰሉት ኹሉ፡ አበክራችሁና አጠንክራችሁ መገንዘብ አለባችሁ:: ይህንም፡ የትውልዱን ተልእኮ፡ በሥራ ላይ አውሎ፡ ለፍሬ ለማብቃት በቅድሚያ ያስፈለገው ተግባር፡ የኢትዮጵያን እውነተኛ ማንነትና ሃይማኖታዊ አቋም፡ በትክክል መግለጽ ኾኖ ተገኘ! ስለዚህ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ሲያያዝ የመጣውና እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በኢትዮጵያውያን ልቦና ላይ ጽፎ ያኖረው፡ ይህ፡ "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት"፡ ከእርሱም ጋር፡ መሠረታዊዉንና መደበኛውን ዘር ሳይለቁ፡ "የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን ጸሎት"፡ "ኢትዮጵያውያን፡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የምስጋና ጸሎት" እና ኢትዮጵያውያን ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት የሰላምታ ጸሎት" የተባሉት ጸሎቶች፡ እነሆ፡ ጊዜው ሲደርስ፡ አምላክ ኢትዮጵያ፡ በጽሑፍ ጭምር እንዲዘጋጁና በይፋ እንዲታወቁ አደረገ::

እነዚህ ጸሎቶች፡ በአምላካዊው ዕቅድና እጅ ተመሥርቶ፡ ተገድግዶና ተደምድሞ በተሠራው፡ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ በእናንተና በእኔ ጭምር፡ የሰውነት ሕንፃ ውስጥ፡ ሕያዋን ኾነው፡ በልብ፡ በቃልና በእስትንፋስ፡ ሲነበቡ፡ ሲጸለዩ የኖሩትና የሚኖሩት ናቸው፡ እነርሱንም፡ ዛሬ፡ ራሱን፡ ለ"እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት" የሚያበቃው፡ ማናቸውም ሰው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም መንበር ፊት፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ፡ ቆሞና ሰግዶ፡ በይፋ በሚሰጠው "የምስክርነት ቃል" ያረጋግጣቸዋል::

# ምዕራፍ ፪፤ ሃይማኖት::
## ስለሦስቱ የሃይማኖት ጸሎቶቻችን::

*ጥያቄ:- ኢትዮጵያውያን: የሃይማኖት ጸሎታቸውና የቀሩት ጸሎቶቻቸው: ከሌሎቹ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጸሎቶች ተለይተው: "የኢትዮጵያውያን" ሊባሉና ሊኾኑ የተገባው: ለምን እንደኾነ ብታስረዳን? በዚህ መልክ መቅረባቸውስ: እስካኹን እየተሠራባቸው ያሉትን ጸሎቶች: በማሻሻል: ወይም በመለወጥ የቀረቡ ናቸው ሊያሰኝ ይቻላል ወይ?*

*መልስ:-* ኢትዮጵያውያን: የሃይማኖት ጸሎታቸውና የቀሩት ጸሎቶቻቸው: ከሌሎቹ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጸሎቶች: የተለዩ ሊኾኑ የተገባው: በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተው ነፃ ህልውናቸው: ከኹሉ የቀደመ በመኾኑ ነው:: ይህን የእግዚአብሔር እውነት: አሌ ሊል የሚችል ማንም የለም:: ይህ: የኢትዮጵያ ህልውና: የእግዚአብሔር ሥራ ስለኾነ: ይህን መለኮታዊ እውነት መቃወም: ራሱን እግዚአብሔርን መቃወም: ሥራውንም ለማፍረስ መሞከር ይኾናል::

የቀደመው ነገር: ወይም ሥራ: በኋለኛው: ይሻሻላል: ወይም: ይለወጣል እንጂ: የኋለኛው: በቀደመው: ሊሻሻል: ወይም: ሊለወጥ አይቻልም:: ሃይማኖትም: ቀዳሚ ስለኾነ: ሊሻሻል: ወይም: ሊለወጥ: ከቶ አይቻልም:: "ኢትዮጵያዊ" የኾነው ኹሉ ደግሞ: ቀዳሚ መኾኑ ተረጋግጧል:: ስለዚህ: ይህን: የቀደመውን: "ኢትዮጵያዊዉን ሃይማኖት" ሊያሻሽሉና ሊለውጡ የሞከሩ: እነርሱ: ሌሎቹ: የዓለም አብያተ ክርስቲያናትና የሃይማኖት ድርጅቶች ናቸው ማለት ነው:: ያ የቀደመው: "ኢትዮጵያዊው ሃይማኖት" ደግሞ: በእግዚአብሔር መንፈስ: በሰዎች ልቦና ላይ ስለተጻፈ: ሊሻሻል: ወይም: ሊለወጥ አልተቻለም::

ዛሬ: የተደረገ አዲስ ነገር: ወይም: የተሠራ አዲስ ሥራ ቢኖር: ያ: እግዚአብሔር: እንደቃል ኪዳኑ: በኢትዮጵያውያን ልብ ላይ ጽፎት፥ በልቦናቸውም ውስጥ አሳድሮት: እነርሱም: በሕይወት እየኖሩትና በቃል እየተናገሩት፥ ለልጅ ልጆቻቸውም በቃል እያስተላለፉት የቆየው የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት: ጊዜው ሲደርስና አስፈላጊ ኾኖ ሲገኝ: *በጽሑፍ ሠፍሮና ተዘጋጅቶ መቅረቡ* ብቻ ነው::

ዙሪያውን: በዱር አራዊት ተከብቦ፥ በመካከሉም: በተሓዋስያን የእባብ ዝርያዎች ተመልቶ እንደሚጨነቅ የእንስሳት መንጋ: በባዕዳን ጠላቶቹና በወገን ባላጋራዎቹ: በሥጋዊውም ኾነ: በመንፈሳዊው አግጣጫ: ሲሠቃይ የሚታየው: ዛሬ: እናንተና እኔ የምንገኝበት: ይህ: ኢትዮጵያዊ ትውልድ: እየወረደበት ያለው ፈተናና መከራ: ካለፉት ኹሉ ይልቅ: የባሰ የረቀቀና የጠለቀ፥ የበዛም ኾኖ: እነሆ ይታያል፤ ይኹን እንጂ: ይህ ዓይነቱ ፈተናና መከራ: ከእኛ ቀደም ባሉት: ኢትዮጵያውያን ትውልዶችም ላይ: በየዘመናቱ ሲደርስ የኖረ ለመኾኑ: እዚህ ላይ: አንዱን፥ የቅርቡን: ለማስረጃነት አቀርብላችኋለሁ፤ ይህም: ከአራት መቶ ዓመታት በፊት የኾነውን: የአጼ ገላውዴዎስን ዜና መዋዕል የሚያስታውሰው ዝክረ ነገር ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ያ ጊዜ፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ በዘመኑ በነበረው ኢትዮጵያዊ ትውልድ ላይ፡ ከውስጥ፡ በአንድ ወገን፡ መንፈሳዊው ጦርነት፡ በአምልኮ ባዕድና በዲያብሎስ አገልጋዮች በኾኑ የክፋት ሠራዊት፡ በምሥጢር ሰፍኖ ይካኼድበት የነበረ ሲኾን፡ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ሥጋዊው ጦርነት፡ በአሕመድ ግራኝ ሠይፍና በአረማውያን ተከታዮቹ ጦር፡ በይፋ እየተመመ፡ አገሪቱንና ሕዝቡን ያጥለቀለቀበት ዘመን ነበር። ይኼ መራራ ጽዋ አልበቃ ብሎ፡ አገሪቱና ሕዝቡ፡ በዚያ የተደራረበ መቅሠፍት መዳከማቸውን ተመልክተው፡ ከውጭ፡ ባዕዳኑ፡ አጋጣሚውን በመጠቀም፡ በአንድ በኩል፡ የዘመኑ ኃያል የነበረው፡ የቱርክ መንግሥት፡ የግዛት ድንበሩን ለማስፋፋት፡ በኢትዮጵያ ላይ፡ ሥጋዊ ጦርነትን ያወጀበት፡ በሌላው በኩል ደግሞ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ የሃይማኖት መረቧን፡ በኢትዮጵያ ላይ ለመዘርጋት ቆርጣ ተነሥታ፡ ሠራዊቷን ያሰማራችበት ወቅት ነበር።

ታዲያ፡ እነዚያ፡ የኢትዮጵያ የዘር ጠላቶች፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ በዚያን ሰዓትም፡ ያን በመሰለ፡ በተባበረና በተቀነባበረ፡ በተቀናጀም መልክ፡ እርሷንና ትውልዷን፡ ጨርሰው፡ ከምድር ገጽ ለመደምሰስ፡ በየፊናቸውና በሙሉ ኃይላቸው፡ ብርቱ እንቅስቃሴ አድርገው፡ በአራቱም ማዕዘን ተረባርበው፣ በወደቁባት ጊዜ፡ ኢትዮጵያ፡ በልጆቿ ተጋዳይነት፡ እነዚያን፡ ረቂቃንና ግዙፋን ወራሪዎቿን ተቋቁማና አሸንፋ፡ በድል አድራጊነት፡ ገድሏን እንድትፈጽም፡ ከዚያ ረቂቅና ግዙፍ አጣብቂኝና ወጥመድ ነበልባልና ማዕበልም ተርፋ፡ በህልውናዋ እንድትቀጥል ያስቻላት፡ ምን ይመስላችኋል?

በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን፡ "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት"።

*ጥያቄ፡-* *ኢትዮጵያን፡ ከነልጆቿ፡ በነጻነት ህልውናዋ፡ እንዲህ እንድትቀጥል ያስቻላት፡ ያ ታላቅና የማይበገር ተአምራዊ ኃይል፡ ከቶ ምን እንደኾነ ለማወቅ፡ ያጓጓልና፡ እስኪ፡ ፈጥነህ ንገረን?*

መልስ፡- የዚያን ጊዜዎቹ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን፡ መሪዎቻችንና አዋቆቻችን፡ ለዚያ ለነበሩበትና ያን ለመሰለው፡ እጅግ አሳዛኝና ተስፋ አስቈራጭ ኹኔታ፡ ጽኑ ትጥቅና ፍቱን መሣሪያ ኾኗቸው የተጋደሉበት ኃይል፡ አዎን! ያው፡ ከቀደሙት ትውልዶቻቸው የተረከቡት፡ ይኸው፡ ዛሬ፡ እኛም ልጆቻቸው፡ የምንጋደልለት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሃይማኖታችን ነው።

ያም ሃይማኖት፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ በ፲፱፻፵፬ ዓ.ም. በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን የተዘጋጀው፡ "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት"፡ እንደጥሩ መስታዋትና እንደማጉያ መነጽር፡ ቍልጭ አድርጎ ያሳየናል።

# ምዕራፍ ፪፤ ሃይማኖት።
## በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን: "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት"።

እርሱም: ልክ: እኛ: የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን: አሁን ላለንበት: ተመሳሳይ ወይም የከፋ ኹኔታ: ጽኑ ትጥቅና ፍቱን መግሪያ ይኾነን ዘንድ: እየተመራንበትና እየተጠቀምንበት እንዳለው: እንደዛሬው "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት" እና "የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን ጸሎት" እንደሚለው የጸሎታችን ዓይነት ማለት ነው።

እነዚህም ጸሎቶቻችን: እነሆ: በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን ከነበሩት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሲያያዝ በደረሰን: በዚያው: በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን ላይ ተመሥርተው የተዘጋጁት ናቸው።

*ጥያቄ:-      እንዴ! በዚያን: በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን: የእርሱንና በዘመኑ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ሃይማኖት የሚገልጽ: የተለየ: የሃይማኖት ጸሎት ነበር ማለት ነው? ካለማ: ኧረ እስኪ እባክህ ግለጽልንና እንወቀው?*

መልስ:-      መልካም! ዋናው የተዘጋጀው: በግእዝ ስለነበረ: እርሱን አስቀድምላችሁና: ትርጉሙን: አስከትልላችኋለሁ። ስሙት!

*"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ።*

*"ዝንቱ ውእቱ ሃይማኖትየ ወሃይማኖተ አበውየ ነገሥታት እሥራኤላውያን፤ ወሃይማኖተ መርዔትየ: እለ ሀለዉ በዐፀደ መንግሥትየ።*

*"ንሕነ [ኢትዮጵያውያን] ነአምን በአሐዱ አምላክ፥ ወበወልዱ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ውእቱ ቃሉ፥ ወውእቱ ኃይሉ፤ ውእቱ ምክሩ፡ ወውእቱ ጥበቡ፥ ዘሀለወ ምስሌሁ: እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። ወበደኃሪ መዋዕል: መጽአ ኀቤነ: እንዘ ኢየአርቅ እመንበረ መለኮቱ። ወተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ: ወእማርያም እምቅድስት ድንግል። ወተጠምቀ በዮርዳኖስ: በ፴ ክረምት። ወኮነ ብእሴ ፍጹመ፤ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል: በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፤ ሐመ፤ ወሞተ፤ ወተቀብረ፤ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት። ወእምዝ: በ፵ ዕለት: ዓርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት፤ ወነበረ በየማነ አቡሁ። ወካዕበ ይመጽእ በስብሐት፥ ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ። ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ፥ እግዚእ ማኅየዊ፥ ዘሠረፀ እምአብ። ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት: ለሥርየተ ኃጢኣት። ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን፥ ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለም፤ አሜን።*

*"ንሕነሰ ነሐውር በፍኖተ ንጉሥ ጽዮን፤ ወኢ ናጸንን: ኢ ለየማን፡ ወኢ ለፀጋም: እምትምህርተ አበዊነ ፲ወ፪ ሐዋርያት፤ ወጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ፡ ወ፸ወ፪ አርድእት፤ ወ፫፻፲ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት: ዘተጋብኡ በኒቅያ፤ ፻ወ፶ በቍስጥንጥንያ፤ ወ፪፻ በኤፌሶን።*

*"ከመዝ ወከመዝ እሜህር: አነ ገላውዴዎስ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ፤ ወስመ መንግሥትየ: አጽናፍ ሰገድ፥ ወልደ ወናግ ሰገድ፥ ወልደ ናዖድ።*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"ወበእንተ ምክንያተ አክብሮትነ ዕለተ ቀዳሚት ሰንበት፡ አኮ ዘናከብራ ከመ አይሁድ፡ እለ ሰቀልዎ ለክርስቶስ፡ እንዘ ይብሉ፡ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ፤ እስመ እሙንቱሰ አይሁድ፡ ኢይቀድሑ ማየ፤ ወኢያነድዱ እሳተ፤ ወኢያበስሉ ጸብኀ፤ ወኢየሐብዙ ኅብስተ፤ ወኢይትፈለሱ እምቤት ውስተ ቤት።

"ወባሕቱ፡ ንሕነሰ፡ ናከብራ፡ እንዘ ነዓርግ ባቲ ቍርባነ፤ ወንገብር ባቲ ምሳሐ፡ በከመ አዘዙነ አበዊነ ሐዋርያት በዲድስቅልያ። አኮ ዘናከብራ ከመ ሰንበተ አይሁድ፡ እንተ ይእቲ ዕለተ ሐዳስ፡ ዘይቤ ዳዊት በእንቲአሃ፡ 'ዛቲ ዕለት፡ እንተ ገብረ እግዚአብሔር፡ ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ።'

"እስመ ባቲ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወባቲ ወረደ መንፈስ ቅዱስ፡ ላዕለ ሐዋርያት፡ በጽርሐ ጽዮን፡ ወባቲ ተሰብአ ውስተ ከርሠ ቅድስት ማርያም፡ ድንግል በኵሉ ጊዜ። ወባቲ ይመጽእ ዳግመ፡ ለዕሤተ ጻድቃን፡ ወለፍዳ ኃጥአን።

"ወበእንተ ሥርዓተ ግዝረትኒ፡ አኮ ዘንትገዘር ከመ አይሁድ፡ እስመ ንሕነ ነአምር ቃለ ምህሮሁ ለጳውሎስ፡ ፈልፈለ ጥበብ፡ ዘይቤ፡ 'ተገዝሮኒ ኢይበቍዕ፥ ወኢተገዝሮኒ ኢያሠልጥ፥ ዘእንበለ ዳእሙ፡ ሐዲስ ፍጥረት፥ ዘውእቱ አሚን፡ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።' ወካዕበ ይቤ፡ ለሰብአ ቆሮንቶስ፡ 'ዘሂ ነሥአ ግዝረተ፡ ኢይንሣእ ቍልፈተ።' ኵሉ መጽሐፈ ትምህርት ለጳውሎስ፡ ሀለወ ኀቤነ፤ ወይሜህረነ፡ በእንተ ግዝረት፥ ወበእንተ ቍልፈት። ወባሕቱ፡ ግዝረትሰ፡ ዘኮነ በኀቤነ፡ በልማደ ሀገር፥ ከመ ብጕንተ ገጽ፡ ዘኢትዮጵያ ወኖባ፤ ወከመ ስቍረተ እዝን ዘሰብአ ሕንድ፥ ዘንተሰ ዘንገብር፡ አኮ በዐቂበ ሕገ ኦሪት፥ ዳእሙ፡ በልማደ ሰብእ።

"ወበእንተ በሊዐ ሐራውያን፡ አኮ ዘንትከላእ፡ በዓቂበ ሕገ ኦሪት፡ ከመ አይሁድ፤ ለዘኒ በልዓ፡ ኢናስቈርሮ፥ ወኢናረኵሶ፤ ወለዘኒ ኢበልዓ፡ ከመ ይብላዕ ኢናከብሮ፤ በከመ ጸሐፈ አቡነ ጳውሎስ ለብሔረ ሮሜ፡ እንዘ ይብል፡ 'ዘኒ በልዓ፡ ኢይመንኖ ለዘኢይበልዕ፤ ወለኵሎሙ እግዚአብሔር ተወክፎሙ። መንግሥተ እግዚአብሔር፡ ኢኮነት፡ በመብልዕ ወበመስቴ፤ ኵሉ ንጹሕ፡ ለንጹሓን፤ ወእኩይሰ ለሰብእ፡ በሊዐ ምስለ ዕቅፍት።' ወማቴዎስ ወንጌላዊ ይቤ፡ 'አልቦ ዘይክል አርኵሶቶ ለሰብእ፡ ዘእንበለ ዘይወፅእ እምአፉሁ፤ ወዘሰ ውስተ ከርሥ፡ ይበውእ፤ ወይትገመር ጽመ፤ ወይትገደፍ፤ ወይትከዓው፤ ወያነጽሕ ኵሎ መባልዕት፤ ወበብሂለ ዝንቱ ቃሉ፡ ነሠተ ኵሎ ሕንፃ ስሕተቶሙ ለአይሁድ፡ እለ ተምህሩ እመጽሐፈ ኦሪት።

"ሊተሰ፡ ሃይማኖትየ ወሃይማኖተ ካህናት ማእምራን፡ እለ ይሜህሩ በትእዛዝየ፡ በዐፀደ መንግሥትየ፤ ወኢይትገኀሡ እምፍኖተ ወንጌል፥ ወእምትምህርተ አቡነ ጳውሎስ፡ ኢ ለየማን፥ ወኢ ለፀጋም። ወበመጽሐፈ ታሪክኒ፡ ጽሑፍ ሀሎ፡ በመጽሐፈ ዚአነ፤ እስመ ቆስጠንጢኖስ ንጉሥ፡ አዘዘ፡ በመዋዕለ መንግሥቱ፡ ለኵሎሙ እለ ተጠምቁ አይሁድ፡ ከመ ያብልዕዎሙ ሥጋ ሐራውያ፡ በዕለተ ትንሣኤሁ፡ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

## ምዕራፍ ፱፡ ሃይማኖት።

## በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን፡ "የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት"።

---

*"ወባሕቱ፡ በከመ አደሞ ልቡ ለሰብእ ይትሔረም እምበሊዓ ሥጋ እንስሳ፡ ዘይፈቅር ሥጋ ዓሣ፡ ወቦ፡ ዘይፈቅር በሊዓ ሥጋ ዶርሆ፡ ወቦ፡ ዘይትሔረም እምበሊዓ ሥጋ በግዕ፡ ወኵሉ፡ ዘከመ አደመ ልቡ ይተሉ። ከመዝ ውእቱ ሥምረቱ ወፈቃዱ ለሰብእ፡ በእንተ መብልዓ ሥጋ እንስሳ፡ አልቦ ሕግ፡ ወአልቦ ቀኖና፡ ውስተ መጽሐፈ ሐዲስ፡ ኵሉ ንጹሕ፡ ለንጹሓን። ወጳውሎስኒ ይቤ፡ 'ዘሰ የአምን፡ ኵሎ ለይብላዕ።'*

*"ዘንተ ኵሉ ዘጸሐፍኩ፡ ለጸሐፍኩ፡ ከመ ታእምር፡ ጽድቀ ሃይማኖትየ።*

*"ተጽሕፈ በ፲ወ፫፻ በ፶ወ፩ ዓመት፡ እምልደተ እግዚእነ ኢየሱስ*[፲፯]

*ክርስቶስ አመ ፳ወ፫ ለሰኔ፡ በሀገረ ዳሞት።"*

ትርጉሙ (በእኔ)

"በአብና በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስም ስም፡ አንድ አምላክ።

"የእኔ ሃይማኖት፡ የእሥራኤላውያን ነገሥታት አባቶቼም ሃይማኖት፡ በመንግሥቴ ክልል ያለው የመንጋዬም (የሕዝቤም) ሃይማኖት ይህ ነው።

"እኛ፡ (ኢትዮጵያውያን) በአንዱ አምላክ እናምናለን። በአንድ ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን፡ እርሱ፡ ቃሉ ነው፡ ኃይሉም ነው፤ ምክሩ ነው፡ ጥበቡም ነው። ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋር የነበረው፡ በኋለኛው ዘመን፡ ከመንበረ መለኮቱ ሳይለይ፡ ወደእኛ መጣ። ከመንፈስ ቅዱስና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ኾነ። በሠላሳ ዓመቱ፡ በዮርዳኖስ ተጠመቀ፤ ፍጹም ሰውም ኾነ፡ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመንም፡ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ፡ ተሠቃየ፡ ሞተ፡ ተቀበረ፡ በሦስተኛውም ቀን፡ ተነሣ። ከዚህም በኋላ፡ በአርባኛው ቀን፡ በምስጋና ወደሰማይት ዓረገ፡ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ። በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድም፡ እንደገና በምስጋና ይመጣል፡ ለመንግሥቱ መጨረሻ የለውም። በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፡ እርሱም፡ ጌታ፡ ሕይወትን የሚሰጥ፡ ከአብ የሠረፀ ነው። ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን። የሙታንን መነሣት፡ የሚመጣውንም የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን፡ አሜን።

"እኛም፡ በጽዮን ንጉሥ መንገድ እንኼዳለን፤ ከአባቶቻችን፡ ከዓሥራ ኹለቱ ሐዋርያት፡ ከጥበቡም ምንጭ፡ ከጳውሎስ፥ ከሰባ ኹለቱም ረዳቶች፡ ሃይማኖታቸው ከቀናው፡ በኒቅያ ከተሰበሰቡት፡ ከሦስት መቶ ዓሥራ ስምንቱ፡ በቍስጥንጥንያ ከተሰበሰቡትም፡ ከመቶ ዐምሣው፥ በኤፌሶን ከተሰበሰቡትም፡ ከኹለት መቶው ሊቃውንት ትምህርት፡ ወደቀኝም፡ ወደግራም አናዘነብልም።

"የናዖድ ልጅ ወናግ ሰገድ የወለደኝ፡ ስመ መንግሥቴ፡ 'አጽናፍ ሰገድ' የኾነ፡ እኔ ገላውዴዎስ፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ፡ እንዲህና እንዲህ አስተምራለሁ።

"ስለመጀመሪያዋ ዕለተ ሰንበት፡ ስለቅዳሜ፡ ያለን አክብሮት፡ ምክንያቱ፡ *'ደሙ፡ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይኹን!'* ብለው ክርስቶስን እንደሰቀሉት፡ እንደአይሁድ ሥርዓት፡ የምናከብራት አይደለም፡ እነርሱ አይሁድማ፡ በቅዳሜ ቀን፡ ውኃ አይቀዱም፡ እሳት አያነድዱም፡[፲፰] ወጥ አይቀቅሉም፡ እንጀራ አይጋግሩም፡ ከቤት ወደቤትም አይዘዋወሩም።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"እኛ ግን፡ የምናከብራት፡ አባቶቻችን ሓዋርያት፡ በዲድስቅልያ፡ እንዳዘዙን፡ በዕለተ ቀኗ፡ በጧት ቀድሰን፡ የቁርባኑን መሥዋዕት በማሳረግና በመቀበል፡ ከዚያም ወጥተን፡ ጠበል ጠዲቁን በመሳተፍ ነው:: አዲሲቱ ዕለት በመኾኗ፡ ዳዊት ስለእርሷ፡ *'እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፡ በእርሷም፡ ደስ ይበለን! ሓሤትንም እናድርግ!'* ብሎ እንደዘመረላት፡ እንደሰንበተ እሑድ የምናከብራት አይደለም:: በእርሷ (በሰንበተ እሑድ)፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሥቶባታልና፡ በእርሷ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በጽርሓ ጽዮን፡ በሓዋርያት ላይ ወርዶባታልና፡ በእርሷ፡ ምንጊዜም ድንግል በኾነችው፡ ቅድስት ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ ሰው ኾኗልና፡ ለጻድቃን፡ ዋጋቸውን፡ ለኃጥአንም፡ ፍዳቸውን ሊከፍል፡ በእርሷ፡ ዳግመኛ ይመጣባታልና::

"ስለግዝረት ሥርዓትም፡ እንደአይሁድ የምንገዘር አይደለንም፡ የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ፡ *'በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን፡ አዲስ ፍጥረት መኾን እንጂ፡ መገዘር ቢኾን፡ አይጠቅምም፡ አለመገረዝም ቢኾን፡ አይሠለጥንም፡'* ሲል ያስተማረውን ቃል እናውቃለንና:: ዳግመኛም፡ ለቆሮንቶስ ሰዎች፡ *'ማንም፡ ግዝረትን የተቀበለ ቢኖር፡ ወደቈላፍንት አይመለስ!'* ብሏል:: የጳውሎስ፡ የትምህርቱ መጽሓፍ፡ በእኛ ዘንድ ስላለ፡ ስለግዝረትና ስለቈላፍንት ያስተማረውን ኹሉ እናውቀዋለን:: ነገር ግን፡ እኛ የምንፈጽመው ግዝረት፡ በኢትዮጵያና በኖባ የሚኖሩ ሰዎች፡ ፊታቸውን እንደሚበጡት፡ የሕንድ ሰዎችም፡ ጆሮአቸውን እንደሚበሱት ዓይነት፡ የአገር ባህል ኾኖ፡ በሰው ልማድ እንጂ፡ ሕገ ኦሪትን ለመጠበቅ ብለን የምናደርገው አይደለም::

"ከአሳማ ሥጋ መብልም የተከለከልነው፡ እንደአይሁድ ሥርዓት፡ የኦሪቱን ሕግ ለመጠበቅ ብለን አይደለም:: አባታችን ጳውሎስ፡ *'የሚበላ፡ የማይበላውን አይናቀው! እግዚአብሔር፡ ኹሉንም ተቀብሎአቸዋል፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መብልና መጠጥ አይደለችም:: ለንጹሖች፡ ኹሉ፡ ንጹሕ ነው፡ በመጠራጠር ከተበላ ግን፡ ለዚያ ሰው፡ ክፉ ነው፡'* ሲል፡ ለሮሚ ሰዎች እንደጻፈው፡ 'ማንም ቢበላ፡ ረክሷል!' ብለን አናገልለውም፡ የማይበላውንም፡ እንዲበላ አድርገን፡ አናከብረውም:: ወንጌላዊው ማቴዎስም፡ *'ሰውን፡ ከአፉ ከሚወጣው በቀር፡ ሊያረክሰው የሚችል የለም፡ ወደሆድ የሚገባው ግን፡ መብሉ ኹሉ፡ በዚያ ተማርቶና በዝግታ አልፎ፡ ወደእዳሪ ይጣላል፡ ይፈስሳልም፡'* ብሏል:: በዚህ ኃይለ ቃሉ፡ አይሁድ፡ ከመጽሓፈ ኦሪት ተምረነዋል ብለው ያቆሙትን የስሕተት ሕንፃ ኹሉ አፈራርሶባቸዋል::

"ለእኔ ያለኝ ሃይማኖቴ፡ ከወንጌል መንገድና ከአባታችን ጳውሎስ ትምህርት፡ ወደቀኝም፡ ወደግራም ሳያዘነብሉ፡ በመንግሥቴ ክልል ውስጥ፡ በትእዛዜ ሥር የሚያስተምሩ የአዋቂዎች ካህናትም ሃይማኖት ይህ ነው:: በታሪክ መጽሓፍ፡ በተለይም፡ በእኛ መጽሓፍ፡ 'ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ፡ በዘመነ መንግሥቱ፡ የተጠመቁትን አይሁድ፡ ኹላቸውን፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ዕለት፡ የአሳማ ሥጋ እንዲያበሏቸው ማዘዙን የሚናገር ጽሑፍ አለ::

# ምዕራፍ ፬፤ ሃይማኖት።
## በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን፡ “የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት”።

---

ትእዛዙ ግን፡ የእያንዳንዱ ሰው ልቦና እንዳሰኘው፡ እንዳማረው እንዲኾን፥ የእንስሳ ሥጋ ከመብላት የተከለከለ አለ፡ የዓሣ ሥጋ የሚወድድ አለ፡ የዶሮ ሥጋ መብላት የሚወድድ አለ፡ የበግ ሥጋ ከመብላት የተከለከለ አለና፡ ለሰዉ ኹሉ በሚያቀርቡት፡ ልቦናው ያሰኘውንና ያማረውን እንዲከተሉ በሚል ነው። ስለእንስሳ ሥጋ መብል፡ የሰው ፍላጎቱና ፈቃዱ፡ እንደዚህ ስለኾነ፡ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ፡ ሕግም አልተሠራ፡ ሥርዓትም የለም፡ ለንጹሓን፡ ኹሉ ንጹሕ ነው፡ ጳውሎስም፡ *'ማንም፡ የሚያምን ቢኾን፡ ኹሉን ይብላ!'* ብሏል።[፰]

"በጽሑፍ ለቀረበው *የንቀፌታ ክርክር*፡ በጽሑፍ የተሰጠው ይህ ኹሉ *የምላሽ ቃል የተጻፈው፡ የሃይማኖቱን እውነተኛነት ታውቁ ዘንድ ነው።*

"ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ፡ በ፲፭፻፶፭ኛው ዓመት፡ ሰኔ ፳፫ ቀን፡ በዳሞት አገር ተጻፈ።"

## ስለአ(ኸ)በገደ ፊደላችንና ስለመዓዛ ቅዳሴያችን።

*ጥያቄ፡- ታዲያ፡ ይህን መሳይ የቅርብ ጊዜ ሕያው የታሪክ ድርጊት እያለ፡ እንዴት፡ ይህን የመሰለው በደል፡ ለዚህን ያህል ዘመን ሲቀጥል ቆይቶ፡ በአሁኑ ዘመን፡ በዚህ ትውልድ ላይ እንደገና ሊከሠት ቻለ? እንዴትስ፡ የእኛ ሊቃውንት፡ ይህን እውነታ ሳይገልጹት እስከዛሬ ዝም አሉ?*

*መልስ፡-* እናንተ! ይህ ነው የሚደንቃችሁ? “ኢትዮጵያውያን፡ ከራሳቸው ወገኖች መካከል፡ ጳጳሳት እንዳይመርጡ፡ እንኳንስ መምረጥ፡ ግብፃዊዉን እንኳ፡ በእጩነት ለማቅረብ፡ የተካፋይነት መብት እንዳይኖራቸው፡ በኒቅያ ጉባዔ ተወስኗል፡” ብለው፡ ግብፃውያን፡ "ፍትሐ ነገሥት" በተባለው መጽሐፋቸው፡ በሥርዋፅ (በእመጫት) ያገቡትንና በአዋጅ ያስታወቁትን ቃል፡ የኢትዮጵያ ቤተ ምልክና፡ ሥጋዊና ምድራዊ፡ ዓለማዊም የኾነ ጠባብ ፍላጎቱን ለማስፈጸም ሲል፡ ተስማምቶ ሲቀበለውና ቤተ ሕዝቡንም እንዲቀበለው ሲያደርግ፡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የሚገኙባት ቤተ ክህነት ጭምር፡ ለ፩ሺ፮፻ ዓመታት ያህል፡ ተቀብላውና ቀንበሩን ተሸክማ ኖራ የለምን? ይህ፡ እንዴት ያስደንቃችኋል! የዚህን ዝርዝር፡ ቀደም ብዬ በገለጽሁላችሁ፡ የባዕዳኑ መጽሐፍና በተለይ፡ “ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!” በሚለው መጽሐፌ ውስጥ ታገኙታላችሁና፡ እዚያ ተመልከቱት!

በዚያ መጽሐፌ ውስጥ ከቀረቡት፡ የበደል ዝርዝሮች መካከል፡ ሐተታ ሳይሰጥበት የቀረ ቢኖር፡ በ"አበገደ" ፊደላችን እና “መዓዛ ቅዳሴ” በተባለችው ቅዳሴያችን ላይ የተፈጸመው ደባና በደል ነው። ይህንንም፡ እንደሚከተለው፡ ባጭሩ ልግለጽላችሁ!

፩ኛ፡ "የአዳምና ሔዋን ልሳን" ተብሎ፡ ለዓለም ቋንቋዎች፡ ሥርና ግንድ ለኾነው ለ"ግእዝ" ማንነት፡ መታወቂያው የኾነውንና በአሌፋቱ (በፊደሎቹ) ተራ፡ በግልጽ የሚታወቀውን፡ የ"አ(ኸ)በገደ"ን ሥርዓተ ፊደል፡ ግብፃውያን፡ ኾን ብለው፡ መሠረታዊ አቋሙን አፋልሰው፡ ደብዛውን ጭምር ለማጥፋት ሲሉ፡ ሥርዓቱን፡ ወደ"ሀሁ" መለወጣቸው ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህ የኾነው፡ ግብፃውያን፡ "በኢትዮጵያ፡ የመጀመሪያው ጳጳሳችን ነው!" በሚሉት፡ እኛ ግን፡ በኢትዮጵያዊነቱ፡ "አባ ሰላማ፡ ከሣቴ ብርሃን" በምንለው፡ በፍሬምናጦስ ዘመን እንደኾነ ይነገራል፡፡ ይህ ድርጊት የተፈጸመው፡ እርግጥ፡ በእርሱ ዘመን ከኾነ፡ "የፊደሉ ተማሪ የኾነው፡ ኢትዮጵያዊው ሕፃን፡ መሠረታዊዉን፡ የ'አ(ኧ)በገደ'ን ፊደል፡ በትክክል አውቆ እንደኾነ ለማረጋገጥ እንዲያስችል፡ ምናልባት፡ በቅን ዓላማ ታስቦ፡ ፊደላቱ፡ በሌላ መልክ ተዛንቀው (ተሠባጥረው) እንዲቀርቡ የተደረገበት መማሪያ ሊኾን ይችላል፡" ብሎ መገመቱ ያስኬዳል፡፡ አለዚያ ግን፡ "ይህን የመሰለው አሠራር፡ በኋለኞቹ ግብፃውያን ተወጥኖ የተፈጸመ የጠላትነት ግብር ነው፡" ከማለት በቀር፡ ሌላ ምክንያት ሊቀርብበት ያዳግታል፡፡

፪ኛ፡ ለእናታችንና ንግሥታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የቅዱስ ቍርባን ምስጋና ኾና፡ መሥዋዕት ሲቀርብባት የኖረችው፡ "መዓዛ ቅዳሴ" የተባለች፡ ኢትዮጵያዊው፡ አባ ጊዮርጊስ፡ ዘጋስጫ የደረሳት፡ የቅዳሴ መጽሐፍ አለች፡፡

ይህች የቅዳሴ መጽሐፍ፡ "ከግብፃውያን የተገኙ" ተብለው ከሚታሰቡት፡ ከሌሎቹ፡ የቅዳሴ መጻሕፍቶቻችን መካከል፡ የኋላ ኋላ፡ በተለይ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የሥልጣን ዘመን፡ በግብፃውያኑ ጳጳሳት፡ ተለይታ እንድትወጣ፡ በእርሷ የመቀደሱ ባህልና ሥርዓትም፡ በመላ የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት፡ እንዲቋረጥ መደረጉ፡ ሌላው በደል ነው፡፡

ቅዳሴ ማርያምና መዓዛ ቅዳሴ፡ ኹለቱም ቅዳሴያት፡ ከተደረሱበት ዘመን ጀምሮ፡ በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን እስከተከሠተው፡ "የኅዳር በሽታ" ድረስ፡ በፍልሰታ ሱባዔ፡ ቅዳሴ ማርያም፡ በወርኀ ጽጌ ደግሞ፡ መዓዛ ቅዳሴ፡ ተመድበው፡ በሌሎቹ፡ የእመቤታችን በዓላት ግን፡ በየተራ፡ ይቀደሱ ነበር፡፡ በተለይም፡ መቅሠፍት በሚኾንበት ወራት፡ ማለትም፡ ቸነፈር (ወረርሽኝ በሽታ)፡ ድርቅና ረሃብ፡ ወይም ጦርነት በተነሣ ጊዜ፡ አብያተ ክርስቲያናት፡ ምሕላ እንዲይዙ ሲታዘዙ፡ "ምሕላ ያዙ! መዓዛ ቅዳሴን ቀድሱ!" እየተባለ፡ የምሕላው ጊዜ እስኪፈጸም ድረስ፡ መደዳውን የምትቀደሰው፡ መዓዛ ቅዳሴ ነበረች፡፡

ግብፃውያን፡ የአገራቸው ሊቃውንት የደረሷቸውን የቅዳሴ መጻሕፍት ተቀብለውና አክብረው፡ በየትምህርት ቤቶቻቸው ሲያስተምሩዋቸውና በየቤተ መቅደሶቻቸው ሲቀድሱባቸው፥ በሌላውም አገር፡ አሠራጭተው እንዲሠራባቸው ሲያደርጉ፥ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እንኳ ሳትቀር፡ መዓዛ ቅዳሴን፡ ተቀብላና አክብራ፥ ከሊቃውንቱ ቅዳሴያትም፡ ቅድሚያ ሰጥታና ተራ አስገብታ በማሳተም፡ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን፡ በሮም ባሉ ቤተ መቅደሶቿ ጭምር እንድትቀደስ ስታደርግ፡ በግብፃውያን አመራር ሥር የነበረችው፡ የራሳችን ቤተ ክህነት፡ ከቅዳሴው መጽሐፍ ተራ አውጥታና ራሳቸው፡ ኢትዮጵያውያን እንዳይቀድሱባት ወስና፡ ወደውጭ መጣሏ፥ ይልቁንም፡ ነፃ የወጣችው፡ የዛሬዋ ቤተ ክህነት ኢትዮጵያውያን መሪዎች፡ ወደነበረችበት የክብር ቦታዋ ሳይመልሷት መቆየታቸው፡ እጅግ ያስገርማል፡፡

# ምዕራፍ ፱: ሃይማኖት::
## ስለአበገደ ፊደላችንና ስለመዓዛ ቅዳሴያችን::

---

በተለይም: የዚህ ኹሉ በደል: ምንጩ ምክንያት: መዓዛ ቅዳሴን የደረሳት: ኢትዮጵያዊ ሊቅ መኾኑና በጸሎቱ ውስጥ: የኢትዮጵያውያን አባት: የመልከ ጼዴቅ ስም መነሣቱ ሲኾን: ይህም: እንደወንጀል ተቈጥሮ:[፳፩] የቅዳሴዋን ዕድል: ከዚህ ማድረሱ: በጣሙን ያሳዝናል::

ስለዚህ: ይህ የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት: ይህን የመሰለ በደል ተፈጽሞበት መቆየቱ: "ይህን ያህል ሊያስደንቅ አይችልም!" ያልኋችሁ: ለዚህ ነው::

## ስለኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት ሐተታ::

*ጥያቄ:- በ፩ኛው ተራ ቍጥር የተመለከተው የኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት: በ፪ኛና በ፫ኛ ተራ ቍጥሮች ከተመለከቱት: ከሐዋርያትና ከሊቃውንት የሃይማኖት ጸሎቶች የሚለየው: ቀዳሚ ሊኾን የቻለውስ: በምንና እንዴት ነው?*

መልስ:- እኛ ኢትዮጵያውያን: በ፩ኛው ተራ ቍጥር ከተመለከተው: የሃይማኖት ጸሎታችን ጋር: በ፪ኛና በ፫ኛ ተራ ቍጥሮች የተመለከቱትን: ኹለቱን የሃይማኖት ጸሎቶች: በሙሉ ተቀብለንና ጨምረን: እንጸልያቸዋለን:: በ፩ኛው ተራ ቍጥር የተመለከተው: የኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት: በ፪ኛው ተራ ቁጥር ከተመለከተው: ከሐዋርያት የሃይማኖት ጸሎት ይልቅ: በ፬ኛው ምዕት ዓመት: በኒቅያ የተሰበሰቡት: ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት ተስማምተው ካወጡት: ከ፫ኛው ተራ ቍጥር የሃይማኖት ጸሎት ጋር: በበለጠ ይቀራረባል: ይኹን እንጂ: ከእርሱም ቢኾን: በጥቂቱ የሚለይበት አለ: ይህም የኾነው: የኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት: ከሊቃውንቱም ኾነ ከሓዋርያቱ የሃይማኖት ጸሎቶች ይልቅ: በጥንታዊነቱና በቀዳሚነቱ ላይ: የጥራት: የቀጥተኛነትና የግልጽነት ባሕርይ ያለው በመኾኑ ነው: የሚለየውም: ከዚህ በሚከተሉት ኃይላተ ቃላት መኾኑን: በማስተዋል ተመልከቱት! እነዚህም:-

*፩: "እኛ ኢትዮጵያውያን!":-*

ጸሎቱ: የኢትዮጵያውያን ብቻ መኾኑን: የሚጸልዩትም: ኢትዮጵያውያን ብቻ መኾናቸውን: ደግሞም: ጸሎቱን: በኢትዮጵያዊነት የማያምን ባዕድ: ሊጸልየው የማይችልና የማይገባ መኾኑን: ገና ከመግቢያው ያመለክታል: የሚያምነው ባዕድ: ሊጸልየው የሚችለውና የሚገባው: በኢትዮጵያዊነት አምኖ: ኢትዮጵያዊ ሲኾን ብቻ ነው ማለት ነው::

*፪: "በእግዚአብሔር ወልድም": "በእግዚአብሔር" መንፈስ ቅዱስም እናምናለን::":-*

የሃይማኖት ጸሎት: በተቻለ መጠን: ኹሉንም ምሥጢራት: በጥራት: በቀጥተኛነትና በግልጽነት አካትቶ መያዝ አለበት: በምሥጢረ ሥላሴም: የሦስቱ አካላት: አንድ እግዚአብሔርነት ተብራርቶ ሊገለጽበትና ተሟልቶ ሊገኝበት ይገባል::

ስለዚህ፡ ቀደም ብሎ፡ ለእግዚአብሔር አብ ብቻ ተሰጥቶ፡ "በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።" የሚለው፡ በሌሎቹ የሃይማኖት ጸሎቶች ውስጥ የሌለው የእምነት ማረጋገጫ፡ በኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት ውስጥ፡ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስም ተሰጥቶ፡ "በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን።"፡ ወረድ ብሎም፡ "በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን።" መባሉ፡ በምሥጢረ ሥላሴ ሃይማኖታቸው ዘንድ፡ ሕፀፅ እንዳይኖር፡ ኢትዮጵያውያን ያደረጉትን ጥንቃቄ ያሳያል። ይህም፡ "ወልድ ፍጡር ነው!"፡ "መንፈስ ቅዱስም፡ ከአብና ከወልድ ያንሳል! የሠረፀውም፡ ከአብና ከወልድ ነው!" የሚሉ መናፍቃን ስላሉ፡ ሦስቱም፡ በእግዚአብሔርነት፡ አንድና እኩል መኾናቸውን አረጋግጦ ለመግለጽ አብቅቷል።

፫፡ *"ከሥጋዋ ሥጋ፡ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡"*፡-

እግዚአብሔር ወልድ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሰው የኾነው፡ ከእርሷ፡ "ከነፍሷ ሳይኾን፡ ከሥጋ አካሏና ባሕርይዋ ብቻ፡ ሰውነትን በመንሣት ነው፡" የሚሉ ወገኖች መኖራቸው በይፋ ይታወቃል፡ የቅዱስ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን ሃይማኖት ዋና መሠረት ደግሞ፡ "እግዚአብሔር ወልድ፡ ፍጹም ሰው ኾኖ፡ በዚህ፡ በልዩው የተዋሕዶ ምሥጢር፡ ከኹለት (የመለኮትና የሰውነት) አካላት፡ አንድ አካል፡ ከኹለት (የመለኮትና የሰውነት) ባሕርያት፡ አንድ ባሕርይ በኾነው ሰውነቱ፡ መከራን ተቀብሎ፡ ደሙን አፍስሶ፡ ሞቶና ተነሥቶ አዳነን!" ብሎ ማመን ነው።

በመሠረቱ፡ ፍጹም ሰው ለመኾን፡ የነፍስና የሥጋ አካላትና ባሕርያት፡ ተዋሕደው መገኘት አለባቸው፡ ይህም፡ ለማንም ሰብአዊ ፍጡር፡ ሥውር አይደለም፡ ስለዚህ፡ ኢትዮጵያውያን፡ የሃይማኖት ጸሎታቸው፡ "ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሰው ኾነ!" በሚለው ቃል መወሰኑ፡ ሕፀፅ (ጉድለት) በሌለባት፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸው ላይ፡ ኾን ተብሎ፡ በባዕዳን የተፈጸመ ደባ መኾኑን በማወቅ፡ "ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ *ከሥጋዋ ሥጋ፡ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡* ፍጹም ሰውን ኾነ!" የሚለው ቃል፡ በትርጓሜ ብቻ ሳይኾን፡ በሃይማኖት ጸሎታቸውም ውስጥ፡ እንዲህ፡ በተጣራና በተሟላ አገላለጽ፡ ተካትቶ እንዲገኝ አድርገውት ኖረዋል።

፬፡ *"በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ።"*፡-

በሠለስቱ ምዕት የሃይማኖት ጸሎት ውስጥ ብቻ የተጠቀሰው ይህ ሐረግ፡ በሐዋርያትም ኾነ፡ በኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት ውስጥ የለም። በኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት ውስጥ የሌለበት ምክንያት፡ የኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት፡ ከመነሻው እስከመድረሻው፡ እግዚአብሔር፡ *"ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፡ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። ...እያንዳንዱ ሰው፡ ባልንጀራውን፡ እያንዳንዱም፡ ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፡ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!"* ብሎ፡ በነቢያቱ አንደበት፡ በተናገረው መሠረት፡ በቅዱሳት መጻሕፍቱ ውስጥ በተመዘገበው ትንቢታዊ ቃሉ መሠረት፡ ከኪዳን ልቦናው ጀምሮ እስከኪዳን ምሕረቱ ድረስ፡ በኢትዮጵያውያን የልብ ጽላት ላይ፡ በቃል ኪዳን ተቀርጾ ስለሚገኝ ነው።[፳፱]

# ምዕራፍ ፱፡ ሃይማኖት።
## ስለኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት ሓተታ።

ኢትዮጵያውያን፡ ለዚህ መለኮታዊ ቃል ኪዳን፡ ቅድሚያን መስጠታቸውና በእርሱ፡ እስከመጨረሻው መጽናታቸው፡ ይህ አቋማቸው፡ ራሱ፡ እውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን፡ እስካኹን መስክሩዋል፤ ዛሬና ወደፊትም ሲመሰክር ይኖራል። ለዚህም፡ በዓለም ላይ ያሉትን፡ የእግዚአብሔር አማኞች ሃይማኖቶች፡ ክርስቲያኖቹን ጭምር፡ እርስ በርሳቸው እንዲለያዩ ያደረጋቸው፡ በቅዱሳት መጻሕፍቱ ቃላት ላይ የተካኼደው፡ *"ፀጉር እስከመሠንጠቅ የደረሰው"* አተረጓጐም መኾኑ፡ በቂ ማስረጃ ነው፤ ይህንም እውነታ፡ ሓዋርያው፡ *"ሰዎች ኹሉ የሚያውቋትና የሚያነብቡት፡ በልባችን የተጻፈ መልእክታችን፡ እናንተ ናችሁ፡ እናንተም፡ በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ፡ በቀለም ባይደለ፡ ሥጋ በኾነ፡ በልብ ጽላት እንጂ፡ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ፡ በእኛም የተገለገለ፡ የክርስቶስ መልእክት እንደኾናችሁ የተገለጠ ነው። በክርስቶስም በኩል፡ ወደእግዚአብሔር የሚያደርስ፡ እንዲህ ያለ እምነት አለን። ብቃታችን፡ ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፡ በገዛ እጃችን እንደሚኾን፡ አንዳችን እንኳ ልናስብ፡ ራሳችን፡ የበቃን አይደለንም፡ እርሱም ደግሞ፡ በመንፈስ እንጂ፡ በፊደል ለማይኾን፡ ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንኾን ዘንድ አበቃን፡ ፊደል ይገድላልና፤ መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።"* ባለው ቃሉ አብራርቶታል።

ስለዚህ፡ ይህ፡ "በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ" የሚለው ሓረግ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ በሃይማኖት ጸሎታቸው ውስጥ፡ ጥንቱኑም፡ ዛሬም፥ ለመቼውም ጊዜ ሳያስፈልጋቸው ኖርዋል፡ ይኖራልም።

፩፡ *"በዙፋኑ* ተቀመጠ።"፡-

ከጸሎቱ ወደታች፡ "ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም፤" ብሎ፡ የንጉሥነት ሥልጣኑን የሚገልጽ ስለኾነ፡ "በአባቱ ቀኝ" የተቀመጠው፡ በዙፋኑ ላይ መኾኑን፡ አግዝፎና እውን አድርጎ ያሳያል።

፪፡ *"በሓዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው።"*፡-

የመንፈስ ቅዱስን ማንነት፥ እግዚአብሔርም፡ በቸርነቱ፡ ለሰውና ለቀረው ፍጥረተ ዓለም ያበረከተውን በጎ ነገርና የሰጠውን ጸጋ፡ በበለጠ አብራርቶ በማስረዳት፡ የኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት፡ ሊቀር የማይገባውንና ከሌሎቹ ጸሎቶች የጎደለውን ክፍል፡ እንዴት አድርጎ፡ አሟልቶት እንደሚገኝ፡ አስተውሉት!

፫፡ *"ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፡ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሓዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡"*፡-

ይህ፡ በሓዋርያት የሃይማኖት ጸሎት ውስጥ የሌለው፡ በሠለስቱ ምዕት የሃይማኖት ጸሎት ውስጥ ደግሞ፡ "ከኹሉ በላይ በምትኾን፡ ሓዋርያት በሰበሰቧት" በሚል ሓረግ የተወሰነውና ለአንዲቷ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ማብራሪያ፡ በኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት ውስጥ ብቻ ሊገኝ የቻለው፡ በምን ምክንያት እንደኾነ፡ ከዚህ የሚከተለው ሓተታ ያስረዳችኋል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

"የሐዋርያት" እና "የሠለስቱ ምዕት" ጸሎታተ ሃይማኖት የተዘጋጁት፡ ከክርስቶስ ዕርገትና ከመንፈስ ቅዱስ ርደት (መውረድ) በኋላ፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በመጀመሪያው ምዕት ዓመት፡ በኢየሩሳሌም በተሰበሰቡ ሐዋርያትና በ፬ኛው ምዕት ዓመት፡ በኒቅያ በተሰበሰቡ፡ በ፫፻፲፰ ሊቃውንት ሲኾን፡ እነርሱም፡ በአዲስ ኪዳኑ መሠረት፡ ወደክርስትና እምነት ለገቡት አይሁድ፡ አሕዛብና አረማውያን፡ የሃይማኖት ማሳወቂያና ማጽኛ ኾነው እንዲያገለግሉ የተጻፉ መኾናቸው፡ የታወቀ ነው:: ለእኒሁ ወገኖች፡ በዘመነ ሐዲስ የተሰበከላቸውን የክርስትናን ሃይማኖት እንድታስተምርና እንድትጠብቅ የተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን፡ በሐዋርያት እንደተመሠረተች ቀደርጎ የተጻፈው፡ ሐዋርያት ባዘጋጁት የሃይማኖት ጸሎት ላይ ሳይኾን፡ በኋለኛው፡ በሊቃውንቱ የሃይማኖት ጸሎት ላይ መኾኑን አስተውላችሁ ተመልከቱት!

ጥያቄ:- *ይህ ለምን ኾነ?*

መልስ:- ምክንያቱ፡ ግልጽ ነው:: በመጀመሪያ ነገር፡ "ኢትዮጵያውያን፡ ከራሳቸው ሰዎች መካከል፡ ጳጳሳትን መርጠው አይሹሙ!" የተባለበትን፡ "ፍትሐ ነገሥት" የተባለውን መጽሐፍ ያዘጋጁት፡ እኒሁ፡ በኒቅያ የተሰበሰቡት ሊቃውንት መኾናቸው፡ በግብፃውያኑ ተነግሮአል:: በዚያ መጽሐፍ ውስጥ፡ ያን የመሰለ፡ ግልጽ ስሕተት የተፈጸመ ከኾነ፡ ይኸም የሃይማኖት ጸሎት በተዘጋጀበት ጊዜ፡ ምናልባት፡ ከማወቅም ኾነ ካለማወቅ የተነሣ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት፡ ሌላ ስሕተት ሊደርስ አይችልም ብሎ ለመደምደም፡ ያዳግት ይኾናል::

የዚህም መነሻ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥተው፡ ዘመነ አበውንና ዘመነ ነቢያትን ባጠቃለለው፡ በብሉዩ ኪዳን ዕድሜያቸው ውስጥ፡ ባሳለፉት ህልውናቸው ጊዜ፡ ማለትም፡ ኪዳነ ልቦናንና ኪዳነ ኦሪትን ተቀብለው በቆዩበት ጊዜ፡ ይዘውት የኖሩት ሃይማኖትና ሥርዓት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር፡ አምልኮተ እግዚአብሔርንና ሥልጣነ ክህነትን አዋህዶ ያካተተ መኾኑን፡ እርግጥ፡ በኒቅያ የተሰበሰቡት፡ እኒያ፡ የአዲስ ኪዳኑ ሊቃውንት የማያውቁ ከኾነ፥ ወይም፡ ያን እውነታ አውቀውት፡ ነገር ግን፡ ለመቀበል፡ ሳይፈልጉ ቀርተው እንደኾነ፡ ያ አላዋቂነት፥ ወይም፡ ያ ዝንባሌ፡ ለዚያ ስሕተት፡ መንሥዔ ሊኾን ስለሚችል ነው::

ስለዚህ፡ የኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት፡ የሐዋርያትንና የሊቃውንቱን የሃይማኖት ጸሎቶች፡ አጠቃልሉና አዋህዶ እንደያዘ ኾኖ፡ በተጨማሪ ግን፡ ኢትዮጵያ፡ ከኹሉ ይልቅ፡ በዘመነ ብሉይ፡ ከኪዳነ ልቦናና ከኪዳነ ኦሪቱ ጊዜ ጀምሮ፡ በአምልኮተ እግዚአብሔርና በሥልጣነ ክህነት፥ በእግዚአብሔር መንግሥትነትም፡ ቅድሚያና ጥንታዊነት ያላት መኾኗን ለማመልከት፡ ይህ፡ የተጠቀሰው ቃል፡ የኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት፡ አካል ኾኖ መኖሩ፡ ሙሉ አግባብነት አለው::

# ምዕራፍ ፪፣ ሃይማኖት።
## ስለኢትዮጵያውያኑ የሃይማኖት ጸሎት ሐተታ።

ቀዳማዊነቷና ጥንታዊነቷም፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ፡ በአዲስ ኪዳኑ መሠረት በተቋቋሙት፡ ዛሬ፡ "ኦርቶዶክስ" እና "ካቶሊክ" ተብለው በተከፋፈሉት፣ በቅርቡም "ፕሮቴስታንት" ተብለው በተለዩት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ነው። ይህንኑ ይዞታዋንና አቋሟን፡ የአዲሱ ኪዳን መሥዋዕት በኾነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ አጽንታና ለፍጹምነት አብቅታ፥ ቤተ መቅደሷንም፡ "ቤተ ክርስቲያን" ብላ ሠይማ፡ ህልውናዋን የቀጠለች በመኾኗ፡ የብቻዋ ስለኾነው፡ ስለዚሁ የሃይማኖት ጸሎቷ ቃል ተገቢነት፡ አንዳችም የሚያጠያይቅ ነገር አይኖርም። ይህ፡ የሃይማኖት ቃል፡ የእግዚአብሔር እውነት ያስገኘችውና በኢትዮጵያውያን የልብ ጽላት ላይ፡ በመለኮት ጣቶች ተጽፎ፡ እንዲህ፡ በሕያውነት ሲነበብ በመኖሩ፡ እናንተም፥ እኔም፥ ኢትዮጵያውያንም ኹሉ፡ እጅግ ደስ ሊለን ይገባል። ፳፬

## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሐተታ።

**ጥያቄ:-** *የዚህን ክፍል ማብራሪያህን ከማብቃትህ በፊት፡ ከዚሁ፡ ከኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ጸሎት ጋር እንድንጸልየው ስለተደረገውና ማንነታችንን በይበልጥ ስለሚያመላክተው፡ ስለኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን ጸሎት፡ አያይዘህ፡ ዝርዝር መግለጫን ብትሰጠን?*

**መልስ:-** አዎን! እንደሃይማኖቱ ጸሎት ኹሉ፡ ይህንም፡ የቃል ኪዳኑን ጸሎት ምንነትና ይዘት፥ ከያዘው ታላቅ መልእክት ጋር በዝርዝር ማወቅ፡ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና ለእያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ቀዳሚ ግዴታ ስለኾነ፡ ይህን ቁም ነገር ማንሣታችሁ፡ ተገቢ ነው። በዚህ ጸሎት ውስጥ ስለተካተቱትና ኢትዮጵያዊዉን ሰው ስላስገኙት፡ ስለሰባቱ ቅዱሳት ቃል ኪዳናት፡ ቀደም ብለውና ተከታትለው በታተሙት መጻሕፍቴ ውስጥ የሠፈሩትን ዝርዝር ማብራሪያዎች አትዘነጉትም። ይልቁንም፡ የዚህ፡ ውይይታችን፡ ፊታውራሪ በኾነው፡ በአንደኛው ውይይታችን ላይ፡ በየራሳቸውና በአጠቃላይ፡ የተሰጡትን ሐተታዎች፡ ከዚህ ጋር እያይዛችሁ ልታስታውሷቸው አስፈላጊ ይኾናል።

እርግጥ ነው! በእግዚአብሔር ፊት፡ በእውነትና በመንፈስ የሚቀርብ፡ ተሰሚነትና ተቀባይነት ያለውን አምልኮ ለመፈጸም፡ የሚጸልዩትን ማናቸውንም ጸሎት፡ ያወቁትና የተረዱት፥ ያመኑበትም ሊኾን እንደሚገባ፡ ማንኛውም እውነተኛ ምእመን ይገነዘበዋል። ነገር ግን፡ በየዘመናቱ እየተነሣና እያለፈ፡ በሥጋ ልደት ሲወርድ ሲዋረድ፡ ከዚህ የደረሰውን ኢትዮጵያዊ ትውልድ፥ ዛሬ በሕይወት ያለውን ጨምሮ፡ በማንነቱና በህልውናው ረገድ ችግር ሲያደርስበት፥ ሲጎዳውም የኖረው፥ አኹንም እየጎዳው ያለው፡ ይህንኑ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱን፡ ከሕጻንነቱ ጀምሮ፡ አፉን በፈታበት እናት ቋንቋውና በተገቢው ሥርዓተ ትምህርት እንዲያውቅ ባለመደረጉ መኾኑ ተረጋግጦ የታወቀ እውነታ ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

በተለይም፡ ከእግዚአብሔር በተማረው ትምህርት ብቻ ጠብቆት የኖረውን፡ የቃል ኪዳን ሃይማኖቱን ሊያስከዱት፡ የበግ ለምድ ለብሰውና በዘመናዊው ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተሠውረው የመጡበትን ጠላቶቹን ሊቋቋማቸው ያቃተው፡ ከዚሁ ጉድለቱና ደካማነቱ የተነሣ መኾኑ፡ ሊታበል ከቶ አይቻልም።

አንዳንድ ቤተሰቦች፡ ልጆቻቸውን፡ "የቄስ ትምህርት ቤት" ይባል ወደነበረው (በአኹኑ ዘመን ግን፡ እርሱዉም ወደቀረው) የትምህርት ገበታ የሚልኩ ቢኖሩም እንኳ፡ በዚያ ገበታ ይቀርብ የነበረው ትምህርት፡ ለሕጻናቱ ይሰጥ የነበረው፡ ትርጉሙ፡ በማይገባቸው፡ በግእዝ ቋንቋ ብቻ በመኾኑ፡ የአላዋቂነቱን መጠን፡ በበለጠ ከፍ አድርጎ አባብሶታል፤ ሕጻኑ ካደገ በኋላ፡ በዚህ መልክ ባገኘው የቃል ትምህርቱም ቢኾን፡ ዘወትር በሚደግመውና በሚሰማው ጸሎቱ አማካይነት፡ ሃይማኖቱን እንዳያጠናክርበት እንኳ፡ የጸሎቱ ቋንቋ የኾነውን የግእዙን ፍቺውን ስለማያውቀው፡ በጸሎቱ አማካይነት ከፈጣሪው ጋር የሚያካኺደው ግንኙነት፡ ከቶውንም፡ ከልቡናው፡ በተፈጥሮው ከሚገነዘበው በቀር፡ በአእምሮው ተረድቶ፡ ሊሠምርለት ሳይችል እንደኖረ፡ በማንም አስተዋይ ተመልካች ዘንድ፡ በቀላሉ ይታወቃል።

ስለዚህ፡ ለዚህ ችግር፡ በቀደመው ጊዜ የነበረው መፍትሔ፡ ራሱን፡ ግእዙን፡ ፊደሉን፡ ንባቡንና አጻጻፉን ብቻ ሳይኾን፡ የቋንቋውን ትርጉምና የሰዋስዉን ሥርዓት ጭምር፡ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና ለእያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ከሕፃንነት ጀምሮ ማስተማሩ ነበረ፤ ዳሩ ግን፡ ያ፡ ስላልኾነ፡ በአኹኑ ጊዜ ያለው ምርጫ፡ አንድ ብቻ ኹኖ ይታያል፡ እርሱም፡ ለወደፊቱ፡ ግእዙን፡ በትምህርት እንዲያውቅ ማብቃቱ ሲኾን፡ እስከዚያው ድረስ ግን፡ ጸሎቱን፡ ለኹለቱም ልሳናት፡ ምንጭ የኾነው ግእዙና መነጋገርያው የኾነው ኢትዮጵያኛው (ዐማርኛው)፡ በትርጉም፡ ጎን ለጎን በሚኼዱ፡ በኹለት አዕማድ ተጽፎ እንዲቀርብ ማድረግ ይኾናል፤ ይኹን እንጂ፡ አኹን ያለው ዕድል፡ በዚሁ፡ በኢትዮጵያኛው ፍቺ ብቻ ጽፎ ማስነበብ ኾኖ ተገኝቷል።

ግእዝ፡ ለኢትዮጵያዊው ትውልድ፡ እናንተንና እኔን ጨምሮ፡ የማንነቱ፡ አንዱ፡ የተለየ መታወቂያ ሀብቱ ስለኾነ፡ በሰዋስው ሥርዓቱ፡ የጠራ፥ በቃላቱ የበለጸገና በሥነ ጽሑፉ የተሟላ የኾነውን፡ ይህን፡ እናትና መሠረታዊ ቋንቋ፡ ዛሬም፥ ወደፊትም፥ ለምንጊዜውም ቢኾን፡ በማስተማር ማሳወቅ የሚገባና የሚያስፈልግ፥ ትውልዱም፡ ይህንኑ ልሳኑን በመማር፡ ማወቅ የሚገባውና የሚያስፈልገው መኾኑን፡ በዚህ አጋጣሚ፡ እዚህ ላይ፡ አበክሬ እንድገልጽላችሁ ግዴታዬ ይኾናል።

የሃይማኖቱ መሠረቶች እንደኾኑት፡ እንደዓሠርቱ የእግዚአብሔር ቃላትና እንደሌሎቹ፡ የሃይማኖት፥ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎታት ኹሉ፡ ይህም የቃል ኪዳን ጸሎት፡ በኢትዮጵያውያን የልብ ጽላት ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጣቶች ተጽፎ፡ ቅዱሱ ኪዳን፡ በእነርሱ ማደሪያነት፡ ገዝፎና ሕያው ኾኖ፥ እነርሱም፡ በእርሱ ሕያዋን ኾነው፡ መልካሙን የኢትዮጵያዊነት ጸጋ፡ ሕይወት አድርገውት፡ ይኸው እስከዛሬ ኖረዋል፤ ዛሬም እየኖሩት ናቸው፤ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም ይኖሩታል።

# ምዕራፍ ፬፤ ሃይማኖት።
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎቷ ሐተታ።

ኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ፡ ሕይወት አድርገውት የኖሩት፥ እየኖሩ ያሉትና ወደፊት የሚኖሩት፥ ማለትም፡ በእነርሱ ሰውነት ላይ ሕያው ኾኖና ገዝፎ የኖረው፥ እየኖረ ያለውና የሚኖረው፡ ሰባቱን ቃል ኪዳናት የያዘው ቅዱሱ ኪዳን፡ በጽሑፍ ሠፍሮ የሚሰማበትንና የሚነበብበትን፡ የኢትዮጵያውያንን የቃል ኪዳን ጸሎት፡ እናንተ፡ በየዐረፍተ ነገሩ እያሰማችሁኝ፡ እኔ፡ ማብራሪያውን እየሰጣችሁ፡ እንደሃይማኖቱ ጸሎት፡ ከዚህ በሚቀጥለው መልክ እንወያይበታለን።

*ጥያቄ፡- መልካም! ምን ዓይነት መልእክታዊ ቊም ነገርን እንደያዘ፡ በቅድሚያ አያብራራህ ልታስረዳን የሚያስፈልገው፡ "እኛ ኢትዮጵያውያን፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች፡ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን።" ስለሚለው፡ ስለጸሎቱ መግቢያ ይኾናል።*

*መልስ፡-* አዎን! ግዙፉን ፍጥረተ ዓለም፡ በፈጣሪነቱ፡ "እም ኀበ አልቦ፡ ኀበ ቦ"፡ ማለትም፡ "ካለመኖር፡ ወደመኖር" ያመጣ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያው ዘመን፡ በአዳምና ሔዋን የወጠነውን፡ ከዚያም፡ በኖኅ፥ በመልከ ጼዴቅ፡ በአብርሃም፡ በሙሴና በዳዊት እያጠናከረ የቀጠለውን እና በመጨረሻው ዘመን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም የፈጸመውን፡ "ቅዱሱ ኪዳን" የተባለውን፡ ባለሰባት ምዕራፍ የቃል ኪዳን ስምምነት፡ ስማቸው፡ እዚሁ ላይ በተገለጸው፡ በእኒሁ ተዋዋዮቹ ምርጦቹ አማካይነት ተካይዶ (ተማምሎ) የሰጠው፡ ለመላው የሰው ዘር፥ ለእያንዳንዱም ሰብአዊ ፍጡር፡ በነፍስ ወከፍ፥ ለኹሉም እንጂ፡ ለኢትዮጵያውያን ብቻ አለመኾኑን፡ በቅድሚያ ልታስተውሉት የሚገባ እውነታ ነው።

እግዚአብሔር፡ እነዚህን ቃል ኪዳናት፡ ለመላው የሰው ልጆች ኹሉ እንጂ፡ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ለይቶ ያልሰጠ መኾኑን፡ አጥብቃችሁ እንድታስተውሉት በግድ የሚያስፈልጋችሁ መኾኑን፡ እዚህ ላይ፡ እኔም፡ እንደገና አበክሬ አስታውቃችሁ ዘንድ፥ እናንተም፡ በእርግጥ ታውቁት ዘንድ አግባብ ይኾናል። ምክንያቱም፡ ፈጣሪ፡ ኢትዮጵያውያንን፡ በቀሩት የዓለም ሕዝቦች ዘንድ፡ ላቆመው ለሰፊው የጸጋ ሚዛኑ፡ መሥፈሪያ፥ ለሚሰጠውም የመጨረሻ ፍርዱ፡ መፋረጃ ያደረገበት አምላካዊ ምክንያት የሚመነጨው ከዚህ እውነታ በመኾኑ ነው።

መለኮታዊ ቸርነቱ፡ እንዲህ፡ ለኹሉ ሰብአዊ ፍጡር የተበረከተ ሲኾን፡ ነገር ግን፡ ይህን፡ የቃል ኪዳን ስጦታውን፡ ኹሉም ሰብአዊ ፍጡር አልተቀበለውም፤ ለምሳሌ፡ በመጀመሪያው፡ በአዳምና ሔዋን ቃል ኪዳን ስጦታው ላይ፡ በኖኅ ዘመን ደርሶ እንደታየው ማለት ነው፤ በእግዚአብሔር እምነትና አምልኮት ላይ የተመሠረተውን፡ ያን፡ የመጀመሪያ የጋብቻ ቃል ኪዳን፡ በዚያን ዘመን፡ ከአንዲት ሚስቱና ከሦስት ልጆቹ ጋር አክብሮ የተቀበለና ፈጽሞ የተገኘ፡ አንድ ኖኅ ብቻ ነበር።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በዚያን ጊዜ፡ በምድር ገጽ በርክተው የነበሩት፡ የቀሩት የሰው ልጆች፡ በሙሉ፡ እንዳቸውም አክብረው እንዳልተቀበሉትና ፈጽመውትም እንዳልተገኙ፥ ከዚህ ዓመፃቸው የተነሣም፡ ኖኅና ቤተሰቡ ብቻ ሲተርፉ፡ እነርሱ ግን፡ ኹሉም፡ በጥፋት ውኃ ተደምስሰው እንዳለቁ ይታወቃል። በተከታታዮቹ ቃል ኪዳናትም ላይ የደረሰው ዕድል፡ ይኸው ዓይነት መኾኑን፡ ዛሬ፡ በመላው ዓለም ላይ፡ በተለያዩት የሰው ልጆች ቋንቋዎች ተተርጉመው የሚነበቡት ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ።

እግዚአብሔር፡ ሰብአውያን ፍጡሮቹ፡ በምድርና በሰማይ፥ በሥጋና በነፍስ፡ ለጊዜውና ለዘለዓለም፡ ያለልዩነትና ያለአድልዎ፡ በመልካም ሕይወት ይኖሩባቸው ዘንድ፡ ሊገለጽ በማይቻል ቸርነቱና ለጋሥነቱ፡ ለኹሉም የሰጣቸውን፡ እነዚህን፡ ሰባቱን ቃል ኪዳናት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምረው፡ እንደኖኅ፡ በእርሱና ከእርሱም በኋላ፡ በሌሎቹ አማካይነት፡ ባልተቋረጠ ይዘት የተላለፉላቸውን፡ እነዚህኑ፡ ሰባቱን ቃል ኪዳናት፡ በየራሳቸው የመምረጥ ነጻነታቸውና የመወሰን ሥልጣናቸው ተጠቅመው፡ በሙሉ ተቀብለውና አክብረው፡ ጠብቀውና ፈጽመው የተገኙ፡ ኢትዮጵያውያን ብቻ ኾኑ!

ስለዚህ፡ "እኛ ኢትዮጵያውያን" የሚለው መነሻ፡ እንዲኖር አስፈላጊ የኾነውም፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን ሊታወቅ ይገባል። እኒህ፡ ሰባቱም ቃል ኪዳናት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነትንና ተከባሪነትን አግኝተው፡ ተጠብቀውና ተፈጽመው የኖሩት፡ በኢትዮጵያዊው ሰውነትና በኢትዮጵያዊነት ባሕርይ ስለኾነ፡ ይህ ሰውነትና ባሕርይ፡ "የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት" ይባላል፤ እርሱም፡ "ሃይማኖት" ኾኖ የሚታመንበት፡ "ምግባር" ኾኖ የሚሠራበት፥ "ሥርዓት" ኾኖ የሚኖርበት ሊኾን ችሏል።

**ጥያቄ፦** *መልካም! የሚቀጥለው፡ የጸሎቱ ዓቢይ ዐረፍተ ነገር፡ እንዲህ በሚል ቃል የሚነበብ ነውና፡ በዘመናት ስለተከፋፈለው፥ ታላላቅ ቁም ነገሮችንም ስለያዘው፡ ስለዚሁ፡ የጸሎቱ መሠረታዊ መነሻ፡ ያለህን ማብራሪያ ቀጥልልን!*

"እምላካችን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ በመጀመሪያው የአበው ዘመን፡ በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ በኪዳን ልቦና መሠረተው፤ ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቍርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤ በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእሥራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሃድ፡ በኪዳኑ አሪት አከናወነው፤ በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡ ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳኑ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው።"

# ምዕራፍ ፪፡ ሃይማኖት፡፦
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሓተታ፡፡

መልስ፡- እዚህ ላይ፡ እንግዴህ፡ ልብ አድርጋችሁ አስተውሉ! ይህ ጸሎት፡ እየራሳችሁን፡ እንደመስታወት፡ በዓይነ ሕሊናና በዓይነ መንፈስ፡ በምልዓትና በጥልቀት የምትመለከቱበት ልዩ መድረክ ነው፡ ዛሬ ሕያው ኹኖ እየኖረ ያለው፡ የእያንዳንዳችሁ ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ ምንና ማን እንደኾነ፥ በማንና ከየትስ ተነሥቶ፡ ከዚህ እንደደረሰ፡ ከሥሩ፥ ከመሠረቱ፡ በዚህ ጸሎት እያረጋገጣችሁ፡ ለእየራሳችሁ ታሳውቃላችሁ፡ ሥሩ፡ መሠረቱ ከኾነው፡ ከራሱ ከእግዚአብሔር ተነሥቶ፡ በአዳምና ሔዋን በኩል ለበቀለው ሓረግ፡ የዛሬው ፍሬዎቹ፥ በአዳምና ሔዋን ላይ ለቆመውም ሕንፃ ጒልላቱ፡ እናንተው ኹናችሁ፡ እየራሳችሁን ታገኙታላችሁ፡ ይህ እውነታ፡ በእየራሳችሁ ማንነት ገዝፎ በምታገኙበት ጊዜ፡ "ለካ፡ እኔ፡ እንዲህ ነኝና!?" እያላችሁ በአንክሮ ከመደነቅና በፍጹም ደስታ ከመዋጥ ጋር፡ በየአፍታው፡ በየልቦናችሁ ውስጥ የሚሰማችሁ የእርካታና የአመስጋኝነት ስሜት፡ በቃላት ሊገለጽ ከቶ አይቻልም፡፡

በዚህ የጸሎት ቃል፡ ዘወትር፡ በእየራሳችሁ ውስጥ፡ ለእየራሳችሁ የምታሰሙት የምሥራች ዜና፡ "እኔኮ፡ በቃል ኪዳን የማመልከው ፈጣሪዬ፡ በመጀመሪያው የአበው ዘመን፡ በኪዳኑ ልቦና ከመሠረተው፡ ከአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ ያስገኘኝ ነኝ፤ ከዚያም፡ ሕይወቴን፡ በኖኅ፡ የቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ፡ የቊርባንና በአብርሃም፡ የግርዛት ምልክቶች ጠብቆና ተከላክሎ፡ መግቦም ያሳደገኝ ነኝ፤ በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አጕልምሶ፡ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእሥራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሓድ፡ በኪዳኑ አሪት፡ ለዓቅመ አዳም፥ ወይም፡ ለዓቅመ ሔዋን ያደረሰኝ ነኝ፤ በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡ ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም የተወለደው ልጁ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ የቆረሰው ቅዱስ ሥጋውና ያፈሰሰው ክቡር ደሙ፡ ባሠረፀው፡ በኪዳኑ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ለእግዚአብሔር ልጅነት፥ ለመንግሥቱ ወራሽነትና ለእውነቱ አገልጋይነት አብቅቶ፡ ይኸው፡ ዘለዓለማዊዉን ዘውድ ያቀዳጀኝ ነኝ፡፡" የሚል ኾኖ ታገኙታላችሁ፡፡

ኢትዮጵያዊው፡ ይህን ምንነቱንና ማንነቱን፡ ለሚያመልከው ፈጣሪው፥ ለራሱና ለሌላውም ሰብአዊ ፍጡር፡ በቃል ኪዳን ሃይማኖቱ አረጋግጦ፡ በይፋ በማሳወቅ ይመሰክራል፡፡ የሚመሰክረውም፡ ከበቂ ማስረጃዎቹና ዋቢዎቹ ጋር፡ ሰባቱም የቅዱሱ ኪዳን ምልክቶች፡ በሕይወቱና በሰውነቱ ላይ፡ በረቂቅና በግዙፍ መልካቸው ታትመው፡ እየኖራቸውና እየሠራባቸው በሚታየው የህልውና ሥርዓቱ ነው፡፡ ይህም ሥርዓቱ፡ ከዚህ በታች ተተንትኗል፡-

፩ኛ፡ "ኪዳነ አዳም ወሔዋን" የተባለውን፡ "አንድ ወንድ፡ በአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴት፡ በአንድ ወንድ ተወስነው ይኑሩ!" በሚል መመሪያ፡ የመጀመሪያው ቃል ኪዳን የኾነው ጋብቻ የተመሠረተበትን፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ፡ በተቀደሰ ትዳር አክብሮ በመፈጸም የሚኖር መኾኑ፡ በራሱ ሕይወት ተረጋግጦ ይታወቃል፡፡ (ብሕትውናና ምንኵስናም፡ በተለየው መንፈሳዊ ትርጒማቸው፡ በዚሁ ሥርዓት ይካተታሉ፡፡)

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

፪ኛ፡ "እናንተ፡ አምልኩኝ! እኔም፡ እጠብቃችኋለሁ!" የሚለውን የመለኮትን ቋሚ ቃል በመከተል፡ የሰው ልጆች፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ጸንተው ከተገኙ፡ ከማናቸውም የተፈጥሮና የሰው-ሠራሽ ጥፋት ይድኑበት ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በአባታቸው፡ በኖኅ አማካይነት፡ በቃል ኪዳን የሰጣቸውን፡ ባለሦስት ቀለማት የቀስተ ደመና ምልክት፡ የቀደሙት አባቶቹና እናቶቹ፡ በቅድሚያ ሲሠሩበት እንደኖሩት፡ አኹንም፡ "ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" እና "ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚሉት መለኮታውያን ትእምርተ ቃላት፡ በመካከሉ ተዋሕደው በማኅተምነት የሠፈሩበትን፡ ይህንኑ፡ የአረንጓዴ፡ ብጫና ቀይ ቀለማት ቅስት፡ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማው አድርጎ እየሠራበት ያለው፡ እርሱ፡ ኢትዮጵያዊው ብቻ፡ መኾኑ፡ ለዚህ ለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት አማናዊነት፡ ሌላው ምስክር ነው።

፫ኛ፡ በመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ ተመሥርቶ፡ በመካከለኛው መልከ ጼዴቅ ተጠናክሮና በመጨረሻው መልከ ጼዴቅ ለፍጹምነትና ለዘለዓለማዊነት የበቃው፡ የዛሬው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕያው ፍሬ፡ እርሱ ራሱ መኾኑን፡ በዚህ የቃል ኪዳን ጸሎቱ ያረጋግጣል፤ ይህ ቍም ነገር ሲብራራ፦

- የእግዚአብሔር መልክ በኾነችው፡ በረቂቋ ነፍስና በግዙፉ ሥጋ ተፈጥሮ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ክብር፡ በክርስትና የጥምቀት ጸጋ የተቀዳጀው፤

- የሴም፡ የካምና የያፌት ነገዶች ተዋሕደውበት፡ የአንድ ኖኅ ዘርነቱ የተረጋገጠበት፤

- በኪዳነ ልቦና ተመሥርቶ፡ በኪዳነ ኦሪት ጸንቶና በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ተፈጽሞ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የበቃው፤

- ቤተ ሕዝብነትን፡ ቤተ ምልክናንና ቤተ ክህነትን አጠቃልሎ የያዘው፡ በመልከ ጼዴቅ፡ "ኢትዮጵያዊ" የሚያሰኘውን መብትና ግዴታ ወርሶ የሚገኘው የዛሬው ሰው፡ እርሱ መኾኑን፡ ለራሱ፥ ለፈጣሪውና ለፍጥረተ-ዓለሙ በአዋጅ ይመሰክራል ማለት ነው።

ይህን እውነታ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በየምክንያቱና በተለያየው በዓሉ ላይ፡ "ጠበል ጠዲቅ" ብሎ፡ በሥነ ሥርዓት በሚያቀርበው፥ የመልከ ጼዴቅ የቃል ኪዳን ምልክት በኾነው ኅብስትና ጽዋ፡ ህልውናው፡ በሕያውነት እንዲቀጥል አድርጎታል።

፬ኛ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በሥጋ መገረዝን ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በልብ መገረዝን፡ ጥንት፡ ከአብርሃም በፊት ጀምረው፡ በኪዳነ ልቦና የአምልኮተ እግዚአብሔር ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው፡ ሲፈጽሙት የኖሩት ሥርዓታቸው መኾኑ፥ በኋላም ዘመን፡ ይህንኑ የግርዛት ሥርዓት፡ አብርሃም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ አማካይነት፡ አውቆትና ተምሮት፥ ተባርኮም፡ በሃይማኖት እንዲቀበለውና በምግባር እንዲያጸናው በመደረጉ ምክንያት፡ ይኸው የግርዛት ሥርዓት፡ በመለኮታዊው ቃል ኪዳን መጠናከሩ ይታወቃል።

## ምዕራፍ ፪፤ ሃይማኖት::
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሐተታ::

ኢትዮጵያዊው: በዚህ እውነታና በመጨረሻ: ለኃጢአት ስርየት በፈሰሰው: በኢየሱስ ክርስቶስ ደም: የአዲስ ኪዳን ዘለዓለማዊ ቅድስና በተሰጠው፥ እርሱም: በኢትዮጵያዊ ሰውነቱ በተቀበለው: ሥጋዊና መንፈሳዊ ግርዛቱ አምኖ: የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱንና ምግባሩን: እንደአብርሃም: ለፍጹምነት ለማብቃት የታደለ፥ ወደዚህ ግብ ለመድረስም: ከረቂቃኑና ግዙፋኑ ኃይላት ከሚወረወርበት ጦር አንጻር: በቆራጥነት የሚጋደል ሰብአዊ ፍጡር መኾኑን: በዚህ የቃል ኪዳን ጸሎቱ ዘወትር እያስታወሰ: ገድሉን ይቀጥላል::

ለአምልኮውም፥ ለምስጋናውም፥ ለሰላምታውም፥ ለአቤቱታውም፥ በደስታውም፥ በመከራውም፥ ለትንሹም፥ ለትልቁም፥ ለኹሉም ነገር: እጆቻቸውን: ወደፈጣሪያቸው ብቻ የሚዘረጉት ኢትዮጵያውያን: እስከዚያ ዘመን ድረስ: ማለትም: ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ: ታቦተ ጽዮን ወደኢትዮጵያ እስከመጣችበት: እስከንግሥተ ሳባና እስከልጇ ቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ ድረስ: በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር እየተዳደሩ: ፈጣሪያቸውን ያመልኩ የነበሩት: በኪዳን ልቦና እንደነበረ: ይህ የቃል ኪዳን ጸሎቱ: ኢትዮጵያዊዉን ያስታውሰዋል:: ይህ እውነታም: *"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤ ...እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፤ ...ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ፤ ...ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ፤"* ማለትም: *"ኢትዮጵያ እጇቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች፤ ...እግዚአብሔር: ግዙፋን ዓለም ከመፍጠሩ በፊትም ንጉሥ ነው፤ ...ኢትዮጵያውያን: በፊቱ ቆመው የሚያመሰግኑት ዜጎቹ ናቸው፤ ...አንተ ንጉሣቸው፤ እግዚአብሔር: ለኢትዮጵያ ሕዝብ: ለሕይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን ኹሉ ሰጠሃቸው፤"* በሚለው የነቢያት ቃል ተረጋግጦለት አብቅቷል::[፳፭]

፫ኛ: ኢትዮጵያዊው: በዚህ የቃል ኪዳን ጸሎቱ: ስለሙሴና ከእግዚአብሔር ስለተቀበለው ጽላተ ኪዳን: በሚመሰጥበት ጊዜ: ለቅዱሱ ኪዳን በበቃው ኢትዮጵያዊ ሰውነቱና ልቦናው ውስጥ አያሌ ትዝታዎች: በዓይነ ሕሊናው ይመለከታቸው ዘንድ: ሕያው ኾነው መጥተው ይደቀኑበታል:: ከእነዚህ መካከል: በዋናነት ሊወሳ የሚገባውን ዓቢይ ምክንያት: እዚህ ላይ እጠቅስላችኋለሁ::

ይህም: እሥራኤላዊው ሙሴ: ተወልዶ ካደገበት: ከግብፅ: ወደኢትዮጵያ እንዲኮበልል፥ በዚያም: ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶና ልጆችን ወልዶ: ለአርባ ዓመታት እንዲኖር፥ ስለሥነ ፍጥረት፥ ስለዓሠርቱ ትእዛዛት፥ ስለአምልኮተ እግዚአብሔርና መሥዋዕት አቀራረብ፥ ቤተ ሕዝብን፥ ቤተ ምልክናንና ቤተ ክህነትን አዋሕዳ ስለያዘችው: የእግዚአብሔር መንግሥት አስተዳደር ተምሮ እንዲያውቅ፥ በመጨረሻም: የእሥራኤል ልጆች: ይኖሩበት ከነበረው የባርነት ግዛት ነጻ ያወጣቸው ዘንድ: እግዚአብሔር: ከኢትዮጵያ: ወደግብፅ እንዲልከው መነሻ የኾነው ዓቢይ ምክንያት ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ያም ምክንያት፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተጽፎ፡ እንዲህ በሚል ቃል ይነበባል፡- *“ሙሴ፡ ካደገ በኋላ፡ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል፡ በሃይማኖት፡ 'እምቢ!' አለ፡ ለጊዜው፡ በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ፡ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር፡ መከራ መቀበልን መረጠ፡ ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ፡ ስለክርስቶስ፡ የመስቀል መከራን መቀበል፡ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲኾን አውቋልና:: በሃይማኖት፡ የንጉሡን ቍጣ ሳይፈራ፡ በግብፅ አገር ኖረ፡ ብድራቱን ተስፋ አድርጎ፡ ከሚታየው ይልቅ፡ የማይታየውን ሊፈራ ወድዷልና::”*[፳፯]

ከዚህ የሙሴ ዜና ሕይወት የተነሣ፡ ኢትዮጵያዊው፡ የዚህ የሃይማኖት ተጋዳይ፡ ታማኝና ጀግና አርበኛ ፍሬ በመኾኑ፡ ራሱን፡ ለዚህ ገድልና ድል ማብቃት እንደሚገባው በማመን፡ እርሱም፡ በየአፍታው ነቅቶና በቅቶ፡ የበኩሉን ግዳጅ ለመቀጠል፡ በተጠንቀቅና በቆራጥነት ተዘጋጅቶ እንዲገኝ፡ የቃል ኪዳን ጸሎቱ ዘወትር ያነቃቃዋል::

ሰው፡ ጥንት፡ ገና፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ *“እግዚአብሔር፡ ሰውን፡ በመልኩ ፈጠረ! ...ሰውም፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!”* በተሰኘው ሉዓላዊ ተፈጥሮው ምክንያት፡ የዓሥሩ ቃላት ታቦት፡ ከልቡናው ጋር አብሬው ተፈጥሬ፡ አብሬው ስትኖር ሣለ፡ እያደር፡ የሰው ልጆች ኹሉ፡ አንድ አንድ እያሉ ሲተዉዋት፡ የመልከ ጼዴቅ ትውልድ በኾኑት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ፡ ምንም እንከን በሌለበት ባሕርይዋ፡ ህልውናዋን ቀጠለች::

“መካከለኛ” በተባለው፡ በኋለኛው የሕግ ዘመን ግን፡ ስለወዳጆቹ፡ ስለአብርሃም፣ ስለይስሓቅና ስለያዕቆብ ሲል፡ የቃል ኪዳን ልጆቹ ሊያደርጋቸው የፈለጋቸው፡ “እሥራኤል” የተባሉት ወገኖች፡ በፈጸሙት የክህደት፣ የዐመፅና የምንዝርና ኃጢአታቸው ምክንያት፡ እግዚአብሔርን፡ እርሱ በሚወድደው፡ በእውነትና በመንፈስ ከሚያመልኩት ይልቅ፡ የሚታይና የሚዳሰስ አካል ያለውን ጣዖት መረጡ፤ እርሱም፡ የባለሟሉን የሙሴን አማላጅነት ተቀብሎ፡ እንደፍላጎታቸው ያመልኩት ዘንድ ስለተስማማ፡ ያችው፡ በልቡናቸው ውስጥ ያለችው፡ የዓሥሩ ቃላት ታቦት፡ በመለኮት ጣቶች፡ በጽላት ላይ ተጽፋና ገዝፋ፡ በቃል ኪዳን ተሰጠቻቸው፤ ይኹን እንጂ፡ እነርሱ፡ ከቀደመው ኃጢአታቸው “ይባስ!” ብለው፡ አኹንም፡ ከዚህ ቃል ኪዳናቸው ውጪ፡ በሃይማኖታቸውና በአምልኳቸው፥ በምግባራቸውና በኑሮአቸው፡ ፈጽመው፡ የፈጣሪያቸው ተቃዋሚዎች ኾነው በመገኘታቸው፡ በዚህ ኃጢአታቸው፡ እነርሱም፥ መኖሪያቸው ኢየሩሳሌምም ሊጠፉ ግድ ኾኖ ተገኘ::

በጊዜው ተፈጽሞ ከታየው፡ ከዚያ ፍርድ የተነሣ፡ እርሷ፡ ጽላተ ኪዳኑ፡ ከነታቦቷ፡ ቀደም ብላ፡ ወደኢትዮጵያ ኼዳ፡ የትስብእቱ ዘመን እስኪደርስ ድረስ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በአደራ ስትጠበቅና ስትመለክ እንድትቆይ፡ በፈጣሪ ተወስኖ ኖሮ፡ ይኸው ውሳኔ፡ በሥራ ላይ ዋለ::

# ምዕራፍ ፪፤ ሃይማኖት::
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሐተታ::

የመጨረሻውም የሕይወት ዘመን ደርሶ: ኢየሱስ ክርስቶስ: ከድንግል ማርያም: ሰው ኾኖ በመወለዱና በምድር ላይ በመመላለሱ: በፈጸመውም የቤዛነት መሥዋዕትነቱ: ይህችው ጽላተ ኪዳን: ከነታቦቷ: በመንፈስ ቅዱስ ጸድቃ: ለዘለዓለማዊ ሕያውነት በቃች::

ይህ በመኾኑ: "በቁርጥ ከፈለገ: ችሎታው አለው!" የሚባለው ሰብአዊው ፍጡር እንኳ: ተቋቁሞ ሊያሸንፈው ያቃተውን: ከፉዉን ኃይል: አጥፊውን ሥጋና ገዳዩን ፍትወት: ማለትም: ዲያብሎስን: በመለኮት ቃል: ኃጢአትን: በደሟ: ሞትንም: በመስቀል መከራዋ ድል አድርጋ: ቅዱሱን መንፈስ: የንስሓን ጸጋ: የትንሣኤ ሕይወትን: ለባለመብቱ የሰው ልጅ መልሳ አቀዳጀች::

እንዲህ: ኢየሱስ ክርስቶስንና ድንግል ማርያምን ኾና: ወደልዕልናዋ ካረገች በኋላም: በዘለዓለማዊው ዙፋኗ ላይ ተቀምጣ: በነፍሳውያንና በሥጋውያን ዘንድ: በሰማይም: በምድርም: በእውነትና በመንፈስ እየተመለከች: በፈጣሪነትና በፍጡርነት: በአባትነትና በእናትነት: በካህንነትና በመቅደስነት: በንጉሥና በንግሥትነት: የመንግሥት አስተዳደርዋን ታካኺዳለች::

ይህን ኹሉ: ወደር የማይገኝለትን የአምላክን የቸርነት ሥራ: ኢትዮጵያዊው ደህና አድርጎ ያውቃል:: እነሆ: ዛሬም: በእርሱ: የልብ ጽላት ላይ: በመንፈስ ቅዱስ ተቀርጻ: በልቦናውም አድራ የምትመራው: እርሱም እየኖራት ያለ መኾኑን: ይኸው የቃል ኪዳን ጸሎቱ: ኢትዮጵያዊዉን: ዘወትር ያስታውሰዋል::

፪ኛ:- እንኳንስ: በዓለም ላይ የሚኖሩት አሕዛብ ቀርተው: በአብርሃም: በይስሓቅና በያዕቆብ ምክንያት: "የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ወገን ነን!" የሚሉት እሥራኤል እንኳ: "ኢየሱስ ክርስቶስ: አምላካችንም፥ መሢሓችንም፥ መድኃኒታችንም፥ ንጉሣችንም አይደለም!" ብለው በይፋ የካዱትና የተቃወሙት፥ አሳልፈው ሰጥተው ያስገደሉትም መኾናቸው: በወንጌላውያኑ የምስክርነት ቃል ብቻ ሳይኾን: ዛሬም: በሕይወተ ሥጋ ባሉት ትውልዶቻቸው ዘንድ እውን ኾኖ መታየቱ ይታወቃል::

ኢትዮጵያውያን ግን: ኢየሱስ ክርስቶስ: የእግዚአብሔር ልጅ እንደመኾኑ: አምላክነቱንና መሢሕነቱን፥ መድኃኒትነቱንና ሊቀ ካህናትነቱን ብቻ ሳይኾን: ንጉሥና ንጉሠ ነገሥት መኾኑን ጭምር በሃይማኖት ተቀብለው: በማረጋገጥ: በራእየ ዮሓንስ: *"ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!"* የሚለውን: መለኮታዊ ቃል: ብሔራዊ ማኅተማቸውና ምልክታቸው አድርገው: በይፋ ሲሠሩበት: እስከዛሬ ኖረዋል፥ እነሆ: ዛሬም እየኖሩ ናቸው፤ ወደፊትም: ይኖራሉ:: ይህም የኾነው: እግዚአብሔር: ለዳዊት የሰጠው የተስፋ ቃል: የዳዊት ዘር ከኾነችው: ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል: ከቅድስት ማርያም: በተወለደው በኢየሱስ ክርስቶስ: ለፍጻሜ ፍሬ በቅቶ በመገኘቱ ነው:: ያም የተስፋ ቃል: *"ዘርህን: ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፥ መንግሥቱንም አጸናለሁ:: ...ዙፋኑንም: ለዘለዓለም አጸናለሁ:: እኔም አባት እኾነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይኾነኛል::"* የሚለው ነው::[፳፯]

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ኢትዮጵያዊው፡ ይህን የቃል ኪዳን ጸሎቱን፡ ለራሱም ኾነ በማኅበር መካከል በሚጸልይበት ጊዜ፡ ያ መለኮታዊ የተስፋ ቃል፡ በእንዴት ያለ ዕቅድ፡ ይዘትና አካኼድ ተከናውኖ፡ ከመጨረሻው ግብ ሊደርስ የቻለበትን የአምላክ ጥበብ፡ በአንክሮና በተመስጦ ያዘክራል። የሚያዘክረውም፡ እግዚአብሔር፡ የጽላተ ኪዳኑን ታቦት ብቻ ሳይኾን፡ ይህን የዳዊትን የቃል ኪዳን ዘር ጭምር፡ ወደኢትዮጵያና ወደኢትዮጵያውያን እንዲመጣ ለማድረግ፡ በባሕርይ ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት "የደቡባ ንግሥት" ብሎ የጠራትን፡ ኢትዮጵያዊቷን ንግሥት ማክዳን፡ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ወደሚኖርባት ወደኢየሩሳሌም እንድትኼዝ ያደረገበትን ታላቅ ቸርነቱን በማሰብ ነው።

አዎን! የቅዱሱ ኪዳን ሰንሰለት፡ ሦስተኛው ቀለበት የኾነው፡ የመልከ ጼዴቅ የቃል ኪዳን ዘር ያስገኘት፡ ድንግሊቱ ኢትዮጵያዊት ንግሥት ማክዳና የቅዱሱ ኪዳን ሰንሰለት፡ ስድስተኛው ቀለበት የኾነው፡ የዳዊት የቃል ኪዳን ዘር ያስገኘው፡ እሥራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን፡ በእግዚአብሔር ስምና ፍቅር ተገናኝተው፡ እግዚአብሔር ወልድን በሰውነት የምትወልደውን ቅድስት ድንግል ማርያምን የሚያስገኘውን የውሕደት ዘር አፍርተው እንዲያልፉ የተደረገበት መለኮታዊ ምሥጢርና ጥበብ፡ እውን ኾኖ የሚፈጸም መኾኑን፡ እግዚአብሔር፡ አስቀድሞ፡ በገሃድ ያሳወቀበትን ድንቅ ሥራውን፡ ኢትዮጵያዊው፡ በዚህ ጸሎቱ ጊዜ፡ በታላቅ አንክሮና በጥልቅ ተዘክሮ ያስታውሳል። ከሚያስታውሳቸው፡ የአምላኩ ድንቅ ሥራ ጣፋጭ ፍሬዎች መካከል፡ ከዚህ የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

- መለኮታዊ ቃሉ የተጻፈባቸው ኹለቱ ጽላት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም የወረሳቸው፡ የሰውነቱ ነፍስና ሥጋ አርአያዎች መኾናቸው፡

- ዓሥሩ ቃላት፡ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ፡

- የኋላ ኋላ፡ ጽላተ ኪዳኑና የድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነችው፡ ጽላተ ኪዳኑን የያዘችው ታቦት፡ ኹለቱም፡ ወደኢትዮጵያ ኼደው፡ በዚያ፡ በኢትዮጵያዊነት መኖራቸው፡

- እግዚአብሔር፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ የሰጠው፡ ዘለዓለማዊው የቃል ኪዳን ምሕረቱ የተገኘው፡ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን መኾኑ፡

- የኢትዮጵያዊነት አብነት እንደኾነው፡ እንደቀዳሚ ምሳሌው፡ እንደመልከ ጼዴቅ፡ በቤተ ሕዝብ ወገንነቱ፥ በቤተ ክህነት ሥልጣኑና በቤተ ምልክና ሹመቱ ብቻ ሳይኾን፡ ከኢትዮጵያዊት እናቱ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት በመወለዱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በትውልዱና በመልኩ ጭምር ኢትዮጵያዊ መኾኑ፡

## ምዕራፍ ፱፣ ሃይማኖት።
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሐተታ።

- ይኸው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደአይሁድ የተላከው፡ ልክ፡ እንደኢትዮጵያዊው ነቢዩ ኤርምያስና የእሥራኤልን ልጆች፡ ከግብፅ የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ ያወጣቸው ዘንድ፡ የእርሱ ሌላ አርአያው የኾነውን፡ ሙሴን፡ እግዚአብሔር፡ ወደፈርዖን በላከው ዓይነት፡ በኢትዮጵያዊነቱ መኾኑ፤

- ያን ሙሴን፡ እግዚአብሔር፡ ለዚያ ተልእኮ የመረጠውና የጠራው፡ አስቀድሞ፡ በጣዖት አምልኮ ከኖረበት፡ ከግብፅ፡ ወደኢትዮጵያ አምጥቶ፡ ስለአምልኮተ እግዚአብሔርና ስለኢትዮጵያዊነት፡ ከኢትዮጵያዊው ካህን፡ ከዮቶር፡ የተሟላ እውቀትን እንዲያገኝና እነዚህን ምስጢራት፡ በሃይማኖት እንዲቀበል ካደረገ፡ ኢትዮጵያዊቷን፡ የዮቶርን ልጅ፡ ሲጳራን አግብቶ፡ ልጆችን ከወለደም በኋላ መኾኑ፤

- ከዚህ የተነሣ፡ *"ሞዐ አንበሳ"*፡ ወይም፡ *"ድል አድራጊው አንበሳ"* የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ኢትዮጵያዊ በመኾኑ፡ አንበሳው፡ የእኛ የኢትዮጵያውያን፡ የብቻችን ብሔራዊ፣ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ምልክታችን ኾኖ መኖሩ፤ እውነተኞቹ እሥራኤላውያንም፡ እኛ ኢትዮጵያውያን መኾናችን፤

- *"ሞዐ አንበሳ"* ከሚለው ቃል ጋር፡ *"ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው ሐረግ፡ ተያይዞ የሚነበብበት ምክንያት፡ ኹለት መሠረታውያን መነሻዎች ያሉት ሲኾን፡ ከእነዚህ መካከል፡ ፩ኛው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በኢትዮጵያዊነቱ፡ የኖኅ ልጆች ከኾኑት፡ ከካምና ከያፌት ብቻ ሳይኾን፡ የሴም ነገድ ከኾነውና "እሥራኤል" ከተባለው፡ ከያዕቆብ፡ ልጅ፤ እርሱም፡ *"ሥርወ ለዳዊት"*፤ *ወይም፡ "የዳዊት ሥር"* ከተባለው፡ ከይሁዳ ዘር፡ *ከዳዊትም* መወለዱን ለማመልከት መኾኑ፤ ፪ኛውም መነሻ፡ *"ይሁዳ፡ የአንበሳ ደቦል ነው! ...ገዢ የኾነው እስኪመጣ ድረስ፡ በትረ መንግሥት፡ ከይሁዳ አይጠፋም!"* ሲል፡ እግዚአብሔር፡ ከ፲፪ቱ የያዕቆብ ልጆች መካከል ፩ዱ ለኾነው፡ ለይሁዳ፡ በአባቱ አንደበት፡ የሰጠውን የተስፋ ቃል መሠረት የሚያደርግ መኾኑ፤

-ይኹን እንጂ፡ ለእግዚአብሔር፡ ስለቸርነቱ፡ ምስጋናችን፤ ለወላጆቻችንም፡ ስለታማኝነታቸው፡ ባለውለተኛነታችን ይድረሳቸውና፡ "አይሁድ" የተባሉት የእሥራኤል ሕዝብ፡ ቀድሞ፡ በሙሴ ላይ፤ ኋላም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በፈጸሙት ክህደት፤ ዓመፅና አመንዝራነት ምክንያት፡ ለዚህ የተስፋ ቃል፡ ሊበቁ ስላልቻሉ፡ በሙሴ አማካይነት፡ ለእሥራኤል ተሰጥታ የነበረችው፡ የድንግል ማርያም አርአያ የኾነችው፡ ጽላተ ኪዳኑና የኢየሱስ ክርስቶስ መታወቂያ የኾነው፡ *"ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!"* የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ ኹለቱም፡ ከቃል ኪዳን ባለቤቶቻቸውና በረከቶቻቸው ጋር፡ የኢትዮጵያውያን ሀብታት መኾናቸው ናቸው።[፳፰]

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

፯ኛ:- እግዚአብሔር፡ በመልኩ ለፈጠረው የሰው ዘር፡ በሥጋዊዉና በመንፈሳዊው የሥነ ፍጥረቱ ዓለም፡ በሥርዓት አዘጋጅቶለት የነበረው፡ የመልካም ሕይወት ህልውና፡ የክፋትና የሐሰት አበጋዝ በኾነው፡ በዲያብሎስ ወጣኝነትና አነሣሽነት፡ በሰብአዊው ፍጡሩም ፍላጎትና ምርጫ እንደተቃወሰ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በሃይማኖቱ ተገንዝቦታል።

በዚህ ምክንያት፡ በምድር ላይ እየቀጠለ የኼደው የኃጢአት ሥራ፡ ጽዋው ሞልቶ፡ በኖኅ ዘመን ከኾነው ጥፋት የባሰ ጠቅላላ ድምሳሴን ሊያደርስ በተቃረበበት ጊዜ፡ ራሷን፡ ለአምላክ እናትነት ያበቃች አንዲት ድንግል፡ በሰዎች መካከል እንደምትገኝና ፍጥረተ-ዓለሙን ከፍጹም መደምሰስ ለማዳን፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፡ ከእርሷ፡ በሰውነት እንደሚወለድ አስቀድሞ ያወቀው ፈጣሪ፡ ለአዳምና ሔዋን የሰጣቸው ተስፋ መኖሩንም፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ ያምናል።

በዚያ የተስፋ ቃል መሠረት፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ያለወንድ ዘር፡ በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ግብር፡ በዚያች ድንግል ማኅፀን፡ በሰውነት ተፀንሶና ተወልዶ፡ ተጠምቆና አስተምሮ፤ ከዲያብሎስ ተፈትኖና የመስቀል መከራን ተቀብሎ፡ ሙቶና ተነሥቶ፤ ዐርጎና በመንፈስ ቅዱስ እንደገና ወደዚህ ዓለም ተመልሶ፡ የጠፋውን፡ ከበደሉ ጽናት የተነሣም፡ ሙቶ የነበረውን፡ የሰውን ልጅ ፈልጎ ማግኘቱን፡ ስለበደሉ ካሣ፡ ራሱን በቤዛነት በማቅረብ፡ ይቅር ብሎና ሕያው አድርጎ፤ ለመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ ካበቃው በኋላ፡ እነሆ፡ ጥንቱን አዘጋጅቶለት ወደነበረው ወደመልካሟ ሕይወት የመለሰው መኾኑን፡ ኢትዮጵያዊው፡ የቃል ኪዳን ጸሎቱን በሚጸልይበት ጊዜ፡ ይህን ትንግርት፡ በራሱ ሰውነትና ህልውና ያረጋግጣል።

ለዚህ እውነታም፡ ኢትዮጵያዊው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ወርሶ፡ በቤዛነትና በመሥዋዕትነት ያበረከተለትን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በመቀበል ዐትሞ፡ የመጀመሪያው ትንሣኤ ባለቤትነቱን ከማጽናት ጋር፡ ቦታና ጊዜ በማይወስነው፥ ጸጋው፡ በምልዓት በተሰጠውና ምንም ኃይል ሊቋቋመው በማይቻለው፡ በመጨረሻው የመንፈስ ቅዱስ ኪዳን፡ ዘለዓለማዊዉን የንግሥ ዘውድ ተቀዳጅቶ፡ ምሳሌ በሌላት በእግዚአብሔር መንግሥት የጀመረውን ህልውናውን ለመቀጠል መብቃቱ ምስክር ነው።

እንግዴህ፡ ከመሠረቱ ጀምሮ፡ በግድግዳው ቋሚነት ተያይዞና ወደጣሪያነት አድጎ፡ በጉልላት እንደሚደመደመው ሕንፃ፡ ኢትዮጵያዊዉም ሰውነት፡ እንዲሁ፡ በመጀመሪያዎቹ ሰዎች፡ በአዳምና በሔዋን ልደት ተመሥርቶ፡ በሌሎቹ ቅዱሳት ቃል ኪዳናት ተካያጆች (ተዋዋዮችን) ግድግዳነት ቁመቱ ካደገ በኋላ፡ ለጠፈርነትና ለጣሪያነት ሲበቃ፡ የመጨረሻዎቹና ዘለዓለማውያኑ አዳምና ሔዋን በኾኑት፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ጉልላትነት፡ ለፍጹምነት የበቃ መኾኑን፡ ኢትዮጵያዊው፡ በዚህ የቃል ኪዳን ጸሎቱ፡ ለራሱ፥ ለፈጣሪውና ለሌላው የተፈጥሮ ወገኑ ያሳውቃል።

# ምዕራፍ ፪፡ ሃይማኖት።
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሓተታ።

ኢትዮጵያውያኑ፡ ተረክበውና ይዘው፡ አክብረውና ጠብቀው ከሚኖሩባቸው፡ ከቀደሙት ቅዱሳት ቃል ኪዳናት ጋር፡ እግዚአብሔር፡ ለእሥራኤላውያኑ፡ ማለትም፡ ለአብርሃም፡ ለሙሴና ለዳዊት የሰጣቸውን፡ ሦስት ቃል ኪዳናት እንኳ ሳይቀር፡ ኹሉንም፡ እንዴት ወደኢትዮጵያ መልሶ አምጥቶ፡ ቅዱሱን ኪዳኑን፡ ለፍጹሙ ሰባትነት ማብቃቱን፡ ኢትዮጵያዊው ያምናል።

ኢትዮጵያዊው፡ በዚህ የቃል ኪዳን ጸሎቱ ጊዜ፡ በአንክሮና በተዘክሮ ከሚመሰጥባቸው የአምላክ ሥራዎች መካከል፡ እግዚአብሔር፡ ኢትዮጵያውያንን፡ ለቅዱሱ ኪዳን፡ ባለአደራነት ጠርቶ የተቀበለበት ቸርነቱና ጥበቡ፡ አንዱ ኾኖ ስለሚያገኘው፡ በመንፈሳዊ ደስታና ምስጋና ይመሰጣል። በዚህም፡ *"የእሥራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር።"*[፳፱] የሚለው፡ የነቢዩ ትንቢት እውንና እሙን መኾኑን ያረጋግጣል።

ጥያቄ፡- *ግሩም ነው! ዕፁብ ድንቅ ነው! ራሱን፡ ለዚህ ማንነት ያበቃ፡ ሰብአዊ ፍጡር፡ ምንኛ ብፁዕ ነው? ራሱን፡ ለዚህ ማንነት ያሳበቃ ሰብአዊ ፍጡር፡ ወይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ከሚለው መካከል፡ ይህን የመሰለው ጸጋ የቀረበለት መኾኑን የማያውቀው፡ ወይም "አውቄአለሁ!" ብሎ፡ ነገር ግን፡ ይህንኑ ጸጋ መቀበልን "እምቢ!" ያለው ወገን፡ ከቶ፡ የቱን ያህል ተጎድቶ የሚኖር ነው? እንዲህ ብርሃን የኾነው፡ የእግዚአብሔር ምሥራች ያለበትን ቃል መስማትስ፡ እንዴት መታደል ነው?*

*ስለተሰማን ደስታ፡ ይህን ያህል ከገለጽንልህ፡ የሚቀጥለውን፡ የጸሎቱን ክፍል እናቅርብልህ! ይኸውም፡* "ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን፡ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።" *የሚለው ነው።*

መልስ፡- አኹንም በማስተዋል ተመልከቱ! ኢትዮጵያ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን ባለመዘንጋትና ይህን እውነታ መሠረት በማድረግ፡ እዚህ ላይ "ኢትዮጵያ" ስንል፡ ሕያው ኾኖ፡ ዛሬ እየኖረ የሚገኘውን፡ እናንተንና እኔን የሚጨምረውን፡ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሰውነት መኾኑን፡ ጸሎቱ ይነግረናል፤ እናንተም፡ ልብ አድርጉት! ቀደም ብሎ፡ በየቦታው በተወሳው በኪዳነ መልከ ጼዴቅ ሓተታ ውስጥ እንደተብራራው፡ ይህ ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ በመልከ ጼዴቅ ልጅነቱ ምክንያት፡ ሦስቱ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የአገልግሎት ዘርፎች የኾኑትን፡ ቤተ ሕዝብን፡ ቤተ ክህነትንና ቤተ ምልክናን፡ በሥጋውና በነፍሱ፥ በመንፈሱም ኹለንተና አዋሕዶ የያዘ በመኾኑ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ፡ በዚሁ፡ በሕይወት ቆሞ በሚኖረው፡ በዛሬው ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ ህልውናዋን ቀጥላለች ማለት ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

አዎን! "ኢትዮጵያ" ማለት፡ እያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ እውነተኛ ኢትዮጵያዊት እንደመኾናቸው መጠን፡ በእነሀ የሰውነት ኹለንተና ውስጥ ሰፍና ያለችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥትም፡ እኒሁ፡ እየራሳቸው፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት መኾናቸውን፡ የቃል ኪዳኑ ጸሎት፡ ለኢትዮጵያዊው ግለሰብ፡ አበክሮ ያስታውሰዋል:: በሌላው የኪዳን ጸሎታችን፡ *"በአልባቢነ፡ ናስተማስል፡ አምሳለ መንግሥትከ ቡቱ" ማለትም፡ "መንግሥትህ፡ በየልቡናችን ላይ እንድትመሠረት፡ በዚያም ሰፍና እንድትኖር አደረግህ::"* የሚለው ሐረግ፡ ይህን እውነታ ያጠናክረዋል::

በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በአገራችን ላይ በደረሰው የፋሺስት ኢጣልያ ወረራ ጊዜ፡ የሞት ፍርድ ተሰጥቶባቸው፡ ሰማዕትነትን የተቀበሉት፡ ኢትዮጵያዊው አቡነ ጴጥሮስ፡ *"ይህ አኹን ያለንበት፡ ዓለም ሌላ ነው፤ ዓይንዎን አይከፍቱም?*

*"እንዲያና ኢትዮጵያዊ፡ 'ኢትዮጵያ' የሚሏት የለችም!"*

ላሉቸው፡ ለአንድ፡ የጠላት አገልጋይ ለኾነ፡ ከሓዲ ያገሩቸው ሰው፡

*"አዎን! አንተ ውስጥ የለችም፡*

*ምክንያቱም፡ አታምንባትም::*

*"አንተ፡ በእግዚአብሔር አታምንም፤*

*"ወይም፡ በአገርህ አታምንም፡*

*ወይም፡ በራስህ አታምንም::*

*"ስለዚህ፡ የእምነት ምስኪን ነህ!*

*መተማመኛ የሌለህ!*

*"እና፡ ለእኔ አታስብ! ቀድሞ፡ ለራስህ አታውቅም፤*

***"እኔ፡ ግን፡ በኢትዮጵያ ስለማምን፡***

***እኔ እስክሞትሁ፡ እርሷ አትሞትም!"***

እንዳሉት ማለት ነው:: የእኒህን ስመ ጥሩ ባለሙያ ኢትዮጵያዊ ዝክረ ነገር፡ ባለፈው ውይይታችን ላይ፡ በአርአያነቱ አውስተነው እንደነበረ፡ ይታወሳል::

የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ፡ በዚህ የመጨረሻው ዘመን፡ እንዲህ፡ በሕያውነቷ ቀጥላ መገኘቷ ይበጃል፤ የሚበጀውም፡ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይኾን፡ ለቀሩትም የዓለም ሕዝቦች ነው፤ ስለዚህ፡ ኹሉም፡ ለየራሳቸው ደኅንነት ሲሉ፡ ስለህልውናዋ ሊያስቡና ሊጨነቁ ይገባቸዋል:: ዓለም፡ ከመጨረሻው ጥፋት የሚድነው፡ በእርስዋ ብቻ ነውና::

ጥያቄ:- *አኹንም፡ ቸር ዜና አሰማኸን! እግዜር ይስጥልን! ከዚህ የሚቀጥለው የጸሎቱ ክፍል፡* "እርሱ፡ 'ክርስቶስ' ተብሎ፡ እኛን 'ክርስቲያን' ያሰኘን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀደመው ዘመን፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን::" *የሚለው ነው::*

## ምዕራፍ ፬፤ ሃይማኖት።
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሐተታ።

መልስ፡- ይህና ከእርሱ ተያይዘው ያሉት፡ የጸሎቱ ተከታታይ የሃይማኖት ማረጋገጫ አንቀጾች፡ አብዛኛዎቹ፡ እስካኹን፡ በዝርዝር የተነጋገርናቸውን የቅዱሱን ኪዳን፡ ንዑሳን አርእስት፡ እጥር ምጥን አድርገው፡ ለአጽንዖትና በአጽንዖት የሚያቀርቡ ናቸው። ከዚህ የተነሣ፡ ስፊ ሐተታ ሊሰጥባቸው የሚያስፈልጋቸው ስላልኾኑ፡ ለእያንዳንዳቸው፡ አጫጭር የማጠናከሪያ ቃላትን በመስጠት እናልፋቸዋለን።

እኹን የሰማነው የጸሎቱ ክፍል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ማን እንደኾነ፡ ለኢትዮጵያዊዉም፡ ምኑ እንደኾነ፡ ለራሱ ለባለጸሎተኛው ኢትዮጵያዊ፡ ተረጋግጦ የተገለጸበት፡ ኢትዮጵያዊዉም፡ ይህን እውነታ፡ በፍጹም እውቀት ተቀብሎ፡ በሃይማኖት ያጸናው መኾኑን፡ ለራሱና ለአምላኩ፡ ለሌላውም የተፈጥሮ ወገኑ፡ ዘወትር የሚያረጋግጥበት የምስክርነት ቃል ነው።

ጥያቄ፡- *መልካም! ከዚህ የሚቀጥለው የጸሎቱ ክፍል፡* <u>"እርሷ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን "ኢትዮጵያውያን" ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕያዋን እናትና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፡ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን።"</u> *የሚለው ነው።*

መልስ፡- ይህም አንቀጽ፡ ድንግል ማርያም፡ ማን እንደኾነች፡ ለኢትዮጵያዊዉም፡ ምኑ እንደኾነች፡ ለራሱ ለባለጸሎተኛው ኢትዮጵያዊ፡ ተረጋግጦ የተገለጸበት፤ ራሱ፡ ኢትዮጵያዊዉም፡ ይህን እውነታ፡ በፍጹም እውቀት ተቀብሎ፡ በሃይማኖት ያጸናው መኾኑን፡ ለራሱና ለአምላኩ፤ ለሌላውም የተፈጥሮ ወገኑ፡ ዘወትር የሚያረጋግጥበት የምስክርነት ቃል ነው።

ጥያቄ፡- *የሚቀጥለው የጸሎቱ ክፍል ደግሞ፡* <u>"አረንጓዴ ብጫ ቀይ የኾነው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን።"</u> *የሚለው ነው።*

መልስ፡- ይህም አንቀጽ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ዛሬ፡ በያለበትና በየምክንያቱ አንግቦት የሚያውለበልበው፡ አረንጓዴ፤ ብጫና ቀይ ኅብረ ቀለማት ያለው ሰሌዳ፤ በሰሌዳው መካከልም ላይ፡ እጆቿን ወደሰማይ የዘረጋችውን፡ የድንግል ማርያምንና የድል አድራጊውን አንበሳ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥዕሎች የያዘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ማኅተም የሠፈረበት ሰንደቅ ዓላማው፡ አገሩና እርሱ፡ በአምላካዊው ኃይል ተጠብቀው፡ መልካም ህልውናቸውን፡ በሚያስተማምን አቋም ይቀጥሉ ዘንድ፡ ከፈጣሪው ያገኘው መኾኑን አውቆ፡ ፈጣሪው፡ ከእርሱ የሚጠብቀውን የቃል ኪዳን ግዳጅ፡ እንደኖኅ መፈጸሙን፡ ለራሱ የሚያስታውስበት፤ ይህንም እውነታ፡ በፍጹም እውቀት ተቀብሎ፡ በሃይማኖት ያጸናው መኾኑን፡ ለራሱና ለአምላኩ፤ ለሌላውም የተፈጥሮ ወገኑ፡ ዘወትር የሚያረጋግጥበት የምስክርነት ቃል ነው።